# አዲስ ዘመን

እንድ

እሁድ 82ኛ ዓመት ቁጥር 106 ታኅሣሥ 16 ቀን 2015 ዓ.ም ዋጋ 10.00 ብዕራችን ለኢትዮጵያ ህዳሴ ይተጋል!





ፎቶ ሳሙኤል ተስፋዬ

# ኢትዮጵያን እግር ከወረች ከያዛት የሙስና ችግር ለማላቀቅ የምርመራ ጋዜጠኝነትን ማጎልበት ያስፈልጋል

- ሙስናን ለመከላከል የሚያስችል የኤሌክትሮኒክስ የግዢ ሥርዓት ተግባራዊ መሆን ጀምሯል
- የተጀመረውን የጸረ ሙስና ትግል ሚዲያዎች ሊያግዙ ይገባል

**ወርቁ ማሩ**

አዳማ፡-ለጋራ እሴቶቻችን እድገት እና ለሕዝብ ተጠቃሚነት እንቅፋት የሆነውን ሙስና ለመዋጋት ሚዲያዎች የጸረ ሙስና ትግሉን መቀላቀል እንዳለባቸው የመንግሥት ኮሙኒኬሽን አገልግሎት ሚኒስትር ለገሰ ቱሉ (ዶክተር) ገለጹ፡፡

የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ስልጠና ማዕከል ትናንት በአዳማ ከተማ ከተለያየ የግልና የመንግሥት ሚዲያዎች ለተውጣጡ የሚዲያ ኃላፊዎችና ባለሙያዎች በምርመራ ዘገባ ዙሪያ ባዘጋጀው የሁለት ቀናት ሥልጠና ላይ የመንግሥት ኮሙኒኬሽን አገልግሎት ሚኒስትር ለገሰ ቱሉ (ዶክተር) እንደገለጹት፤ መንግሥት ለዴሞክራሲያዊ ሥርዓት መጎልበት፣ ለጋራ እድገትና አገራዊ እሴቶች እድገት በርካታ ስራዎችን እያከናወነ ይገኛል፡፡ በተለይ ኢትዮጵያን እግር ከወረች ከያዛት የሙስና ችግር ለማላቀቅ የምርመራ ጋዜጠኝነትን ማጎልበት ያስፈልጋል፡፡

በተለይ ከለውጡ ወዲህ የተጀመሩ የሪፎርም ስራዎች የታለመላቸውን ስኬት እንዲያስመዘግቡ ለማድረግ ጥረቶች ሲደረጉ መቆየታቸውን የተናገሩት

ኢትዮጵያን እግር ከወረች ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል



ፎቶ ፀሐይ ንጉሤ

## በጦርነት ጉዳት የደረሰባቸው ኢንዱስትሪ ፓርኮችን ዳግም ወደ ሥራ ስመመለስ እየተሠራ ነው

- የመቀሌን የኢንዱስትሪ ፓርክ ዳግም ስራ ማስጀመር የሚያስችሉ እንቅስቃሴዎች ተጀምረዋል

**ፋንታነሽ ክንዴ**

አዲስ አበባ፡- በሰሜኑ የአገራችን ክፍል በነበረው ጦርነት ጉዳት የደረሰባቸውን ኢንዱስትሪ ፓርኮች ዳግም ወደ ሥራ ለመመለሥ እየተሠራ መሆኑን የኢንዱስትሪ ፓርኮች ልማት ኮርፖሬሽን አስታወቀ፡፡

የኮርፖሬሽኑ የማርኬቲንግና ኮሚኒኬሽን መምሪያ

በጦርነት ጉዳት የደረሰባቸው ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል



## “ሕገ-ወጥ የሰዎች ዝውውር በሰው ደም የሚረማመዱ ጨካኞች የሚተውኑት አሰቃቂ ድርጊት ነው”

- አቶ ደመቀ መኮንን

**በጋዜጣው ሪፖርተር**

አዲስ አበባ፡- ሕገውጥ የሰዎች ዝውውር በሰው ደም የሚረማመዱ ጨካኞች የሚተውኑት አሰቃቂ ድርጊት መሆኑን ሁሉም ሊገነዘብ እንደሚገባ ምክትል ጠቅላይ ሚኒስትርና የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ደመቀ መኮንን ገለጹ።

በለውጥ ሂደት ፈተናዎች የሚጠበቁ ቢሆንም ችግሩን መቀነስና ውጤቱን ማበልጸግ ከመንግሥትና ሕዝብ የመጠበቅ ተግባር መሆኑን ገልጸዋል።

በኢትዮጵያ የደቡብ ክልል ሀድያና አካባቢው፣ በአማራ ክልል ወሎና ኦሮሞ ብሔረሰብ አስተዳደር፣ እንዲሁም አንዳንድ የኦሮሚያ አካባቢዎች ከፍተኛ ሁኔታ

“ሕገ-ወጥ የሰዎች ዝውውር ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል


ደርባ ሚድሮክ ሲሚንቶ ኃ/የተ/የግል ማህበር

በልዩ የደርባ ሲሚንቶ መስመር 8688 ወይም
- 0111 26 26 27 - 0922 11 53 24/26
- 0111 26 26 28 - 0922 72 74 48/49
- 0111 26 26 29 - 0922 72 38 70
- 0111 26 26 30 - 0922 72 38 72

ፋክስ፡- 0111 26 23 45 እና 0111 26 23 18

ይዘዙን

ደረጃቸውን ጠብቀን የምናመርታቸውን ጥራት ያላቸው የሲሚንቶ ምርቶች ቤትዎ ወይም ፕሮጀክትዎ ደጃፍ ላይ ያለውጣ ውረድ በደርባ ትራንስፖርት ኃ.የተ.የግ.ማ አማካይነት እናቀርባለን።

ነገን ዛሬ እንሥራ



ፀደይ ባንክ (አ.ማ)
TSEDEY BANK (S.C)

የሁሉም ባንክ
Bank for all !

የብዙዎችን ተስፋ ያለመለመ !

በፋይናንስ አቅርቦት በተግባር የተፈተነ እንዲሁም ሰፊና ጽኑ መሰረት ያለው ባንክ በአነስተኛ የፋይናንስ አገልግሎት ዘርፍ በአገለገለባቸው 25 ዓመታት አለም አቀፍ ዕውቅናዎችን ሲያገኝ የቆየው አማራ ብድርና ቁጠባ ተቋም ወደ ፀደይ ባንክ ተሸጋግሮ የተሟላ አገልግሎት በመስጠት ላይ ይገኛል።

Tel: +251 115 58 12 70/011 551 73 48/011 558 99 98
P.O.Box: 9630
E-mail: mekonnenyelewemwessen@tsedeybank-sc.com
Web: www.tsedeybank.org.et
Addis Ababa, Ethiopia



eccs

የኢትዮጵያ የግንባታ ግብዓቶች አቅራቢ ኃ/የተ/የግል ኩባንያ
ETHIOPIAN CONSTRUCTION COMMODITIES SUPPLY PLC.

የአርማታ ብረት እና ሌሎች ብረታብረቶች አከፋፋይ

Mob. 0911 225057/ 0989 343434

አድራሻ፡ ከሜክሲኮ አደባባይ ወደ መርካቶ በሚወስደው መንገድ ከዲ-አፍሪክ ሆቴል ፊት ለፊት



ከወዳጅ ዘመዶቻችን ጋር ወደ ሁሉም የሀገር ውስጥ ኔትዎርክ እንደውል

ልዩ ጉርሻ

25 ብር — 75 ደቂቃ — 100 ሜጋ ባይት
50 ብር — 150 ደቂቃ — 500 ሜጋ ባይት
100 ብር — 300 ደቂቃ — 1 ጂ.ቢ

ሂሳብዎን ለመሙላት ወደ *705# ይደውሉ

Safaricom
ሳፋሪኮም



አዳማ ቆርቆሮ ፋብሪካ
ADAMA STEEL FACTORY

ሚስማር ከ3 ቁጥር -15 ቁጥር

የበረንዳ ታይልስ ኤጋ መደበኛ ኮልሞ

0940 505050/0940 606060/0940 909090/0940 808080/0920 656565


## የከተማ አስተዳደሩ የገዛቻው 100 አውቶብሶች በቅርቡ ወደ አገር ይገባሉ

ገጽ 4



የቱሪዝም ሚኒስትር ዴኤታ ሰላማዊት ዳዊት

## ስገና እና ጥምቀት በዓላት ወደ አገራቸው የሚመጡ ዳያስፖራዎችን ስመቀበል ዝግጅት እየተደረገ ነው

በጋዜጣው ሪፖርተር

አዲስ አበባ፡- የገና እና ጥምቀት በዓላትን ለማክበር ወደ አገራቸው የሚመጡ ኢትዮጵያውያንና ትውልደ ኢትዮጵያውያንን ለመቀበል ዝግጅት እያደረገ መሆኑን የቱሪዝም ሚኒስቴር ገለጸ።

የቱሪዝም ሚኒስትር ዴኤታ ሰላማዊት ዳዊት እንደገለጹት፤ በ2014 ዓ.ም "ጉዞ ወደ አገር ቤት" በሚል የተጀመረው መርሃ-ግብር በየዓመቱ ይቀጥላል። በዚህ ዓመት በሚከበረው የገና እና ጥምቀት በዓላት የተደረገውን የሰላም ስምምነት ተከትሎ በድምቀት ለማክበር ዝግጅት እየተደረገ ይገኛል።

በዓላቱን ለማክበር ወደ አገራቸው ለሚመጡ ኢትዮጵያውያን፣ ትውልደ-ኢትዮጵያውያና የኢትዮጵያ ወዳጆች ከኢትዮጵያ አየር መንገድና ሌሎች አጋር አካላት ጋር እየተሰራ መሆኑን ገልጸዋል።

የመሰረተ-ልማትና ሌሎች ቅድመ-ዝግጅቶች መደረጉን ጠቁመው፤ ሆቴሎችም እንግዶችን ለመቀበል አስፈላጊውን ዝግጅት እያደረጉ መሆኑን አስረድተዋል።

እንደ ሚኒስትር ዴኤታዋ ገለጻ ፤ በዓሉን ለመታደም የሚመጡ እንግዶች ላሊበላና አካባቢውን እንዲጎበኙ ፓኬጆች ተዘጋጅተዋል። የሠላም ስምምነቱን ተከትሎ ኢትዮጵያ ያላትን የቱሪዝም መስህብ ለአገር ውስጥና ለውጭ ጎብኚዎች ለማስተዋወቅ እየተሰራ ይገኛል።

በተለያዩ አገሮች የሚኖሩ ኢትዮጵያውያንና የኢትዮጵያ ወዳጆች በተዘጋጀው መርሃ-ግብር ላይ እንዲሳተፉ ጥሪ መደረጉን መናገራቸውን ኢዜአ ዘግቧል።


በ2014 ዓ.ም "ታላቁ ጉዞ ወደ አገር ቤት" እንዲሁም "ከዒድ እስከ ዒድ ወደ ሀገር ቤት" በሚል የተዘጋጀውን ጥሪ ተቀብለው በመላው ዓለም የሚገኙ በርካታ ኢትዮጵያውያን፣ ትውልደ-ኢትዮጵያውያንና የኢትዮጵያ ወዳጆች ወደ ኢትዮጵያ መምጣታቸው ይታወሳል።

ይህንንም ተከትሎ ዳያስፖራዎቹ የገና እና ጥምቀት በዓላትን በአገራቸው ከማክበር ባሻገር በጦርነት የተጎዱ አካባቢዎችን ተዘዋውረው በመጎብኘት ለመልሶ ግንባታ የበኩላቸውን አስተዋጽኦ ማድረጋቸውም የሚታወስ ነው።

# ላሊበላ ለገና በዓል 1 ነጥብ 8 ሚሊዮን እንግዶችን ለመቀበል ተዘጋጅታለች

ልጅአለም ፍቅሬ

አዲስ አበባ፡- በመጪው የገና በዓል ከአንድ ነጥብ ስምንት ሚሊዮን በላይ እንግዶችን ለመቀበል ዝግጅት ማጠናቀቁን የላሊበላ ከተማ አስተዳደር ባህልና ቱሪዝም ጽህፈት ቤት አስታወቀ።



የላሊበላ ከተማ ምክትል ከንቲባና ባህል ቱሪዝም ጽህፈት ቤት ሃላፊ ዲያቆን አዲሴ ደምሴ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ በኮቪድ-19ኙና በሰሜኑ የሀገሪቱ ክፍሎች ተከስቶ በነበረው ጦርነት ላለፉት ሶስት ዓመታት በከተማዋ የነበረው የቱሪስቶች እንቅስቃሴ ተቀዛቅዞ ነበር። በእነዚህ ምክንያቶች ተቀዛቅዞ የቆየውን የቱሪዝም እንቅስቃሴ ወደ ነበረበት ለመመለስና የቱሪስት ፍሰቱን ይበልጥ ለመጨመር የላሊበላ ከተማ በመጪው የገና በዓል ከአንድ ነጥብ ሥምንት ሚሊዮን በላይ እንግዶችን ለመቀበል ዝግጅት ተደርጓል።

ምክትል ከንቲባው መጪው በዓል በደማቅ ሁኔታ ለማክበርና እንግዶችን ለመቀበል ስምንት ጊዜያዊ አብይ ኮሚቴዎች ተቋቁመው ወደ ስራ መግባታቸውን ጠቅሰዋል። ኮሚቴዎቹም ከሰላምና ጸጥታ ሁኔታ፣ በጽዳትና ውበት፣ ጊዜያዊ ገቢ አሰባሳቢና ልዩ ልዩ ኮሚቴዎችን ያካተተ ሲሆን፤ በየዘርፉ ካሉ ባለድርሻ አካላት ጋር እየሰሩ መሆኑን ገልጸው፤ በተለይ ሰላምና ጸጥታ ዘርፉ ከታህሳስ አንድ ቀን 2015ዓ.ም ጀምሮ ስምሪት ተሰጥቶት የከተማዋን ደህንነት እያስጠበቀ ይገኛል ብለዋል።

በዓሉን ለማክበር የሚመጡ ቱሪስቶች የሚያርፉበት እንዳያጡ 45 ሆቴሎችን በማነጋገር አገልግሎቶችን አሟልተው እንዲጠብቁ ዝግጅት ማድረጋቸውን አስታውቀዋል። በበዓሉ የሚታደሙ የውጭ ዜጎች ምንም አይነት የቋንቋ ችግር ሳይገጥማቸው የበዓሉ ሃይማኖታዊና ባህላዊ ትውፊት ተረድተው እንዲመለሱ ከአስጎብኚዎች ጋር በጋራ ለመስራት ዝግጅት ተጠናቋል ብለዋል።

በተጨማሪም እንግዶች ላይ ያልተገባ የዋጋ ጭማሪ እንዳያደርጉና ሕገ ወጥ ነጋዴዎችን ለመከላከል የንግዱ ማህበረሰብ አወያይተናል፤ ይህንንም የሚመራ ግብረ-ሃይል አቋቁመናል ሲሉ ገልጸዋል፡ ፡

በዓሉ ከሃይማኖታዊና ትውፊታዊ እሴቱ ባሻገር ለማህበራዊ መስተጋብር፣ ለቱሪዝም መነቃቃትና ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታ እንዳለው ያስታወሱት ዲያቆን አዲሱ ፤በመጪው በዓል ከአንድ ነጥብ ስምንት በላይ እንግዶች በመቀበል ከአገርና ከአገር ውጭ በሚመጡ ቱሪስቶች ከ141 ሚሊዮን ብር በላይ ገቢ ለማግኘት መታቀዱን ገልጸዋል።

የከተማው ኢኮኖሚ እንንቅስቃሴ ከቱሪዝም ወጪ ሌላ አማራጭ የለውም ያሉት ዲያቆን አዲሴ፤ ኮሮናና ጦርነቱ የከተማው ምጣኔ-ሀብት ሙሉ በሙሉ ተቀዛቅዞ ከዝቅተኛው እስከ ከፍተኛው የኑሮ ደረጃ የሚኖር ማህበረሰብ ለከፋ ችግር ዳርጎት እንደነበር አስታውሰዋል።

ካለፉት ሶስት ዓመታት በፊት ውቅር አብያተ-ክርስትያናቱን ለመጎብኘት የሚመጣው ቱሪስት 39 ሺ በላይ እንደነበር አስታውሰው፤ በዚህም ከውጭ ሀገር ቱሪስት ብቻ በዓመት ከ260 ሚሊዮን ብር በላይ ከቱሪዝም ዘርፉ ይገኝ ነበር ብለዋል።

አካባቢው ላይ በነበረው ጦርነት ከተማው ላይ ወደ 260 ሚሊዮን ብር የሚገመት ሀብት ወድሟል፤ የቱሪስት ፍሰቱም ከ39 ሺ ወደ 767 ዝቅ ብሎ እንደነበር ያስታወሱት ዲያቆን አዲሴ ፤ አሁን ሰላም በመሆኑና መሰረተ-ልማት ዳግም በመሟላቱ በመጪው የገና በዓል እስከ አንድ ነጥብ ሥምንት ሚሊዮን እንግዶችን ተቀብለን ከ141 ሚሊዮን ብር በላይ ከአገር ውስጥና ከውጭ ሀገር ቱሪስት ገቢ መሰብሰብ መታቀዱን ጠቁመዋል።

የደብረ ሮሐ ቅዱስ ላሊበላ ገዳም አስተዳዳሪ ቆሞስ አባ -ጽጌሥላሤ መዝገቡ በበኩላቸው መጪውን የገና በዓል በላቀ ሁኔታ ለማክበር ከመንፈሳዊ ዝግጅት በተጨማሪ ከውበትና ፅዳት፣ እንግዳ ማረፊያ ከማዘጋጀት አንጻር ከአካባቢው ማህበረሰብና ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ጋር በቅንጅት እየሰራን እንገኛለን ብለዋል።

የገና በዓል በድምቀት ከሚከበርባቸው ቦታዎች መካከል የደብረ ሮሐ ቅዱስ ላሊበላ ገዳም አንዱ ነው ያሉት ፤ ቆሞስ አባ ጽጌሥላሤ፤ በሆቴል ለማረፍ ገንዘብ መክፈል ለማይችሉ ከአካባቢው ማህበረሰብ በመወያየት አቅሙ ያላቸው ሰዎች ማረፊያ እንዲያዘጋጁና በቅጽረ- ቤተ ክርስቲያን ለሚያርፉ ደግሞ ቦታ እያመቻቸን እንገኛለን። በእለቱም የተደራጁ መንፈሳዊ ወጣቶች ስንቅ ለሌላቸው ስንቅ እንዲያቀብሉ የተቸገሩትን የሚረዱ አጠቃላይ በበጎ ፈቃድ የሚያስተባብሩ ወጣቶች መዘጋጀታቸውን ተናግረዋል።

የደብረ ሮሐ ቅዱስ ላሊበላ ገዳም አስተዳዳሪ ቆሞስ አባ ጽጌሥላሤ ከሃይማኖታዊ ይዘቱና ከቦታው ቅዱስነት በተጨማሪ ቀደምት አባቶቻችን የነበራቸው የሥነ-ሕንጻ ጥበብ፣ መልካም ባሕልና እሴት የሚያሳይ ትልቅ የታሪክ አሻራ ያለው በመሆኑ ሁሉም ኢትዮጵያውያን መጥተው በዓሉን እንዲያከብሩ ጥሪ አስተላልፈዋል።

# የገዳ ባንክ በይፋ ተመርቆ ሥራ ጀመረ

ቃልኪዳን አሳዬ

አዲስ አበባ፡- የገዳ ባንክ ከባለአክሲዮኖች በተሰበሰበ 552 ሚሊዮን የተከፈለ ካፒታል እና አንድ ነጥብ አንድ ቢሊዮን የተፈረመ ካፒታል ይዞ በይፋ ተመርቆ አገልግሎት መስጠት ጀመረ።



ፎቶ ገበቡ ገብሬ

የምረቃ ሥነሥርዓቱ ላይ የኦሮሚያ ክልል ርዕሰ መስተዳድር አቶ ሽመልስ አብዲሳ፣ የብሔራዊ ባንክ ገዥ ዶክተር ይናገር ደሴ፣ ከፍተኛ የመንግሥት ስራ ኃላፊዎች፣ አባገዳዎች እንዲሁም የኃይማኖት አባቶች በተገኙበት በትናንትናው እለት ተካሂዷል።

የባንኩ ዋና ሥራ አሥኪያጅ አቶ ወልዴ ቡልቱ በምረቃ ሥነሥርዓቱ ላይ እንዳሉት የገዳ ባንክ ከ28ሺ በላይ የአክሲዮን ባለድርሻዎችን ገንዘብ በማሰባሰብ በተለይም በገጠሩ ክፍል ያለውን የባንክ ተደራሽነት ክፍተት ለመሙላት ቀዳሚ ዓላማው አድርጎ ወደ ገበያው ተቀላቅሏል።

ባንኩ ለገጠሩ ማህበረሰብ የፋይናንስ አገልግሎትን ተደራሽ በማድረግ ላይ እንደሚያተኩር ጠቁመው፤ የቁጠባ ባህልን በማሳደግ፣ ተገቢውን የብድር አገልግሎት በማቅረብ የሚታየውን ክፍተት ወደ ዕድል ለመቀየር ይሰራል ብለዋል።

የብሔራዊ ባንክ ገዢ ዶክተር ይናገር ደሴ በበኩላቸው እንዳሉት ፤ አሁን ባለው ነባራዊ ሁኔታ የውጭ ሀገር ባንኮች በቅርብ ጊዜ ውስጥ የኢትዮጵያን የባንክ እንዱስትሪ ይቀላቀላሉ ተብሎ ይጠበቃል። ከዚህ አኳያ ከአገር ውስጥም ሆነ ከውጭ ባንኮች በሚኖረው ውድድር ገዳ ባንክ ተወዳዳሪ ሆኖ ለመዝለቅ፤ የባንኩ ባለአክሲዮኖች፣ የማኔጅመንት አባላት እንዲሁም የባንኩ ደንበኞች እና ሰራተኞች ከፍተኛ ጥረት ማድረግ ይኖርባቸዋል።

በአሁኑ ጊዜ በአገሪቱ ነባርና አዳዲስ ባንኮች ለኢኮኖሚው ከፍተኛ ድጋፍ እያደረጉ እንደሆነ ገልጸው፤ ከባንኮች የሚሰጥ ብድር ምንጩ ከቁጠባ የሚገኝ ገንዘብ በመሆኑ ባንኮች ቁጠባን መሠረታዊ ስራቸው አድርገው መውሰድ አለባቸው፤ በዚህ ረገድ ገዳ ባንክም ትልቅ ደረጃ ለመድረስ በቁጠባ ላይ ርብርብ ሊያደርግ እንደሚገባ ተናግረዋል።

በአሁኑ ጊዜ የባንኮች ስራ ከተማ ላይ ያዘነበለ በመሆኑ የፋይናንስ ተደራሽነት በገጠሩ ክፍል ገና ብዙ የሚቀረው መሆኑን አመልክተው፤ ባንኩ በገጠሩ ክፍል በትኩረት መስራት እንደሚኖርበትም ተናግረዋል።

በተለይ የገጠር የሚኖረውን ህብረተሰብ ክፍል በኢኮኖሚ ለመደገፍ ከአነስተኛ ብድር ጀምሮ እስከ መካከለኛና ከፍተኛ የብድር አቅርቦት ድረስ በማመቻቸት ረገድ ትኩረት ሰጥቶ እንዲሰራ ማድረግ አስፈላጊ መሆኑን የብሄራዊ ባንክ ገዢው ጠቁመዋል።

የኦሮሚያ ክልል ርዕሰ መስተዳድር አቶ ሽመልስ አብዲሳ እንደተናገሩት የገዳ ባንክ ከስሙ ጋር የተጣጣመ እና የሀገሪቱን ኢኮኖሚ በመደገፍ ረገድ ድርብ ኃላፊነት እንዳለበት እና ባንኩ ስሙን የሚመጥን ስራ መሥራት እንደሚኖርበት ተናግረዋል።

የማስጀመሪያ መርሃ ግብሩ ባንኩ በአዲስ አበባ ጎተራ አካባቢ ባስገነባው ሕንጻ ያካሄደ ሲሆን ባንኩ በሰላሳ ቅርንጫፎች አገልግሎት ለመስጠት ዝግጅቶች ማጠናቀቁን ታውቋል። የዓለም አቀፍ ደረጃን በጠበቀ መልኩ የባንክ አገልግሎት ስራውን ለማሳለጥም ከተለያዩ ዓለም አቀፍ ባንኮች ጋር ግንኙነት መፍጠሩ ተገልጿል ።

# ርዕሰ አንቀፅ

## የክትባት ዘመቻው ጤናማ ትውልድ ለመፍጠር ትልቅ አቅም ነው!

ልጆችን ከባድ ከሆነ በሽታ ለመከላከልና ከሞት ለመታደግ ክትባት ቀላሉ እና ደህንነቱ የተጠበቀ ዘዴ መሆኑን ሁሉም ሰው መረዳት ይኖርበታል። ሁሉም ክትባቶች ለልጆች እንደ የእድሜያቸው በነፃ የሚሰጥ ሲሆን ልጆች ጤናማ ሆነው እንዲያድጉ በሽታን አስቀድሞ የመከላከያ አቅማቸውን እንዲያዳብሩ ወሳኙ ዘዴ ነው። በመሆኑም ወላጆች ይህንን በመረዳት ልጆችን ማስከተብ አገርንም ወገንንም ማገዝ መሆኑን ማወቅ ይኖርባቸዋል።

ለዓለምም ሆነ ለኢትዮጵያ ትልቅ ስጋት የሆነው የኩፍኝ በሽታ በአሁኑ ወቅት በአንዳንድ ክልሎች በወረርሽኝ ደረጃ ተከስቷል። በተለይም በአማራ፣ ኦሮሚያ፣ አፋር፣ ደቡብ ብሄር ብሄረሰቦችና ሕዝቦች ክልሎች እንዲሁም በአዲስ አበባም በተለያዩ ክፍለ ከተሞች በወረርሽኝ መልክ በመታየት ላይ መሆኑን መረጃዎች ያመለክታሉ።

የኩፍኝ በሽታ መከላከያ ክትባት በወቅቱ ካልተወሠደ በሽታው በፍጥነት ከልጅ ወደ ልጅ የሚዛመትና እስከ ሞት የሚደርስ ጉዳት የሚያስከትል በመሆኑ በአገር አቀፍ ደረጃ ከፍተኛ ትኩረት ተሰጥቶት ክትባቱ በዘመቻ መልክ በመሰጠት ላይ ይገኛል ። በመሆኑም ሁሉም ኅብረተሰብ የችግሩን አሳሳቢነት በመረዳት እና የክትባቱን አስፈላጊነት በመገንዘብ ሕጻናቱን ማስከተብ አለበት።

አገራችንም እንደ ፖሊዮና ኩፍኝ እንዲሁም ሌሎቹን በሽታዎች ሙሉ በሙሉ ለማጥፋት ከመደበኛው የክትባት ፕሮግራም በተጨማሪ የተለያዩ ዘመቻዎችን በማድረግ ብዙ ርቀቶችን ተጉዛለች። አሁንም ይሄንኑ የክትባት ፕሮግራም ከመደበኛ ፕሮግራም በተጨማሪ በዘመቻ መልክ እየሰጠች ትገኛለች። ክትባታቸውን ሙሉ በሙሉ ያጠናቀቁ ሕጻናት ከተለያዩ የበሽታ አይነቶች የተጠበቁ፤ የመከላከል ብቃታቸውም የዳበረ ሲሆን ያልተከተቡት ደግሞ በከፍተኛ ደረጃ ለከባድ ህመም ተጋላጭ በትንሽ በትልቁ ችግር ውስጥ የሚወድቁም ስለመሆናቸው ጥናቶች አረጋግጠዋል።

ኩፍኝ በሀገራችን ብቻ ሳይሆን በመላው ዓለም ያልጠፋ ከመሆኑም በላይ እስከ አሁንም በዓለም ላይ 140 ሺ የኩፍኝ ኬዞች አሉ። በአገራችንም ከአምስት ዓመት በታች ያሉ አንድ ነጥብ አንድ ሚሊዮን ሕጻናት ኩፍኝን ጨምሮ ከተወለዱ ጊዜ ጀምሮ ምንም ዓይነት ክትባት ያላገኙ ስለመሆናቸው ከጤና ሚኒስቴር የተገኘው መረጃ ያመለክታል።

ይሁን እንጂ እስካሁንም በተለያዩ ምክንያቶች በክትባት ልንከላከላቸው የምንችላቸውን በሽታዎች የሕጻናት የጤና ችግር ሆነው ቀጥለዋል። ለሕጻናት ሞትም ምክንያት ሆነዋል።

የበሽታው ስርጭትና የመግደል መጠን ከዓመት ዓመት ከመጥፋት ይልቅ የተለያዩ መጠኖችን እያስመዘገበ መምጣቱ አሳሳቢ ሆኗል። በዚህም እ.ኤ.አ በ 2015 ላይ 197 የነበረው የሞት መጠን እ.ኤ.አ በ 2016 ወደ 50 ዝቅ ብሎ ነበር፤ እኤአ በ 2021 ደግሞ 18 ሕጻናት ሕይወታቸውን አጥተዋል። ብዙ ጊዜም ዘመቻዎች የሚደረጉት የበሽታውን ስርጭት ለመግታት ፣ የከፋ ሞትና ህመም እንዳይመጣ ለማስቻል ነው፤ አሁንም በተለያዩ የአገሪቱ አካባቢዎች የኩፍኝ ወረርሽኝ በመኖሩ ምክንያት የዘንድሮው ዘመቻ አስፈላጊ ሆኗል።

በመሆኑም ይሄንን አሳሳቢ የጤና ችግር ሙሉ ለሙሉ ከአገራችን ለማጥፋት ከመደበኛ የክትባት ፕሮግራም በተጨማሪ በዘመቻ መልክ ክትባት ለሕጻናት እንዲዳረስ ጤናው የተጠበቀ ትውልድ ለማፍራት በመላው ሀገሪቱ ከፍተኛ ስራ እየተሰራ ይገኛል።

በያዝነው ዓመትም ከታህሳስ 13 እስከ 22 ቀን 2015 ዓ .ም ድረስ በመላው አገሪቱ በሚካሄደው የተቀናጀ የኩፍኝ መከላከያ ክትባት እድሜያቸው ከአምስት ዓመት በታች ለሆኑ ሕጻናት እንዲሁም እድሜያቸው ከ18 ዓመት በላይ ለሆኑ ወጣቶች ደግሞ የኮሮና ቫይረስ መከላከያ ክትባት በመሰጠት ላይ ነው። በመሆኑም ኅብረተሰቡ ለተጀመረው የተቀናጀ የኩፍኝ በሽታ መከላከያ ክትባት ዘመቻ ውጤታማነት ክትባቱን ያላገኙ ሕጻናት በሙሉ ክትባት እንዲያገኙ በማድረግ የድርሻውን መወጣት አለበት ።

ይሄ የክትባት ዘመቻ ውጤታማና የነገው አገር ተረካቢ ትውልድ ጤንነቱ የተጠበቀ እንዲሆን በተለይም የሃይማኖት አባቶች ፣ መገናኛ ብዙሃን ፣ እንዲሁም ጉዳዩ የሚመለከታቸው አካላት የኩፍኝ በሽታ መከላከያ ክትባት አለመውሰድ የሚያመጣውን ችግር በማስገንዘብ ልጆች የክትባቱ ተጠቃሚ እንዲሆኑ ማስተማርና ማንቃት ይገባቸዋል። የክትባት ዘመቻው ጤናማ ትውልድ ለመፍጠር ትልቅ አቅም መሆኑን ደግሞ ደጋግሞ ማስረዳትም ይጠበቃል።

ክትባቱ እስከ ታህሳስ 22 ድረስ የሚቆይ በመሆኑ ሕጻናቱን በአቅራቢያቸው በሚገኙ የጤና ተቋሟት በመውሰድ የክትባቱ ተጠቃሚ እንዲሆኑ ማድረግ ይገባል። በአጠቃላይ ለዘመቻው ውጤታማነት፣ ሁሉም የድርሻውን መወጣት አለበት ።


# አዲስ ዘመን

ግንቦት 30 ቀን 1933 ዓ.ም ተቋቋመ

**የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ዋና ስራ አስኪያጅ**

ስልክ ቁጥር - 011-126-42-22

**ዋና አዘጋጅ**

አንተነህ ኃ/ብርሃን ወ/መድህን

**አድራሻ**

ንፋስ ስልክ ላፍቶ ክ/ከ

ወረዳ 06

የቤት ቁጥር 319

ኢሜይል - anteneh.hailebirhan@press.et

ስልክ ቁጥር - 011-1-26-42-40

**የአዲስ ዘመን ማኔጂንግ ኤዲተር**

ወንድወሰን ሽመልስ ታደሰ

ስልክ፡- 011 126 4240

Email:- wendweson.shimelis@press.et

wendwesonshimelis@gmail.com

**የአዲስ ዘመን ምክትል ዋና አዘጋጆች**

- ወርቁ ማሩ
- ኃይሉ ሣህለድንግል
- አልማዝ አያሌው
- እስማኤል አረቦ

**የገበያ ልማትና ፕሮሞሽን ዘርፍ**

ኢሜይል - etpresspromotion@gmail.com

ስልክ - 011-126-43-41

ፋክስ - 011-811-13-15

**የማስታወቂያ መቀበያ ክፍል**

ስልክ ቁጥር - 011-156-98-73

ፋክስ - 011-126-58-12

**የማስታወቂያ ሽያጭ ማስተባበሪያ**

ስልክ - 011-1-26-43-39

**ማከፋፈያ**

ስልክ ቁጥር - 011-157-02-70


ነፃ ሃሳብ

**ይህ አምድ በተለያዩ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጉዳዮች ዙሪያ ዜጎች ነፃ ሀሳባቸውን የሚሰጡበት ነው፡፡ በዓምዱ ላይ የሚወጡ ጽሁፎች የዝግጅት ክፍሉን አቋም አያመለክቱም፡፡**

## ሚዛን ቀሻቢዎቹ

በንግድ ሥርዓት ውስጥ ሻጭና ገዢ ዋጋ ቆርጠው ግብይት እንዲፈጽሙ ከሚያስችሏቸው መለኪያዎች አንዱ ሚዛን ነው። ከሚሊ ግራም እስከ ኪሎ ግራም ያሉ መለኪያዎችን እንደ አስፈላጊነቱ እየተጠቀምን የምንገበያየው ሚዛን በሻጭና በገዢ መካከል የቃል ኪዳን ማሰሪያ ውል በመሆኑ ነው።

አንድ ኪሎ ስጋ፣ ግማሽ ኪሎ ሽንኩርት፣ አንድ ኪሎ ሙዝ ወዘተ እንደየ ወቅቱ የገበያ ሁኔታ ተመን የሚወጣላቸው ቢሆንም መለኪያቸው ግን ሚዛን በመሆኑ ሸማቹ ባስመዘነው መጠን ልክ ሂሳብ እንዲከፍል ሻጩም በተጠየቀው ልክ መዝኖ እንዲያስረክብ ስምምነቱ ያስገድዳቸዋል።

ባለንበት ዘመን በውስጣዊም ይሁን ውጫዊ ምክንያቶች መሸቶ በነጋ ቁጥር በሸቀጦችና በምግብ ፍጆታዎች ላይ የዋጋ ጭማሪን መስማት የተለመደ ጉዳይ ነው። ከዚህ የሚከፋው ደግሞ ሚዛን የሚቀሽቡ ነጋዴዎች የመበራከታቸው እውነታ ሲሆን ፤ ችግሩም ለሸማቹ ማህበረሰብ ላይ ‹‹በእንቅርት ላይ ጆሮ ደግፍ›› ከሆነ ውሎ አድሯል።

በተለይም ከዕለት ተዕለት ኑሯችን ጋር በተገናኘ በምንሸምታቸው የምግብ ፍጆታዎች ላይ የሚደረገውን የሚዛን ቅሸባ የመንደራችን አትክልት ቤቶች፣ ዳቦ ቤቶችና ሥጋ ቤቶች የማይደብቁት እውነታ ነው።

ሌብነት መልኩ ብዙ ነው፤ ደረጃውና በሕብረተሰቡ ላይ የሚያሳድረው ተጽዕኖም ይለያያል። ለምሳሌ የመንግሥትን መሬት በመሸጥና ጨረታን በማጭበርበር የሚፈጸም ሌብነት የሀገርን ኢኮኖሚ ከማቀርቀዝ አንጻር ጉዳቱ ከፍተኛ እንደሚሆን አያጠራጥርም። እንዲህ አይነቱ ሌብነት ጉዳቱ የሚታየው በሂደት ስለሆነ በሕብረተሰቡ ላይ የሚያሳድረውን ተጽእኖ ከመቅጽበት ልናየው አንችልም።

ይህ ሲባል ጊዜያዊ ችግር አያስከትልምና ችላ እንበለው ለማለት አይደለም። በየቢሮው ተሰግስገው የሚዘርፉ ሌቦችን መንግሥት በጀመረው መንገድ እያደነ ለፍርድ በማቅረብ ከሌብነት የጸዳ አሠራርን ማስፈን እንዳለበት እናምናለን።

ከዚህም በተጨማሪ በዕለት ተዕለት ኑሯችን ላይ ፈታና የሆኑና በልቶ የማደርና ያለማደራችንን ጉዳይ እየወሰኑ ያሉ ሌብነቶችም ተመሳሳይ ትኩረት ሊሰጣቸው ይገባል።

በመንግሥት ተቋማት አካባቢ የተጀመረው ሌባን የማጽዳት ዘመቻ በቢሮ ደረጃ ብቻ ተወስኖ መቅረት የለበትም። ይልቁንም ከጉሮሮ ላይ ወደሚናጠቁ ሚዛን ቀሻቢዎች ፊቱን አዞሮ ለሕብረተሰቡ የእለት ተእለት ጥያቄ አፋጣኝ መልስ መስጠት እንዳለበት ይሰማኛል።

አብዛኛው የማህበረሰብ ክፍል ዕለት ተዕለት ከሚጠቀማቸው የምግብ ፍጆታዎች መካከል ዳቦ የመጀመሪያው ነው። ዳቦ በተለይም ኑሯቸው ከእጅ ወደ አፍ የሆነ ሰዎች በቀላሉ ገዝተው የሚጠቀሙት የቀን ደራሽ ምግብ ነው። የቀን ሥራ እየሠሩ በሚያገኙት ገንዘብ በየቀኑ ዳቦ እየሸመቱ ልጆቻቸውን የሚያሳድጉ ወላጆችም በርካቶች ናቸው።

በእርግጥ መንግሥት የዳቦ ገበያውን ለማረጋጋት ቀደም ሲል ከውጭ በሚያስገባው ስንዴ ላይ ድጎማ ከማድረግ ጀምሮ በአዲስ አበባ ከተማ የሸገር ዳቦ ፋብሪካን በመገንባት ለከተማዋ ነዋሪዎች የዳቦ አቅርቦትን በስፋት ተደራሽ ለማድረግ የቻለውን ሁሉ አድርጓል። አሁንም የማስፋፊያ ሥራዎችን እየሠራ ይገኛል።

ሸገር ዳቦ ከሚሸጥበት ተመጣጣኝ ዋጋ አንጻር ሕብረተሰቡን እየደጎመ መሆኑ ባይካድም የአዲስ አበባ ከተማ ነዋሪዎችን የዳቦ ፍላጎት መልሷል ማለት ግን አይቻልም። በዚህ የተነሳ ዛሬም ድረስ አብዛኛው ሕዝብ ከዳቦ ቤቶች እየሸመተ የሚያድር በመሆኑ ግራም እየቀሸቡ ለሚሸጡ ነጋዴዎች ተጋላጭ ሆኗል።

የሀገሪቱ የደረጃ መስፈርት የአንድ ዳቦ አነስተኛ ክብደት 100 ግራም እንዲሆን የሚያስገድድ ቢሆንም ነጋዴዎች ግራሙን በመቀሸብ አንድ ዳቦ መሆን የሚገባውን ሁለት ዳቦ እያደረጉና ዋጋ እየቆለሉ ሕብረተሰቡን ለከፍተኛ ወጪ እየዳረጉት መሆኑ የሁላችንም ትዝብት ነው።

ኢትዮጵያ ስንዴን አምርታ ኤክስፖርት ለማድረግ በተዘጋጀችበት በዚህ ወቅት ዳቦ ዋጋው ተቆልሎ ፤ ግራሙ አሽቆልቁሎ መመልከት የሚያሳፍር ነው። ዳቦ ተገቢውን ግራም አሟልቶ ለገበያ እንዲቀርብ የሚመለከተው ባለድርሻ አካል ቁጥጥር ማድረግ ይኖርበታል።

የቀድሞው ንግድና ኢንዱስትሪ ሚኒስቴር በአንድ ወቅት በሚዛን ላይ የሚደረግ እንዲህ አይነት ማጭበርበርን ለመቆጣጠር ዲጂታል ሚዛኖች ጥቅም ላይ እንዲውሉ ይደረጋል ማለቱ ይታወሳል። ነገር ግን እስከ ዛሬ ድረስ ተግባራዊ ባለመደረጉ እና ቁጥጥሩ አናሳ በመሆኑ የዳቦ ነጋዴዎች ከደሃው ጉሮሮ እየነጠቁ የማይገባቸውን ጥቅም እያግበሰበሱ ይገኛሉ።

የዳቦን ግራም እየቀነሱ የሚሸጡ ነጋዴዎች በኑሮ ውድነቱ ላይ ብቻ ሳይሆን በማህበረሰቡ ሥነ ልቦና ላይ የሚፈጥሩት ጫና ቀላል ግምት የሚሰጠው አይደለም። ሰዎች ያለፈውን ዘመን ካሉበት ዘመን ጋር እያነጻጸሩ በዚህ ዘመን መኖራቸውን እንደበረከት ሳይሆን እንደ እርግማን እንዲመለከቱት የሚያደርግ እና የመኖር ተስፋንም የሚያጨልም ነው።

ዛሬ ገበያ ላይ ቀርቦ የምናየው ዳቦ የመጠኑ ማነስ ብቻ ሳይሆን የጥራት ችግርም ያለበት ነው። ገና ከተቀመጠበት አንስተን ልንቆርሰው ስንሞክር ልብሳችን ላይ ተፈርፍሮ የሚቀረውን ቤቱ ይቁጠረው።

የዳቦን ጉዳይ ‹‹የሆድ ነገር ሆድ ይቆርጣል›› በሚለው ብሂል ብቻ መለካት የለብንም። ጉዳዩ ሀይ ባይ ካላገኘ ግላዊና ማህበራዊ ቀውስ ከመፍጠር አልፎ ፖለቲካዊና ኢኮኖሚያዊ ችግር ወደ መሆን መሸጋገሩ አይቀርም። ለነገሩ በዳቦ ላይ አተኮርኩኝ እንጂ በአትክልትና ፍራፍሬ ፣ በሥጋ ፣ በነዳጅ ወዘተ ያለው ቅሸባ ስር የሰደደና ተመሳሳይ አንድምታ ያለው ነው።

ባለፈው የኢህአዴግ መንግሥት ሌብነት እንደ አንድ የሥራ መስክ እውቅና ከተሰጠው ወዲህ ሁሉም በተሰማራበት ሥራ በአቋራጭ መክበርን እንደ ጥሩ ስልት በመያዙ ነባሩ በታማኝነት የማገልገልና እና የጨዋነት እሴታችን ፈተና ላይ ወድቆ መክረሙ የሚታወስ ነው።

አሁን ከሌብነት የጸዳ ሥርዓትን ለመፍጠር የተጀመረው ንቅናቄ በመንግሥት ተቋማት ብቻ ተወስኖ ሳይቀር ፊቱን ወደ ሚዛን ቀሻቢዎችም በፍጥነት ማዞር ቢችል ብዙኋኑን በተለይም ዝቅተኛውን የህብረተሰብ ክፍል ከስግብግብ ነጋዴዎች መታደግ ይቻላል።

# የከተማ አስተዳደሩ የገዛቸው 100 አውቶብሶች በቅርቡ ወደ አገር ይገባሉ

**ማርቆስ በላይ**

አዲስ አበባ፡-የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ግዢ ለመፈጸም በዕቅድ ከያዛቸው 200 የከተማ አውቶብሶች መካከል 100ዎቹ የግዥ ሂደታቸው ተጠናቆ በቅርቡ ወደ አገር እንደሚገቡ ሸገር የብዙሃን ትራንስፖርት አገልግሎት ድርጅት አስታወቀ።

በሸገር የብዙሃን ትራንስፖርት አገልግሎት ድርጅት ምክትል ዋና ሥራ አስኪያጅ አቶ አዳነ አብደታ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ የሸገር የብዙሃን ትራንስፖርት አገልግሎት ድርጅት ለከተማዋ ነዋሪዎች የተቀላጠፈ የብዙሃን ትራንስፖርት አገልግሎት ለመስጠት እየሰራ ይገኛል። ይህን አገልግሎቱን ይበልጥ ለማቀላጠፍና ተደራሽ ለማድረግም የከተማ አስተዳደሩ ግዢ ለመፈጸም በዕቅድ ከያዛቸው 200 የከተማ አውቶብሶች መካከል በመጀመሪያው ዙር 100ዎቹ የግዥ ሂደታቸው ተጠናቆ በቅርቡ ወደ አገር ይገባሉ።

አስተዳደሩ የገዛቸው አውቶብሶች ዘመናዊ መሆናቸው ገልጸው፤ የአካል ጉዳተኞች መግቢያና የዊልቸር ማስቀመጫን ጨምሮ፣ ለሕጻናትና ለአዛውንቶች አገልግሎት የሚውሉ የተለዩ ስድስት ወንበር ያላቸው መሆናቸውን ገልጸው፣ አውቶብሶቹ በመንገድ ላይ ችግር



ቢያጋጥማቸው ከፍ ብሎ ማለፍና ዝቅ ብለው ተሳፋሪን መጫን የሚችሉ መሆናቸውን ጠቁመዋል።

ለአውቶብሶች ስምሪት መስጠትና መቆጣጠር የሚያስችል ዘመናዊ ቴክኖሎጂ የተገጠመላቸው በመሆናቸውም ከሸገር አውቶብሶች ጋር ተመሳሳይ እንደሚያደርጋቸው አመልክተዋል።

እንደ አቶ አዳነ ገለጻ፤ የመጀመሪያው ዙር የ100 አውቶብሶች ግዥ በመጠናቀቁ ቻይና ከተመረቱበት ፋብሪካ ከአንድ ሳምንት በኋላ ወደ ወደብ ይጫናሉ። በአንድ ወር ጊዜ ውስጥም ጂቡቲ ወደብ ይደርሳሉ። በዚህ መነሻነትም በጂቡቲ ወደብ የጉምሩክ ርክክቡን ቀደም ብሎ በማጠናቀቅ አውቶብሶቹ በአጭር ጊዜ ውስጥ ወደ አዲስ አበባ እንዲመጡ ይደረጋል።

በሁለተኛ ዙር ከሚመጡ ቀሪዎቹ 100 አውቶብሶች ውስጥ የ50ዎቹ ተመርተው መጠናቀቃቸውን ጠቁመው፤ ቀሪዎቹም በምርት ሂደት ላይ ናቸው ብለዋል። እነዚህም በቅርቡም የመገጣጠም ሥራው ሙሉ በሙሉ ሲጠናቀቅ ወደ አገር ውስጥ የሚገቡ መሆኑን ገልጸዋል።

በመዲናዋ የአውቶብስ ተጠቃሚ ቁጥር ከጊዜ ወደ ጊዜ እየጨመረ መምጣቱን የገለጹት ምክትል ዋና ሥራ አስኪያጁ፤ የ200 አውቶብሶች ግዥም በከተማው የሚታየውን የትራንስፖርት ችግር ለመቅረፍ ከፍተኛ አስተዋጽኦ እንደሚኖራቸው ተናግረዋል።

ለከተማ አስተዳደሩ ከዚህ በፊት አውቶብሶችን የሚያቀርበው የኢትዮጵያ ኢንጂነሪንግ የቢሾፍቱ አውቶሞቲቭ ማምረቻ ኢንዱስትሪ መሆኑን ምክትል ዋና ሥራ አስኪያጁ አውስተው፤ አሁን ካለው የትራንስፖርት ፍላጎትና ችግር አንጻር በቶሎ ወደ አገልግሎት ለማስገባት ሲባል ከውጭ በቀጥታ እንዲመጡ መደረጉን አስረድተዋል።

በከተማዋ ለሕዝብ የትራንስፖርት አገልግሎት እየሰጡ የሚገኙ ከአንድ ሺህ የማይበልጡ የሸገርና አንበሳ አውቶብሶች ያሉ ሲሆን ከእነዚህ በተጨማሪ 200 አውቶብሶች መምጣታቸው ጥቅሙ ትልቅ መሆኑን አንስተዋል።

## ኢትዮጵያን እግር ከወርች...

ከ1ኛው ገጽ የዞረ

ሚኒስትሩ፣ ይሁን እንጂ ይህንን ለማደናቀፍ የውስጥና የውጭ ሃይሎች ተቀናጅተው ሲሰሩ መቆየታቸውን ጠቁመዋል።

ሙስናን ለመከላከል የተጀመሩ ስራዎች ከዳር እንዳይደርሱ የውስጥና የውጭ ጠላቶች በየደረጃው እንቅፋት ሲፈጥሩ መቆየታቸውን ጠቁመው፤ እነዚህን ችግሮች ለመከላከል በተለይ የምርመራ ጋዜጠኝነት ወሳኝ መሆኑን ተናግረዋል።

ሙስናን የመታገል ስራዎች ግን በሁለት ዋና ዋና ጉዳዮች እንቅፋት ይገጠማቸዋል ያሉት ሚኒስትሩ፤ አንደኛው በክህሎት ማነስ፣ ሙስናን መከላከል የሚያስችል የአሰራር ሥርዓት ያለመዘረጋት እና በሎጂስቲክስ አቅም ምክንያት የሚፈለገው ውጤት ማምጣት አደጋች መሆኑን ጠቅሰዋል።

እንደ ሚኒስትሩ ገለጻ፤ የጸረ ሙስና ትግሉ በፖለቲካ ተጽዕኖ፣ በአክራሪነትና በጽንፈኝነትና በብልሹ አሰራር ምክንያት የተፈለገው ውጤት ሳይመጣ ቆይቷል። እነዚህ ተጽዕኖዎችን ለመዋጋት በርካታ ስራዎች ቢሰሩም በተለያዩ ምክንያቶች ከዳር ሳይደርሱ ቀርተዋል።

ኢትዮጵያን እግር ከወርች ከያዛት ችግሮች ውስጥ አንዱ ሙስና መሆኑን የጠቆሙት ዶክተር ለገሰ፣ ከዚህ አንጻር ሥልጠናው እንደመነሻ ጠቃሚ መሆኑን ጠቁመዋል።

በአሁኑ ወቅት የሰላም ማስከበሩ ስራ በጥሩ ሁኔታ እየሄደ ቢሆንም በአንጻሩ በመልካም አስተዳደር እንዳይሰፍን ለማድረግ ሙስና ትልቅ እንቅፋት መሆኑን ተናግረዋል።

በመድረኩ ላይ የመነሻ ጽሁፍ ያቀረቡት የመንግሥት ግዢና ንብረት ባለሥልጣን ዋና ዳይሬክተር አቶ ሃጂ ኢብሳ እንደገለጹት፣ በአገራችን ከሚመደበው በጀት ውስጥ 70 ከመቶ የሚሆነው ለግዢ የሚወጣ ነው። ይህንን ሀብት ከሙስና በጸዳ መልኩ ማንቀሳቀስ ካልተቻለ እንደአገር የሚደርሰው ኪሳራ የከፋ ይሆናል።

ከዚህ መነሻነትም በዘርፉ ሙስናን ለመከላከል ዘርፈ ብዙ ጥረቶች እየተደረጉ መሆኑን የጠቆሙት አቶ ሃጂ፣ ከእነዚህም መካከል አንዱ የመንግሥት የኤሌክትሮኒክስ ግዢ ተጠቃሽ ነው ብለዋል።፡

የመንግሥት የኤሌክትሮኒክስ ግዥ ከሙስና መከላከያ መንገዶች አንዱ መሆኑን አቶ ሃጂ ጠቁመው፣ በአሁኑ ወቅትም 72 የፌዴራል ተቀማት በዚህ ሥርዓት ግዢ ለመፈጸም ወደዚህ አሰራር ገብተዋል ብለዋል።

ይህ ሥርዓት ዘርፈብዙ ጠቀሜታዎች አለው ያሉት አቶ ሃጂ ለምርመራ ዘገባውም መረጃን በቀላሉ ተደራሽ እንዲሆን በማድረግ ግልጽነትን ለመፍጠር ትልቅ አቅም እንደሚሆን ጠቁመዋል።

እስከ መጪው የካቲት ወር 2015ዓ.ም ድረስም ሁሉም የፌዴራል ተቋማት በዚህ ሂደት ውስጥ የሚያልፉበት አሰራር እንደሚፈጠር እና በቀጣዩ ዓመት የክልልና የከተማ አስተዳደሮችም ወደዚህ ሥርዓት እንዲገቡ እንደሚደረግ ተናግረዋል።

በአገራችን በሕግ በተደነገገው መሰረት እያንዳንዱ ተቋም የግዥ እቅድ እስከ ሃምሌ 30 ድረስ ማቅረብ ቢኖርበትም እስከ አለፈው መስከረም 30 ድረስ 60 ተቋማት አለማቅረባቸውን የጠቆሙት አቶ ሃጂ፣ ያለእቅድ የሚደረግ ግዢ ለሙስናና ብልሹ አሰራር በር የሚከፍት መሆኑን ተናግረዋል።

የኤሌክትሮኒክስ አሰራር እቅድ ያላቀረቡትን ስለማያስተናግድ ሙስናን ለመከላከል ትልቅ አቅም እንደሚሆን ጠቁመው፤ የኤሌክትሮኒክስ የግዢ ሥርዓት ከ20 እስከ 25 ከመቶ ሙስናን ለመከላከል እንደሚያስችልም አቶ ሃጂ አመልክተዋል።

የፍትህ ሚኒስትር ዴኤታው አቶ ፍቃዱ ጸጋ በበኩላቸው በአገራችን የመልካም አስተዳደር ችግር ከሪፎርም በፊትም የነበረና አሁንም እንደአገር መሻገር ያልቻልነው ትልቅ የልማት እና የእድገት ጠንቅ መሆኑን ጠቁመዋል።

ከለውጡ ወዲህ መንግሥት እድገትን ለማስመዝገብ በተለይ በሙስና ላይ ሰፊ ስራ ለመስራት ቢወጥንም ከቅርብም ሆነ ከሩቅ ይህንን ኃላፊነተ በአግባቡ እንዳይወጣ ማሰናከያዎች ሲደረጉ ነበሩ ብለዋል።

በተጨማሪ የኮቪድ 19 እና የሰሜኑ ጦርነት ተጨምሮ በሙስና ላይ በሚገባው ልክ ሳይሰራ መቆየቱን የተናገሩት አቶ ፍቃዱ፤ ብዙ ተስፋ የተደገረገበት የጸረ ሙስና ትግል መንግሥት ቃል በገባው ልክ ሳይፈጸም መቆየቱን ተናግረዋል። ያም ሆኖ ግን ፀረ ሙስና ትግሉ አለመቆሙን ጠቁመዋል።

በቅርቡም መንግሥት ሰባት አባላት ያሉት ኮሚቴ በማዋቀር ወደ ስራ መግባቱን አቶ ፍቃዱ አውስተው፣ ይህ ኮሚቴ ትኩረት የሚያደርግባቸው ዋና ዋና ዘርፎች ተለይተዋል ብለዋል። በዚህም መሰረት መሬት፣ ፍትህና ጸጥታ ዘርፍ፣ ገቢ፣ ፋይናንስ ጉዳዮች እና አገልግሎት አሰጣጥ ከተለዩ ዋና ዋና ዘርፎች ግንባር ቀደም መሆናቸውን ተናግረዋል።

ያም ሆኖ ግን ሙስና ዘርፈ ብዙና ውስብስብ በመሆኑ በኮሚቴና በመንግሥት ብቻ የሚሰራ ባለመሆኑ ሚዲያውና መላው ህብረተሰብ ማገዝ እንደሚኖርበት ጥሪ አቅርበዋል። በውይይቱም ከተሳታፊዎች ጥያቄዎችና አስተያየቶች የቀረቡ ሲሆን ከመድረኩም ምላሽ ተሰጥቶባቸዋል።

## “ሕገ-ወጥ የሰዎች ዝውውር...

ከ1ኛው ገጽ የዞረ

ወጣቶች ለሕገ-ወጥ የሰዎች ዝውውር የተዳረጉ አካባቢዎች መሆናቸውን ገልጸዋል።

"የስኬት መንገድን የለውጥ ጉዞን ከጫማችን ስር እንፈልገው" ያሉት አቶ ደመቀ፣ መንግሥት በሕገ-ወጥ መንገድ የተሰደዱ ዜጎችና አስከሬን በመቀበል ስራ ላይ ተጠምዷል፣ ስደት ይብቃ ብለዋል።

መንግሥት ባለፈው አንድ ዓመት በጦርነት እየተፈተነ ከ100 ሺህ በላይ ሕገ-ወጥ ስደተኞችን ተቀብሏል ያሉት አቶ ደመቀ፤ስናብር የማንፈታው ችግር እንደሌለ የህድያ ሕዝብ ማሳያ ነው፤ የመጣውን ሰላም ወደ ተሟላ የሰላም አውድ ለመመለስ በጋራ መስራት እንደሚገባም አመልክተዋል።

የትኛውም ስኬት ቢመዘገብ ዜጎችን ከሕገ-ወጥ ስደት ማስቆም ካልቻልን ወጤቱ ሙሉ አይሆንም ብለዋል አቶ ደመቀ።

ጥቂት ያመለጡ የተሳካላቸው ብዙዎችን ወጣቶች ለመከራ እየዳረጉ በመሆኑ ሁሉም ቆም ብሎ ማየት እንዳለበት መግለጻቸውን ኢዜአ ዘግቧል።

## በጦርነት ጉዳት የደረሰባቸው...

ከ1ኛው ገጽ የዞረ

ኃላፊ አቶ ዘመን ጁነዲ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ በሰሜኑ የአገራችን ክፍል ሲካሄድ የነበረው ጦርነት በአካባቢው ላይ በሚገኙ ኢንዱስትሪ ፓርኮች ላይ የተለያየ መጠን ያለው ጉዳት አድርሷል። የሰላም ስምምነቱን ተከትሎ በተፈጠረው የሰላም አየር ኮርፖሬሽኑ ጉዳት የደረሰባቸውን ኢንዱስትሪ ፓርኮች ወደ ሥራ ለማስገባት የሚያስችል የቅድመ ዝግጅት ሥራ እያከናወነ ነው።፡

መንግሥት በወሰደው ከፍተኛ ተነሳሽነት በመንገድ፣ በኤሌክትሪክ ሃይልና የቴሌኮም አገልግሎቶችን ዳግም ሥራ እያስጀመረ እንደሚገኝ አስታውሰው፤ እነዚህ በመሠረተ ልማቶች ዳግም አገልግሎት መስጠታቸው ፓርኮቹን ወደ አገልግሎት ለመመለስ ትልቅ አቅም የሚፈጥሩ መሆኑን ገልጸዋል።

ጉዳት ደርሶባቸው ከነበሩ ፓርኮች አንዱ የሆነው የኮምቦልቻ ኢንዱስትሪ ፓርክ በአሁኑ ጊዜ በጥሩ የሥራ እንቅስቃሴ ላይ ነው ያሉት አቶ ዘመን፤ የሠመራ ኢንዱስትሪ ፓርክም ጥሩ እንቅስቃሴ ላይ የሚገኝና የብዙ ባለሀብቶች ዓይን ማረፊያ እየሆነ መምጣቱን አመልክተዋል።

የሠመራ ኢንዱስትሪ ፓርክ በሙሉ አቅም ወደ ሥራ እንዲገባ ለማድረግና የመቀሌ ኢንዱስት ፓርክም ላይ ዳግም ወደ ስራ እንዲመለስ በኮርፖሬሽኑ መሠራት የሚገባቸው የቅድመ ዝግጅቶች ሥራዎችን ተጠናቀው ተግባራዊ እንቅስቃሴ መጀመሩን ገልጸዋል።

ከሰላም ስምምነቱ ጋር ተያይዞ በተለይም ባለፉት ሁለት ወራት የአገር ውስጥና የውጭ አገር ባለሀብቶች ወደ ኢንዱስትሪ ፓርኮች ለመግባት ጥያቄ እያቀረቡ ነው ያሉት ኃላፊው፤ በሂደት ላይ ያሉትን ሳይጨምር ባለፉት ሦስት ወራት ብቻ ከ20 በላይ ባለሀብቶች አስፈላጊውን ቅድመ ሁኔታ አሟልተው ወደ ማምረት ሥራ ገብተዋል ብለዋል።

የኮርፖሬሽኑ አመራሮች ታች ድረስ ወርደው ኩባንያዎች፣ አምራቾችና ሠራተኞችም ጭምር በምን ሁኔታ ላይ እንደሚገኙ የመከታተልና ውሳኔ በሚያስፈልጋቸው ጉዳዮች ላይ ውሳኔ እያሳለፉ የቅርብ ድጋፍና ክትትል እያደረጉ መሆኑንም ገልጸዋል።

እንደ አገር ወደ ኢንዱስትሪ ፓርኮች ለሚመጡ የአገር ውስጥ የውጭ ባለሀብቶች የተቀላጠፈ አገልግሎት ለመስጠት የአንድ መስኮት አገልግሎት በተጠናከረ ሁኔታ እየተሰጠ መሆኑን የጠቆሙት አቶ ዘመን፤ ወደ ሥራ ገብተው ውጤታማ እንዲሆኑ ለማስቻል የተለያዩ የማበረታቻ፣ የክትትልና እገዛ ተግባራት እንደሚከናወኑም አመላክተዋል።

# ነፃ ሃሳብ



ቁምላቸው አበበ በአማራ ባህል፣ ቱሪዝምና ማስታወቂያ ቢሮ፤ በኢትዮጵያ ዜና አገልግሎት፤ በደቡብ መገናኛ ብዙኀን፤ በጋዜጠኝነትና በታሪክ ባለሙያነት ያገለገሉ ሲሆን፤ የደቡብ ኤፍ ኤምን ከባልደረቦቻቸው ጋር በመሆንም አቋቁመዋል። በፌዴራል ውሃ ስራዎች ኮንስትራክሽን ድርጅትና በአለ በጅምላ በኮሙዩኒኬሽን ዳይሬክተርነት አገልግለዋል። ከአአዩ በቋንቋና ታሪክ የመጀመሪያ ዲግሪያቸውን የሰሩ ሲሆን፤ በዚሁ ዩኒቨርሲቲ በጋዜጠኝነትና ኮሙዩኒኬሽን ሁለተኛ ዲግሪያቸውን በማጠናቀቅ ላይ እያሉ ባጋጠማቸው ድንገተኛ ህመም ተስተጓጉሏል። ጥልቅ ሀሳብ ያዘሉ ወቅታዊ ጉዳዮች ላይ የሚያተኩሩ ፅሑፎችን በማህበራዊ ሚዲያና በተለያዩ ጋዜጦች በማውጣት ይታወቃሉ።

በቁምላቸው አበበ ይማም (ሞሼ ዳያን)
fenote1971@gmail.com

# አጉራ ዘለሉ የግብይት ሒደት ስርዓት ይበጅለት ፤

ሰሞኑን ለንባብ የበቃው የ"The Economist" የፈረንጆች ገና ልዩ ዕትም መጽሔት ፤ የራሽያ ዩክሬን መውረር ተከትሎ በተቀሰቀሰው ጦርነት ሳቢያ የስንዴ ፣ የዘይትና የሌሎች መሠረታዊ ሸቀጦች ዋጋ አልቀመስ በማለቱ ከ90 በላይ በሚሆኑ ሀገራት አለመረጋጋት መፍጠሩን ያትታል። በአሜሪካ ፣ በእንግሊዝና በአውሮፓ በተከሰተው የዋጋ ግሸበት የተነሳ የገንዘብ ፓሊሲያቸውን ጠበቅ አድርገዋል ። የአሜሪካ ግምጃ ቤት ከ2018 ዓም ወዲህ ለመጀመሪያ ጊዜ የብድር የወለድ ምጣኔውን ከፍ አድርጓል ።

የእንግሊዝ ባንክ ከ1980 ዓም ወዲህ ለመጀመሪያ ጊዜ እንዲሁ ከፍ አድርጓል ። ወደ ሀገራችን ስንመጣ ግን በገንዘብ ፓሊሲው ላይ ጠበቅ ያለ እርምጃ ካለመወሰዱ ባሻገር ፤ ከፍተኛ ገንዘብ ወደ ኢኮኖሚው እየተረጨ ነው። የአዲስ አበባን ጨምሮ በመላ ሀገሪቱ የሚካሄዱ ሜጋ ፕሮጀክቶች መቀጠላቸውን ስንመለከት ብሔራዊ ባንክም የገንዘብ ፓሊሲውን ጠበቅ ማድረግ የዋጋ ግሸበቱን ከመቆጣጠር አንጻር እምብዛም ለውጥ አያመጣም ማለቱ፤ መንግስትም ከዋጋ ግሸበቱ አንጻር ፊሲካል ፓሊሲውን በተለያዩ ምክንያቶች ለመከለስ አለመፈለጉ ፤ ከሌሎች ኀልቆ መሳፍርት ምክንያቶች ጋር ተዳምሮ ከምንገኝበት ሀይፐር ኢንፍሌሽንና የኑሮ ውድነት የምንወጣበትን መንገድ አርቆታል ።

ከአሁን አሁን የዋጋ ግሸበቱና የኑሮ ውድነቱ ላይ ወሳኝ መታጠፊያ ሊሆኑ የሚችሉ ውሳኔዎች ሊተላለፉ ይችላሉ ተብሎ ቢጠበቅም አንገብጋቢ ችግርነቱን የሚመጥን የተለየ ትኩረት አለማግኘቱና አቅጣጫ አለመቀመጡ ግራ ያጋባል። የዋጋ ግሸበቱና የኑሮ ውድነቱም ተባብሶ ቀጥሏል። ብሔራዊ ባንክ በበጀት አመቱ የዋጋ ግሸበቱንና የኑሮ ውድነቱን የሚያሰክኑ መጠነኛ እርምጃዎችን ቢወስድም የተጠበቀውን ያህል ሆኖ አለተገኘም ። የንግድና ቀጣናዊ ትስስር ሚኒስቴርም ታክቲካዊና ስትራቴጂካዊ መፍትሔ ይዞ ይመጣል ተብሎ ቢታሰብም ከ"ሰንበት ገብያ"ባሻገርና እሳት ከማጥፋት ውጭ ይሄነው የሚባል ነገር ይዞ አልመጣም ።

የሲሚንቶን ነገር እዚህ ላይ ልብ ይሏል ። የግብይት ስርዓቱን ስብራትና አጉራዘለልነት ቁልጭ አድርጎ ያሳያል ። እነዚህን ሁሉ ተቋማት አስተባብሮ መፍትሔ ይዞ ሊመጣ ይችላል ተብሎ የተጠበቀው የፕላንና ልማት ሚንስቴርም ይዞት የመጣ አዲስ የተጠና መፍትሔ አልታየም ። አለ ከተባለም ውጤት አላመጣም ። እርምጃዎች መሬት ላይ በተግባር ካመጡት ተጨባጭ ለውጥ ጋር ተነጻጽረው ስለሚመዘኑ ነው አጥጋቢ አይደሉም የሚል መደምደሚያ ላይ እየተደረሰ ያለው ።

በዚሁ ጋዜጣ ደጋግሜ እንደምለው የኑሮ ውድነት ፣ የዋጋ ግሸበት ፣ ስራ አጥነት ፣ ድህነትና ሌሎች ኢኮኖሚያዊ ችግሮች ብሔርና ሀይማኖት የላቸውም ። አማራ ፣ ኦሮሞ፣ ሲዳማ ፣ ሱማሌ ፣ ትግሬ ፣ ወዘተረፈ አይደሉም ። ኦርቶዶክስ፣ እስላም ፣ ክርስቲያን ፣ ዋቄ ፈና ፣ ወዘተረፈ አይደሉም ። ኢትዮጵያዊ ከፍ ሲልም ሰው ናቸው ። እነዚህ የኢኮኖሚ መሠረታዊ አላባውያን ማለትም የዋጋ ግሸበቱና የስራ አጥነቱ ቢያንስ ባለነጠላ አኃዝ እንዲሁም የኢኮኖሚ ዕድገቱ ጤናማ ከሆነ ሕዝብን በአዎንታ ሳይነጋገር አንድ ያደርጋሉ።

ሕዝብን ለድጋፍ ለአንድነትና ለፍቅር ያነሳሳሉ። በተቃራኒው እነዚህ መሠረታውያን ጤናማ ካልሆኑ የዋጋ ግሸበቱ አሻቅቦ የኑሮ ውድነቱ ከተባባሰ ፤ የስራ አጥነቱ ካሻቀበና ኢኮኖሚያዊ ዕድገቱ ፍትሐዊ ካልሆነ ሕዝብን በአሉታ ማለትም ለተቃውሞና ለአመጽ በአንድነት ያነሳሳሉ ። ይህ ኢኮኖሚያዊ ስኬታችንም ሆነ ውድቀታችን ከፓለቲካው በላይ ጉልበት እንዳለው ያስረዳል። ከፓለቲካችን በላይ ለኢኮኖሚያችን ልዩ ትኩረት መስጠት ግድ የሚለው ለዚህ ነው ።

በዚህ ሰሞን በተለያዩ ሰበቦችና ምክንያቶች የተቀሰቀሱ ቀውሶች ፓለቲካዊ ካባ ይደረብላቸው እንጅ በውስጠ ታዋቂነት የኢኮኖሚያዊ ብሶትና ተስፋ መቁረጥ ቅርሻዎች ናቸው ። የዋጋ ንረቱንና የኑሮ ውድነቱን ለማርገብ የሚደረገው ጥረት የችግሩን ስፋትና ጥልቀት የሚመጥን፣ አጥጋቢና ወጥ አለመሆኑን ለታዘበ ፤ ለዘላቂ መፍትሔ ተጨባጭ ፣ ግልጽና ተፈጻሚ የአጭርና የረጅም ጊዜ ዕቅድ ካልተነደፈ ፤ የተለያዩ ጥያቄዎች ለማንሳት ያስገድዳል ።

የኑሮ ውድነቱንና የዋጋ ግሸበቱ በዚህ ከቀጠለ ከጽንፈኝነትና የሴራ ፓለቲካ በላይ የህልውና አደጋ ፤ የኑሮ ውድነቱ የደህንነትና የጸጥታ ስጋት የመሆን አሉታዊ አቅሙ በቅጡ ግንዛቤ ተይዞበታል !? የኑሮ ውድነት ወላፈኑስ ያለ ልዩነት እኩል ዜጋውን እየተሰማው ነው !? የመንግስት ባለስልጣናትስ የኑሮ ውድነት እንደ ተራው ሕዝብ ይሰማቸዋል !? ካልተሰማቸው እንዴት የመፍትሔው አካል ይሆናሉ !? እንዴትስ ለመፍትሔው ፓለቲካዊ ቁርጠኝነት ሊኖራቸው ይችላል !?

ሁለት አስር አመታትን ያስቆጠረው የዋጋ ግሸበትና የኑሮ ውድነት የዜጋውን ኑሮ በብርቱ እየፈተነው ፤ ከኢኮኖሚያዊ ችግርነት ወደለየለት ማህበራዊና ፓለቲካዊ ቀውስነት እንዳይባባስ እያሰጋ ይገኛል ። በእንቅርት ላይ ጆሮ ደግፍ እንዲሉ ኢኮኖሚው ለቀደሙት 27 አመታት የአንድ ቡድንና የጭፍራው መጠቀሚያ በመሆኑ በተከሰተው ኢፍትሐዊ ተጠቃሚነት ላይ አሻጥር ፣ ስግብግብነት ፣ አልጠግብ ባይነት፣ ግጭት ፣ ጦርነትና አለመረጋጋት ተጨምሮበት ኑሮው አልቀመስ ብሏል ።

በአናቱ የውጭ ምንዛሬ እጥረት ፤ የተራዘመ የግብይት ሰንሰለት ፤ ከገበሬ ማሳና ከጉልት እስከ ጅምላ አከፋፋይ የተሰገሰገ ደላላ ፤ የገነገነ ሙስና ፣ በግብይት ሰንሰለቱ የተንሰራፋው ስርዓት አልበኝነት ፤ ዋጋን በአድማ መወሰን ፤ ምርትን በመደበቅ ሰው ሰራሽ እጥረት መፍጠር ፤ የፍላጎትና የአቅርቦት አለመጣጣም ፤ የኑሮ ውድነቱን ለመከላከል በመንግስት መዋቅር ዘንድ ወጥ የሆነ ፓለቲካዊ ቁርጠኝነት አለመኖር ፤ የሎጅስቲክስ አገልግሎቱ ቀልጣፋ አለመሆን ፤ ወደብ አልባ በመሆናችን በየአመቱ ቢሊዮኖችን የምናወጣ እና ስለሙብቱ የሚቁረቁርና የሚጠይቅ ጠንካራ ሸማች አለመፈጠሩ እንደ ዚምባብዌና ቬኒዞይላ ባይሆንም በሰዓታት ልዩነት ለሚተኮስ ከፍተኛ የዋጋ ግሸበት እንዲዳረግ ሆኗል።

በየፍጆታ ሸቀጦች ላይ የሚታየው የዋጋ ግሸበት በሌሎች ምርቶችና አገልግሎቶች ላይ ግሸበትንና የኑሮ ውድነቱን እያባባሰው ይገኛል ። አምስት ሊትር የምግብ ዘይት ሰሞኑን 1010 ብር መግባቱ ሳያንስ ፤ ሲያሻው ከገበያ ይጠፋል ። ስንዴን ወደ ውጭ ለመላክ እየተዘጋጀን ባለንበት የስንዴ ፉኖ ዱቄት በኪሎ ወደ 68 ብር ተተኩሷል ። ገና ሲቆርሱት ዱቄት የሚሆን ዳቦ 6 ብር ገብቷል ። ጤፍ እንደዚሁ በኪሎ 63ና ከዚያ በላይ ገብቷል ። ቡና በኪሎ ወደ 500 በር አሻቅቧል ። ሽንኩርት ፣ ቲማቲም አጠቃላይ አትክልትና ፍራፍሬ አልቀመስ ብሏል ። አቡካዶ በኪሎ 80 ብር ፣ ቢጨምቁት ጠብ የማይለው አንድ ሎሚ 10 ብር ገብቷል ። ቲማቲም ከሰሞኑ በአንጻራዊነት ቀንሷል ቢባልም እንደለመደው ተመልሶ ማሻቀቡ አይቀርም ። እህልና ጥራጥሬውም ብሶበታል ።

በዚህ ሳቢያ በመዋቅራዊና በተቋማዊ ችግር የተነሳ ጽኑ ታማሚ ሆኖ ለኖረው ኢኮኖሚ ሌላ ራስ ምታት ሆኖበታል። የለውጡ መንግስት ባለፉት አራት አመታት የኑሮ ውድነቱንና የዋጋ ግሸበቱን ወደ ነጠላ አኃዝ ለማውረድ ያደረገው ጥረት ውጤት ሊያስገኝ አልቻለም ። አልበርት አነስታይን፤" ችግሩን በፈጠረው አስተሳሰብ ፤ ችግር መፍታት አይቻልም:: "እንዳለው ከሳጥኑና ከተለመደው አተያይ ወጣ ብሎ መፍትሔን ማማተር ግድ የሚለ አሳሳቢ ወቅት ላይ ብንገኝም ፤ በሚያሳዝን ሁኔታ የሚፈለገውን ያህል እየሰራን አይደለም ። እንዲያውም ችግሩ ከዕለት ወደ ዕለት እየተባባሰ ይገኛል ።

ስነ ምግባር የጎደላቸው አንዳንድ የመንግስት አመራሮች በዚህ ሕገ ወጥ የግብይት ስርዓት ተሳታፊ ሆነው መገኘታቸው ችግሩን እንዳወሳሰበው በዚያ ሰሞን የጸረ ሙስና ኮሚሽን ባካሄደው መድረክ ይፋ ሆኗል ። የኦሮሚያ ክልል ርዕሰ መስተዳድር አቦ ሽመለስ አብዲሳ ባለፈው በተካሄደው ጨፌ ኦሮሚያ ይሄን ሀቅ ደግመውታል ። ከዚህ ውይይት በፊት የብሔራዊ መረጃና ደህንነት አገልግሎት ከሕዝብ በደረሰው ጥቆማና ባደረገው ክትትል መሠረት በየመካዝኑ ተከዝነውና ተደብቀው የሚገኙ የምግብ ዘይት ፣ የስንዴ ዱቄት ሌሎች መሠረታዊ ሸቀጦችን ለመያዝ ሲንቀሳቀስ በየአካባቢው ያለ አመራር ለመተባበር እንዴት እግሩን ይጎትትና ለማደናቀፍም ይጥር እንደነበር መግለጹ የኮሚሽኑን ግኝት ተጨባጭ ያደርገዋል ። መንግስት መዋቅሩን ካላጠራ ችግሩ ተባብሶ የስርዓቱም የሀገሪቱም አደጋ መሆኑ አይቀርም ።

ይሄን ስርዓት አልባ የግብይት አሰራር መንግስት በማያዳግም ሁኔታ በሕግ አግባብ ስርዓት ሊያሲዘው ካልቻለ፤ ከማሳና ከጉልት እስከ ጅምላ አከፋፋይ የተሰገሰገውን ደላላ ከግብይት ሰንሰለቱ ካላስወጣ ፤ በድጎማ ከውጭ የሚገባን ዘይትና ስንዴ ለነጋዴው 70 በመቶ ፤ ለሸማቹ 30 በመቶ የነበረውን የስርጭት ቀመር ቀይሮ የተገላቢጦሽ ካላደረገ ፤ በመሠረታዊ ሸቀጦች ላይ ተመንና የትርፍ ሕዳግ ካልተቀመጠ ፤ ገብያውን ለውጭ ኩባንያዎች ክፍት ካላደረገው ፤ የንግድ ውድድርና የሸማቾች ጥበቃ ባለስልጣን ከንግድና ቀጣናዊ ትስስር ሚኒስቴር ጉያ ወጥቶ ስልጣኑና አደረጃጀቱ ተሻሽሎና ተጠናክሮ እንደገና ካልተደራጀ ፤ በግብይት ሒደቱና ሰንሰለቱ የሚስተዋለው አጉራዘለልነትና ውንብድና በሕግ የበላይነት ስርዓት እንዲይዝ ካልተደረገ ፤ ችግሩ ተባብሶ ተባብሶ ወደለየለት የጸጥታና የደህንነት ችግር እንዳይባባስ ያሰጋል ።

የዋጋ ግሸበቱ ከ40 በመቶ በላይ ተተኩሶና በየቀኑ እየተባባሰ ባለበት ፤ የኑሮ ውድነቱ ከእጅ ወደ አፍ የነበረውን ኑሮ የማይቀመስ ካደረገው ፤ የስራ አጡ ቁጥር ከዕለት ወደዕለት እየተባባሰ እንዴት ስለኢኮኖሚያዊ ስኬት ማውራት ይቻላል ። እንዴት ስለብልጽግና ማለም ይታሰባል። ከፍ ብሎ ለመግለጽ እንደተሞከረው ይሄን ኢኮኖሚያዊ ትብታብ አሁን ላለው መንግስት በእዳ የተላለፈለት እንጅ ለብቻው የፈጠረው አይደለም ። ሆኖም ይሄን ትብታብ የመፍታት ኃላፊነት ትክሻው ላይ ወድቋል ። እንደ ሰበብ/excuse/ሊጠቀምበትም አይችልም ። የጦርነቱ ጫናም ቀላል አይደለም ። ኮቪድና የራሽያ ጦርነት የፈጠረው የዋጋ ግሸበትም ተጽዕኖው ከባድ ነው ።

በባህሪው ገብያ/ኢኮኖሚ ድንጉጥ ነውና ። አይደለም ጦርነትና የግጭት አዙሪት የተሳሳተ ፓሊሲና የገብያ ትንበያ/ speculation/ገብያን ያስበረግጋል ። ይሄን ችግር ይበልጥ አሳሳቢ ያደረገው ሸማቹ ሕዝብ የመንግስት ቁርጠኝነት በሙላት ሲገለጥ አለማየቱ ነው ። በዚህ የተነሳ ከዛሬው ነገ እንዳይከፋ አስፈርቶታል ። አስጨንቆታል ። የኑሮው ጉዳይ ልዩ ትኩረት ይሻል ። በተለይ በግብይት ስርዓቱ የሕግ የበላይነትን የማስፈን ጉዳይ ለነገ የሚባል ጉዳይ አይደለም ። ከአቅርቦትና ከፍላጎት አለመመጣጠን ፤ ከኮቪድና ከራሽያ ጦርነት ፤ በሀገራችን ከሚስተዋሉ ቀውሶችና ግጭቶች ባልተናነሰ ለኑሮ ውድነቱ መባባስ ግንባር ቀደም ተጠቃሹ ስርዓት አልባ የሆነው የግብይት ስርዓት ነው ። ለዚህ ነው በግብይት ስርዓቱ የሕግ የበላይነት ይረጋገጥ እየተባለ የሚወተወተው ። ስርዓት ይበጅ የሚባለው ።

መንግስት ችግሩን በዘላቂነት ለመፍታት ከብር ለውጥ ጀምሮ ምርትንና ምርታማነትን ለማሳደግ ኩታ ገጠም ግብርናን ፤ የቆላ ስንዴን ፤ የግብርና ሜካናይዜሽንን ለማስፋፋት ፤ የአረንጓዴ አሻራን ለማሳካት ጥረት እያደረገ ነው። ሆኖም ምርት ማሳደግ ብቻውን መፍትሔ አይሆንም። ብልሹው የግብይት ስርዓት ካልታረመ ፤ ደላላው ከገብያው ካልወጣ ፤ የኢኮኖሚ አሻጥረኞችን በሕግ ስርዓት ማስያዝ ካልተቻለ ፤ ማህበራዊ ስብራታችን ካልታጀለ ምርታማነታችን የቱንም ያህል ቢያድግ ከዚህ አዙሪት መቼም ቢሆን ሰብረን መውጣት አንችልም ። ወቅቱ ስንዴን ጨምሮ ምርት ተሰብስቦ ወደ ገብያ የሚቀርብበት ቢሆንም ገብያው በደላላ ስለሚወሰን የዋጋ መቀነስ አይታይም ።

ሆኖም ይሄ ችግር በመንግስት የተናጠል ጥረት ብቻ አይፈታም ። ዩኒቨርሲቲዎች ፣ እንደ የኢኮኖሚክስ ባለሙያዎች ያሉ ማህበራት ፣ የንግድና የዘርፍ ማህበራት ምክር ቤት ፣ የሀይማኖት ተቋማት ፣ እንደ የኢትዮጵያ ሸማቾች መብት ተቆርቋሪ ድርጅት ያሉ የሲቭል ማህበረሰብ ድርጅቶችና ሌሎች ባለድርሻ አካላት ተቀናጅተውና ተናበው መስራት ይጠበቅባቸዋል ። በተለይ ዩኒቨርሲቲዎችና እንደ የኢኮኖሚክስ ባለሙያዎች ማህበር ያሉ ተቋማት ይሄን ችግር ለመፍታት ጥናትና ምርምር በማድረግ የፓሊሲ ሀሳብ ማመላከትና ማመንጨት ይጠበቅባቸዋል ።

ይሄን ሁሉ ተቋም ተሸክመን የዋጋ ግሸበትና የኑሮ ውድነት እንዴት እንደ ስፔስ ሳይንስ እስከ መቼ እንደተወሳሰበብን ይቀጥላል ። በእርግጥ የዋጋ ግሸበቱና የኑሮ ውድነቱ የተፈጠረው በምርት እጥረት ነው ፣ በግብይት ስርዓት ችግር ፣ እሴት በማይጨምር ደላላ ፣ በውጭ ምንዛሬ እጥረት ፣ በአልጠግብ ባይ ነጋዴዎች ፣ በዩክሬንና በራሽያ ጦርነት ፣ በኮቪድ 19 የተነሳ ፤ ወዘተረፈ ነው !? መልሱን በጥናት ማግኘት የማያዳግም መፍትሔ ለማስቀመጥ ይረዳል። በተረፈ ችግሩንና ተጠያቂነቱን ያለአድራሻ ማስቀመጥና ጣት መቀሳሰር ከተዘፈቅንበት አረንቋ አያወጣንም ።

የውጭ ንግዳችን ከሀገር ውስጥ ገብያው ይልቅ የውጭ ምንዛሬ ማሳደድ ላይ መጠመዱ የኑሮ ውድነቱን አባብሶታል። የቅባት እህል ወደ ውጭ ልኮ የፓልም ድፍድፍ ገቢ ያደርጋል። አትክልትና ፍራፍሬ ወደ ውጭ ልኮ መድሀኒት በውጭ ምንዛሬ ያስገባል ። የውጭ ንግድ መሠረቱንና አይነቱን ማስፋት ሲገባው ከሸማቹ ጉሮሮ እየቀማ ወደ ውጭ ይልካል ። ይሄ የተፋለሰና ወለፈንዲ የሆነ አሰራር በጥናት ተፈትሾ መስተካከል አለበት ። የሀገር ውስጥ ገብያን እያራቆቱ ምርትን ወደ ውጭ መላክ ለዜጋው አለማሰብ ነውና። ስንዴን ወደ ውጭ ለመላክ የሚደረገውን ሩጫ እዚህ ላይ ልብ ይሏል። የፉኖ ዱቄት በኪሎ ወደ 70 ብር ተጠግቶ፤ ሲቆረስ ዱቄት የሚሆን ዳቦ 6 ብር እየተሸጠ ባለበት ሀገር ገብያው ሳይረጋጋ ስንዴን ኤክስፓርት ለማድረግ መጣደፍ ምን ይሉታል ።

መንግስት የግብይት ስርዓቱን ስድ መልቀቁ የኑሮ ውድነቱንና የዋጋ ግሸበቱን አባብሶታል ። ስለሆነም በሕግና በአደረጃጀት ነገ ዛሬ ሳይል ስርዓት ሊያሲዘውና የቁጥጥርና የክትትል አሰራር ሊዘረጋ ይገባል ። የመኖሪያና የንግድ ቤት ኪራይ የኑሮ ውድነቱን ከሚያባብሱ ችግሮች ዋናው ነውና ተመን ሊወጣለት ይገባል ። በመሠረታዊ ሸቀጦች የትርፍ ሕዳግና የዋጋ ተመን ሊወጣ ግድ ይላል ። በአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ የኢኮኖሚክስ ትምህርት ክፍል መምህር ዶክተር ብርሃኑ ደኑ ሰሞኑን ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ በሀገሪቱ ውስጥ የንግድ ሥርዓቱ ፈር የለቀቀ እንዲሆንና የኑሮ ውድነትና የዋጋ ግሸበት እንዲባባስ ከሚያደርጉ ምክንያቶች አንዱና ዋነኛው በገበያ ሥርዓቱ ውስጥ የሸቀጦች የትርፍ ህዳግ ገደብ አለመቀመጡ ነው::

በመሆኑም በየጊዜው እየጨመረ የመጣውን የኑሮ ውድነትና የዋጋ ግሸበት ለማረጋጋት መንግሥት የሸቀጦች የትርፍ ህዳግ ገደብ ሊያስቀምጥ ይገባል ብለዋል :: ሌላው ለሸማቾች ሲል ዘይት ፣ ስንዴና ሌሎች መሠረታዊ የምግብ ሸቀጦች ከቀረጥ ነጻ እንዲገቡ ቢያደርግም የቁጥጥርና የክትትል ስርዓት ስለአልዘረጋ ገብያው ሊረጋጋ አልቻለም። መንግስት በዚህ ፓሊሲው ከ27 ቢሊየን ብር በላይ ቢያጣም ለሸማቹ ጠብ ያለ ነገር የለም ። ይህ ከፍ ብሎ ለመግለጽ እንደተሞከረው የሕግ ክፍተት መኖሩን ያሳያል ። ስለሆነም በማያዳግም ሁኔታ ስርዓት ሊበጅለት ይገባል ።

ትኩረት በኑሮ ውድነት አለንጋ እየተገረፈ ላለው ሸማች!!!

# መንገደኛው ታሪክ ተካይ

ጽጌረዳ ጫንያለው

አያሌው አስፋው ይባላሉ:: ትውልዳቸው ወሎ ክፍለአገር ዶቢ በሚባል አካባቢ በወራኢሉና በቦረናሳይንት አውራጃ መካከል ነው:: ሁሉንም በእኩል ደረጃ ማስተዳደር ከተቻለ በሙስሊሙ እምነት ዘንድ ከአንድ በላይ ሚስት ማግባት ይፈቀዳልና እርሳቸው በብዙ እናቶች መሀል ሆነው አድገዋል:: አምስት የሚሆኑ እንጀራ እናቶችን ባህሪም ለምደው ዓመታትን አስቆጥረዋል:: ምክንያቱም እናትና አባታቸው ተለያይተው ስለነበር አባታቸውን በመምረጣቸው ይህ ሆኖባቸዋል:: በእርግጥ በአንድ በኩልም እድለኛ ነበሩ:: ምክንያቱም የአያት ልጅ ቅምጥል እንዲሉት አይነት የመሆን አጋጣሚንም አግኝተዋል::

እርሳቸው እድለኛ ሆነው ከእናታቸው ጋር አለማደጋቸው የእንጀራ እናት ባህሪን ቢያሳያቸውም የተጎዱበት እንደነበር አይሰማቸውም:: ምክንያቱም ከሰው ጋር መኖር እንዴት እንደሚቻል አለማምዷቸዋል:: ረጅሙን የልጅነት ጊዜና የወጣትነት እድሜያቸውን ሲያሳልፉ መሰረት የሆናቸው እርሱ ስለነበር:: በዚያ ላይ ብቻቸውን ራሳቸውን ለማገዝ በሚያደርጉት ጥረት ውስጥ መግባባት ቀላል ነገር እንዲሆንላቸው ያደረገው በዚያ በተለያየ ቤተሰብ ውስጥ ማደጋቸው ነው:: በእርግጥ አንዳንዴ ይከፋቸዋል:: ምክንያቱም እንደሌሎች ሕጻናት ሲከፋቸው እናታቸው ጋር መሄድ አይችሉም:: እርሷን ያጧት ገና ትንሽ ሳሉ በደንብ ሳይጠግቧት ነው::

የአምስት እንጀራ እናት ባህሪ ጠንካራ ያደረጋቸው ባለታሪካችን፤ በብዙ ፈተና ውስጥ ቢያልፉም በቀላሉ አይወድቁም:: ይበልጡንም ጉልበታም ሆነው ይወጣሉ እንጂ:: ከሊስትሮነት እስከ software engineernet (ዳታ ዴቨሎፐ አድራጊነት) የደረሱትም በዚህ ብርታታቸውና ታታሪነታቸው እንደሆነ በሚገባ ያውቃሉ::



ፎቶ በገባቦ ገብሬ

አቶ አያሌው አስፋው

### ሊስትሮው ተማሪ

የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርታቸውን የተከታተሉት በአቅራቢያቸው ባለ ቦረና ሳይት አውራጃ መካነሰላም ላግሜራ ትምህርት ቤት ሲሆን፤ ከአንደኛ እስከ ሦስተኛ ክፍል ተከታትለውበታል:: ከዚያ ወደ ሆጤ በር ትምህርት ቤት አመሩ:: ከአራተኛ እስከ ስድስተኛ ክፍል ትምህርታቸውን መከታተል ቻሉ:: በዚህ ትምህርት ቤት በጣም ጎበዝ ተማሪ በመሆናቸው ሦስቱንም ክፍል በአንድ ዓመት ውስጥ አጠናቀውታል::

ከስድስተኛ ክፍል በኋላ ግን ግድ ወደሌላ አካባቢ መሄድና መማር ነበረባቸው :: ምክንያቱም በዚያ ሰባተኛ እና ስምንተኛ ክፍልን የሚማሩበት ትምህርት ቤት የለም:: ስለዚህም ቀን ሙሉ በእግራቸው እየተጓዙ ወደ ሚማሩበት አቃስታ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት አቀኑ:: ይህንን ቦታ ቀደም ሲል በአንድ አጋጣሚ ያውቁት ነበር:: የስድስተኛ ክፍል ፈተና ለመውሰድ ፎቶግራፍ መነሳት ግድ ነውና በአቃስታ አቋርጠው ደሴ ድረስ አራት ቀን ሙሉ ከአባታቸው ጋር በመሆን ተጉዘ ፎቶግራፉን ተነስተው ትምህርታቸውን ተመዝግበው ከዛም ከሆጤ በር እስከ አቃስታ ድርስ በአንድ ቀን ተጉዘው ሰባተኛና ስምንተኛ ክፍልን ተምረዋል::

እንግዳችን የወሎ ድርቅ ሲመጣ በሁሉም አካባቢ ላይ ችግር ነበርና ትምህርታቸውን ለመቀጠል አልቻሉም:: አቃስታ ከተማ ላይ የእርዳታ ማስተባበሪያ ኮሚሽን ተቋቁሞ ነበርና ከኮሚሽኑ ኃላፊ ጋር በመግባባታቸው ለእርዳታው የሚመጡ እቃዎችን የመመዝገብ ስራ አገኙ:: ስራውንም እየሰሩ ሰኔ ወር ላይ ትምህርት ስለማይገባ ወደቤታቸው ሊሄዱ ተሰናዱ:: ሆኖም ተማሪዎች ወደ ማሰልጠኛ ይግቡ የሚል ትዕዛዝ ስለመጣ እርሳቸውን ጨምሮ በአቃስታ የሚማሩ ተማሪዎች በኮምቦልቻ እርሻ ማሰልጠኛ ውስጥ ገቡ:: የሦስት ወር ስልጠናም ወሰዱ::

ከስልጠናው በኋላም ቢሆን ወደቤታቸው አልተመለሱም:: ዳግመኛ ለሌላ ስልጠና ወደ ታጠቅ ተላኩ:: እዚህም የሦስት ወር ስልጠና ወሰዱ:: ስልጠናው በአብዛኛው ውትድርናን መሰረት ያደረገ ነበርና ከዝንባቤ ነጻ አውጪ አባላት ጋር በመሆን ሰለጠኑ:: ስልጠናው ሲጠናቀቅ ሦስት ምርጫዎች ተቀመጡላቸው:: የመጀመሪያው ወደ ሰሜን ከዘመተው ጦር ጋር ተቀላቀሎ መሄድ ሲሆን፤ ሁለተኛው ደግሞ ወደ ሰፈራ መሄድ ነበር :: ሁለቱንም አልፈልግም ያለ ደግሞ ወደ መጣበት አካባቢው ይመለስ የሚሉ አማራጮች ተቀምጠው ነበር ::

እንግዳችን ትምህርቴን ብቀጥል ይሻለኛል ብለው ሦስተኛውን ምርጫ መርጠው ወደ ወሎ ተመለሱ:: ነገር ግን ያሰቡት አልሆነም:: ስለዚህም ትምህርት የሚማሩበትን መንገድ ለማግኘት የተለያዩ አማራጮችን ሞከሩ:: በስተመጨረሻ ወደ አዲስ አበባ ሄደው በቤት ሰራተኝነት ተቀጥረው ሲሰሩ ትምህርት የመማር እድሉን አገኙ:: ቀን የቤት ሰራተኛ ናቸው በማታው ክፍለጊዜ ደግሞ በዳግማዊ ምኒልክ ትምህርት ቤት የዘጠነኛ ክፍል ትምህርታቸውን ይከታተላሉ ::

አስረኛ ክፍል ሲደርሱ ደግሞ ሁኔረታዎች ተቀያየሩና አቶ እያሱ የሚባሉ ጓደኛቸው ጋር በመሆን ቀን ቀን ሊስትሮና ጋዜጣ መሸጥን የመሳሰሉ ስራዎችን እያከናወኑ በማታው ክፍለ ጊዜ ደግሞ ትምህርታቸውን ቀጠሉ:: 12ኛ ክፍልም እስኪደርሱ የማንንም እገዛ አልጠየቁም:: በራሳቸው ሁሉንም ነገር ማከናወንም አልተሳናቸውም :: ይሁንና ዩኒቨርሲቲ መግቢያ ውጤት ግን ማምጣት አልቻሉም:: ስለዚህም ውጤታቸው የሚያስገባቸው ኮሌጅ ነበርና ኮተቤ መምህራን ማሰልጠኛን ተቀላቀሉ:: በኮሌጁም በውጪ ቋንቋና ስነጽሁፍ ትምህርት መስከ በዲፕሎማ ተመረቁ ::

በነገሮች ተስፋ ቆርጠው የማያውቁት አቶ አያሌው፤ምንም እንኳን ድግሪያቸውን የመማር ከፍ ያለ ፍላጎት ቢኖራቸውም በተመረቁበት ዘርፍ ለሁለት ዓመት ማገልገል ነበረባቸውና ‹‹ልቤ ፋና አንደኛና መለስተኛ ትምህርት ቤት›› የመምህርነት ስራቸው ጀመሩ ፤ ቀን እየሰሩ ማታ በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የዲግሪ ትምህርታቸውን ጀመሩ :: በግብርና ሚኒስቴር ከዚያም የውጪ ኢኮኖሚ ትብብር ሚኒስቴር ውስጥ በመዘዋወር ሰርተዋል:: እናም ይህ ሥራቸው የፈለጉትን ማድረግ አላስቻላቸውም:: ስለዚህም የአዲስ አበባውን ዩኒቨርሲቲ ትምህርት ትተው ሌሎች አማራጮችን መፈለግ እንዳለባቸው ወሰኑ:: ይህ ውሳኔ ደግሞ የውጪ የትምህርት እድሎችን መሞከር ነበርና ፤ ተሳካላቸው::

አውስትራልያ የሚገኝና ወሎን ጎንግ ‹‹Wollongong University›› የሚባል ዩኒቨርሲቲ ምላሽ ሰጣቸውና ለመማር ወደ ስፍራው ተጓዙ:: በዩኒቨርሲቲውም የኮምፒውተር ሳይንስ ትምህርት አጠኑ:: አሁን ደግሞ ሁለተኛ ድግሪያቸውን በሳይቨር ኢንቨስቲጌሽን ኤንድ ፎረንሲክ እንዲሁም Information and Communications Technology የትምህርት መስከ ሙሉ ወጪያቸው በአውስትራልያ መንግስት ተሸፍኖላቸው እየተማሩ ይገኛሉ:: ነገር ግን ትምህርቱ በፈተና የታጠረ እንደነበር ያወሳሉ::

የመጀመሪያው ሳይቨር ኢንቨስቲጌሽን ኤንድ ፎረንሲክ የሚል ጨምረው እየተማሩ ሳለ አንድ ዓመት ተኩል እንደተማሩ ከመምህራቸው ጋር ተጋጩ:: ምክንያቱ ደግሞ ፕላጃሪዝም አድርገሃል የሚል ነበር:: ትምህርቱ የሚሰጥበት ስርዓት ፊት ለፊት ሳይሆን በበይነ መረብ በመታገዝ (በዙም) ነው:: እናም አንድ ጉዳይ ይመረጥና ጥያቄ ተሰጥቶ በቤት ውስጥ ፈተና (አሳይመንት) መልኩ ለአሰልጣኙ በጽሁፍ ይቀርባል። በሰለጠኑት መሰረትም መስራትና የተሻለ ሀሳብ ማቅረብ ደግሞ የግድ ነው:: ስለዚህም እርሳቸው ይህንን አድርገው ቢሰሩም በተደጋጋሚ ከሰሳቸው:: ስለዚህም አስተማሪውን እውቀት አለው እንጂ ማስተማር አይችልም ብለው ከጓደኞቻቸው ጋር በመሆን ከእርሱ ክፍል ራሳቸውን ለማግለል ወሰኑ። ዩኒቨርሲቲው ሁኔታውን ተረዳላቸውና ወደሌላ የትምህርት መስክ እንዲቀይሩ አገዛቸው:: በዚህም ከአንድ ዓመት ትምህርት በኋላ ቀይረው የኢንፎርሜሽን ኮሚኒኬሽን ቴክኖሎጂን መማር ጀመሩ:: አሁን ትምህርቱን ለማጠናቀቅ የስድስት ወር ጊዜ ብቻ ነው የቀራቸው::

### ችግር የፈጠረው ጥንካሬ

አቶ አያሌው ገና ከቤተሰብ ጋር እያሉ ነው የራሳቸው ጌታ መሆን እንዳለባቸው የተረዱት:: በዚህም በርካታ ችግሮችን ማለፍ እንዲችሉ ሆነዋል:: የመጀመሪያው የወሎ ድርቅ ሲሆን፤ ሌላው ደግሞ መሬት ላራሹ ተብሎ እንደልባቸው መንቀሳቀስ ያቃታቸው ጊዜ ነበር:: ሆኖም አንድም ቀን ለችግር እጅ ሰጥተው የማያውቁት አቶ አያሌው ሰው ካገኙ ሰው እንደሚሆኑ በሚገባ ያምናሉ:: አንድ ቀን ይህ እንደሚሆንም ያስባሉ:: እምነታቸው ግን በአሰቡት ቀን ባይሆንም እውን ሆኖላቸዋል::

ሁለቱ የአክስታቸው ልጆች ከጅማ ሲመጡ እንዲወስዷቸውና በዚያ እየሰሩ እንዲኖሩ ጠይቀዋቸው ነበር:: ነገር ግን እነርሱ የራሳቸውን እህትና የእህት ልጆችን ስለወሰዱ ለእርሳቸው ቦታ አልነበራቸውም:: እሳቸውም አልተናደዱባቸውም፤ ተስፋም አልቆረጡም:: ይህ አቋማቸው በወራት ውስጥ ሌላ አቅጣጫ ጠቆማቸው:: በአካባቢያቸው የሚያውቁትና የሚቀርቡት ሰው ወደ ጅማ እንደሚሄድ ነገራቸው:: ስለዚህም ቤተሰብ በዚያ አላቸውና ለማንም ምንም ሳይናገሩ ተከትለዋቸው ሄዱ:: ጅማ ሲደርሱም ዘመዶቻቸውን ተቀላቀሉ:: ዓላማቸው ሰርቶ መለወጥ ነውና ብዙም በዘመድ ቤት አልቆዩም::

ድንገት ተነስተው አንዱን የአክስታቸውን ልጅ ይዘው እግራቸው ወደመራቸው ቦታ ለመድረስ ጉዞ ጀመሩ:: ጫካውን እያቋረጡም "የቡ" የምትባል ከተማ ደረሱ:: ከተማዋ በስፋት ቡና የሚመረትባት ነበረች:: ወቅቱ ደግሞ ቡና የሚለቀምበት ጊዜ ነው:: እናም እነርሱም በለቀማ ሥራው ላይ ተሰማርተው ለስድስት ወራት ሰሩ:: ወደ ስምንት ኩንታል ቡና ለየግላቸው አግኝተውም ተመለሱ:: ከዚያ ልጁን ለቤተሰቡ መልሰው የደረሳቸውን ቡና በመሸጥ ገንዘቡን ይዘው ወደትውልድ ቀያቸው ወሎ ገቡ::

ወሎ ከደረሱ በኋላ ግን ሀሳባቸውን አባታቸው ሊቀበሉት አልፈለጉም:: ‹‹አግብተህ ውለድ፣ ከዚህ መሄድ የለብህም›› አሏቸው:: ገና ሰርቼ አልጠገብኩም የሚሉት ባለታሪካችን በሀሳባቸው ሊስማሙ አልቻሉም:: ስለዚህም በሁለቱ መካከል አለመግባባት ተፈጠረና ቀያቸውን ትተው ወደ አዳማ (ናዝሬት) አክስታቸው ጋር ተጓዙ::

አክስታቸው ለእርሳቸው ቀርቶ ለራሳቸውም በብዙ ድካምና ልፋት የሚኖሩ ናቸው:: ስለዚህም ክረምትን ብቻ በዚያ ቤት አሳልፈው ሥራ ቅጥር ወደ ደላሎች ጋር አመሩ:: ከአዲስ አበባ የመጡ ሰዎች አገኙ ፤ ሰዎቹ የተማሩና ሌሎችን ማገዝ የሚወዱ ስለነበሩም እንደሚያስተምሯቸው ቃል ገቡላቸው:: ስለዚህም ማቄን ጨርቄን ሳይሉ ተከተሏቸው:: አዲስ አበባን መማሬያዬም፤ መስሪያዬም ያሉት ከዚህ በኋላ ነበር :: አሁን ያሰቡትን ነገር ያገኙም መስሏቸዋል:: ምክንያቱም በማታ የሚማሩበት እድል ተሰጥቷቸዋል:: ቀን ደግሞ በቤት ሰራተኝነት ገንዘቡ ቢያስም ተከፍሏቸው ይሰራሉ:: ብዙ ነገሮች ተደላድለውላቸዋል::

ከጥበቃ እስከ ጽዳት ድረስ የመስራት ግዴታው የእርሳቸው ነበር:: ሥራው የወንድ የሴት አይባልም:: በዚህ ደግሞ ቀጣሪያቸው ሳይቀሩ ይሳተፋሉ:: እማወራዋ ታማሚ ስለሆኑ አባወራው ናቸው ምግብ የሚያበስሉት:: ከቤት ወጥተው ከጓደኞቻቸው ጋር በመሆን መስራት ሲጀምሩ ደግሞ የበለጠ መሰረት እንደጣሉላቸው ተረዱ::

ቤቱ ትምህርት ቤታቸው እንደነበርም አመኑ:: የሥራን ክቡርነት ፤ የቤት ጽዳት ጉዳይ አሳሳቢ እንዳይሆንባቸው አድርጓቸዋል፤ ሥራን ሳይመርጡ መስራትን አለማምዷቸዋል:: ከሁሉም በላይ ለዛሬ መሰረት የሆናቸውን የኤሌክትሮኒክስ ሥራን እንዲያውቁት አስችሏቸዋል:: ማለትም ቀጣሪያቸው የሌላ ሙያ ባለቤት ቢሆኑም በቤት ውስጥ የአካባቢው ሰው በሙሉ የኤሌክትሮኒክስ መሳሪያዎች ሲበላሽባቸው ይሰሩላቸዋል:: ጎን ለጎንም እርሳቸውን ያሰሯቸዋል:: ይህ ደግሞ አቶ አያሌውን ከቴክኖሎጂው ጋር እንዲተዋወቅ አድርገዋቸዋል::

አቶ አያሌው አዲስ ነገር መሞከር የሚወዱ በመሆናቸው ከጭንቀት ልገላገል በሚል ከተመቻቸው ቤት መውጣት ፈለጉ:: ግን መንስኤ የሆናቸው አንድ ነገር ነው:: ይህም የአሰሪያቸው ጉብዝናቸውን አላደንቅም ማለት ነው:: በተደጋጋሚ የደረጃ ተማሪ ቢሆኑም አድናቆታቸውን አልቸሯቸውም:: ይልቁንም ‹‹በክፍል ውስጥ ሁለት ተማሪ ነበር አንደኛው በለጠህ አንተ ምርጫ ስለሌለ ሁለተኛ ወጣህ›› ይሏቸዋል:: ይህ ደግሞ እጅጉን ያማቸው ነበርና አክስቴ ታማለች በሚል ሰበብ ደብዳቤ

ማህበራዊ

# የሕይወት ገጽታ



**ሙስና ሲስተም እንጂ ሌላ አይደለም። ማንም ባለስልጣንም ሆነ አመራር ያለ ህግ ክፍተት አይሰራም። ሕጉን ተጠቅሞ ክፍተቱን አይቶ በአሰራር ውስጥ አልፎ አገርን ሊሰርቅ ይችላል**

በመጻፍ በእርሳቸው ፖስታ ሳጥን ቁጥር አስገብተው ከቤት እንዲወጡ ሆኑ።

ኑሯቸውን በትምህርት ቤት ያወቋቸው ጓደኛቸው አቶ እያሱ ቤት አደረጉም። አቶ ኢያሱ ደግሞ ከሰዎች ጋር መግባባት የሚችሉና ብዙ የሚያቋቸው ሰዎች ያሏቸው በመሆናቸው መርካቶ ብርሃን ቁርስ ቤት አስቀጠረዋቸው በአስተናጋጅነት ሥራ ጀመሩ። ከካሳንቺስ ተነስተው መርካቶ ድረስም ሌሊት በመነሳት በእግራቸው እየሄዱ ቢሰሩም ይህ ሁኔታ ከባድ ፈተና እንዲያጋጥማቸው አድርጓቸዋል። በዚህም የሥራ ቦታ ለመቀየር ተገደዱ። አንድ ዓመት ከፈተናው ጋር እየታገሉ ቆይተውም ሥራውን አቆሙትና በቀላሉ ሰርተው የሚገቡበትን አማራጭ ፈለጉ። ይህም የሊስትሮ ሥራ ሲሆን፤ ከጃንሜዳ እስከ ቅድስት ማሪያም ቤተክርስቲያን ድረስ እየተዘዋወሩ ከትምህርታቸው ጎን ለጎን መሥራታቸውን ቀጠሉ።

ይህንን ሁኔታ የተመለከቱ በአዲስ አበባ ከተማ ታዋቂ የነበሩት የአየለ ፎቶ ቤት ባለቤት አቶ አየለ በራቸውን ክፍት አደረጉላቸውና ጃንሜዳ አካባቢ በሚገኘው ቡና ቤታቸው በአስተናጋጅነት ቀጠሯቸው። ይህ እድል ደግሞ ለስድስት ወር ያህል ሲሰሩበት የቆዩትን ሊስትሮ ካማስቆሙም ባሻገር ሌላ መልካም አማራጭ ይዞላቸው ብቅ አለ። በግብርና ሚኒስቴር ውስጥ የሚቀጠሩበትን ሁኔታ አመቻቸላቸው። በ30 ብር ደሞዝ በተላላኪነት ተቀጥረውም የመንግስት ሰራተኝነቱን እንዲለማመዱት ሆኑ።

በመስሪያ ቤቱ በመዝገብ ቤት ሰራተኝነት ያገለገሉ ሲሆን፤ ከ10 ዓመት በላይ በቦታው ቆይተዋል። ሆኖም በተቋሙ የቁጥጥር ኮሚቴ የሚባል ሲቋቋም እርሳቸው የቁጥጥር ኮሚቴው ጸሐፊ በመሆናቸው የተነሳ ነገሮች የተለየ ችግር ፈጠሩባቸው። በዚህም ወደሌላ ቦታ እንዲመደቡ ውሳኔ ተላለፈ። ሆኖም ግን እርሳቸው አጋጣሚዎችን መጠቀም ይችላሉና ነገሩን ውሳኔውን አስቀየሩት። ደርግ ሊወድቅ ትንሽ ዓመታት ሲቀረው የውጪ ኢኮኖሚ ትብብር ሚኒስቴር የሚባል ተቋም በመመስረቱ እዚያ የሚገቡበትን ሁኔታ አመቻቹ። መጀመሪያ የመዝገብ ቤት ሰራተኛ በመሆን ከዚያም ኃላፊ በመሆንና በመቀጠል የጠቅላላ አገልግሎቱን ጨምረው በመስራት ለስድስት ዓመት ያህል አገለገሉ። ከዚህ ጎን ለጎንም ትምህርታቸው እንዳለ ሆኖ የሙያና መደበኛ ትምህርት የሚባል በወጣቶች የተጀመረ እንቅስቃሴ ነበርና ለስድስት፣ ስምንትና 12ኛ ክፍል የወደቁ ተማሪዎች የመደገፍና የማስተማር ሥራን በማስተባበር ያከናውኑ ነበር።

አቶ አያሌው ለትምህርት በሄዱበት ከአገራቸው ውጪ ብዙ ሰርተዋል። ሆኖም የአገራቸው ጉዳይ ያንገበግባቸዋልና እዚያ ያለውን ሥራ ጭምር ትተው በመምጣት ካንፓኒ ጭምር ከፍተው ሲንቀሳቀሱ ቢቆዩም ስራቸው ያልተመቻቸው ሰዎች ዳግመኛ ከአገራቸው እንዲወጡ አደረጓቸው። ስለዚህም የአውስትራልያና የኒውዝላንድ ዜግነት ስላላቸው ከአገራቸው ሌላ ሚስት አግብተው ወደ አሜሪካ ተመለሱ። በዚያም ልዩ ትኩረታቸውን መጽሐፍ መጻፍ ላይ በማድረግ ሁለት መጽሐፍትን ለንባብ አበቁ።

## ባህር ማዶ የተሸገረው ሥራ

ቀጣዩ ሥራቸው ባህር ማዶ የተሸገሩበት ሲሆን፤ ለትምህርት በሄዱበት ቀርተው ከአውስትራልያ ወደ ኒውዝላንድ በማቅናት የሰሩበት ነው። ድርጅቱ ኮንቴክ ግሩፕ ኢንተርናሽናል ሲባል በኮምፒውተር ሳይንስ ፕሮግራሚንግ ሰራተኝነት ያገለገሉበት ነበር። ከኒውዝላንድ ወደ አውስትራልያ ተመልሰው ደግሞ ሎካትሪክስ ኢንተርናሽናል ፒቲ ሊተድ በሚባል ድርጅት ውስጥ ሶፍትዌር ዶቨሎፐር በመሆን አገልግለዋል። በዩኒውካስል ዩኒቨርሲቲ የፕሮግራም ሲስተም የተማሪዎች ረዳት ሆነውም ሰርተዋል።

ከዓመታት ቆይታ በኋላ ደግሞ የኒውዝላንድ ዜግነት ያላት ሚስት አግብተው የዚያን ዜግነት አግኝተው እንደልባቸው እየተዘዋወሩ እንዲሰሩ ሆኑ። ስለዚህም የእርሳቸው የሥራ ቦታ ኒውዝላንድና አውስትራልያ ላይ ያረፈ ሆነ ። አውስትራልያ ላይ ራሳቸውን ወደማስተዳደሩ እንዲገቡ ያገዛቸውም እንደልብ መዘዋወር መቻላቸው ነው። ከሰሯቸው ሥራዎች አንዱ ቴሌኮም ላይ የሚሰራ ካንፓኒ ውስጥ ተቀጥረው ለዓመታት የሰሩበት ሲሆን በሶፍትዌር ቴስት ኢንጅነርነት አገልግለውበታል። ከዚያ ከአምስት ዓመት የሥራ ላይ ቆይታ በኋላ በአንድ ጉዳይ ባለመስማማታቸው የተነሳ «አርጅቷል» በሚል ከሥራ ተሰናበቱ።

ሥራውን እንዲያቆሙ ያደረጋቸው የማርጀት ጉዳይ ሳይሆን ሀቀኝነታቸው ነበር ። እርሳቸው እንደሚሉት፤ መነሻው ድርጅቱ አንድ የስራ ፈቃድ (ላይሰንስ) ለአንድ ኮምፒውተር የሚል ስምምነት አድርጓል። ይህንን ግን ለ100 ኮምፒውተር ካልተጠቀምኩ አለ። ፊርማውን የሚያረጋግጡት ደግሞ የሶፍትዌር ቴስት ኢንጅነሩ እርሳቸው ናቸው። እናም አይሆንም ብለው ከለከሉ። በዚህም ሌላ መስሪያ ቤት ለመቀጠር እንኳን አልቻሉም ነበር። ምክንያቱ ደግሞ የስራ ልምዳቸው ታይቶ የሰሩበት መስሪያ ቤት ሲደወል «ከሰርክል ውጪ ማሰብ አይችልም» ይሉባቸዋል።

በምንም ጉዳይ ተስፋ ቆርጠው የማያውቁት ባለታሪካችን፤ ሁኔታውን መከላከል በሚችሉት መልኩ ሁሉ አከናውነው መግቢያ መስሪያ ቤታቸውን አመቻቹ። ሥራው አየር መንገድ ውስጥ የተቀጠሩበት ሲሆን፤ ደንታ ( Dubai national Airline Transite Association) ይባላል። የዱባይ ካንፓኒ ነው። ዋና ሥራቸው ኬተሪንግ ሰርቪሱ ላይ ከቀረጥ ነጻ (ዲዩቲ ፍሪ) የሚገቡ እቃዎችን ቁጥጥር ማድረግና በኮምፒውተር መመዝገብ ነበር። ኮቪድ እስኪገባ ድረስም በቦታው ላይ አገልግለዋል። ዛሬ ደግሞ በአውስትራልያ ሆነው ከትምህርታቸው ጎን ለጎን የራሳቸውን ሥራ ይሰራሉ። አንዱ የኢትዮጵያ ቡናን ማቅረብ ሲሆን፤ ሌላው እንደ ፋስት ፉድ አድርገው የጀርመን ባህላዊ ሶሴጅን በዳቦ አድርገው ይሸጣሉ።

## የአገር አበርክቶ

ለአቶ አያሌው ሁልጊዜ አገር ትቀድማለች። በየጊዜውም በሥራቸው ሁሉ እርሷን ሳያስታውሱ ተኝተው አያድሩም። በኒውዝላንድም ሆነ በአውስትራልያ እያሉ በሚሰሯቸው ትልልቅ ሥራዎች ውስጥ ለአገሬ ምን ይጠቅማል የሚል ነገርን ያስባሉ። በዚህም ብዙ ነገሮችን ሰርተው አገር ውስጥ የሚተገበርበትን ሁኔታ ይፈጥራሉ። ለምሳሌ የኤሌክትሮኒክስ ላይብረሪ ማኔጅመንት ሲስተምን በአገር ውስጥ እንዲተገበር ያስቻሉት በኒውዝላንድ አገር ተቀጥረው በሚሰሩበት ተቋም ውስጥ ሶፍትዌሩን dere አማርኛ ተርጉመው በመስራታቸው ነው።

ነገሩ እንዲህ ነው ኒውዝላንድ ሆነው በሚሰሩበት ወቅት ጃፓኖች የላይብረሪ አጠቃቀማቸውን ለማዘመን ሲሉ ሶፍትዌር አሰሯቸው። እርሳቸው በእንግሊዝኛ የሰሩትን በጃፓንኛ ተርጉመው ተግባራዊ አደረጉት። እናም የአገራቸውን ችግር በቅርበት ያውቁታልና ወደ አማርኛ ተረጎሙት። ይህ የተተረጎመ ሶፍትዌርም በመጀመሪያ በአንድ በካናዲያን ዜጋ አማካኝነት ተገዝቶ ጎንደር ዩኒቨርሲቲ ገባ። ይህቺው ሴት በቀጣይ ወደ ጅማ ዩኒቨርሲቲ አምርታ ነበርና በዚያም የሚገባበትን ስርዓት ፈጠረች። በመጨረሻ በብሪቲሽ ካውንስል አማካኝነት በ 300 ሺህ ብር ተገዝቶ ፒያሳ አካባቢ በነበረው ቤተመጽሀፍት (ላይብረሪ) ውስጥ ሲተገበር ቆየ። በኋላም ትምህርት ቤቱ ወደ ኢንባሲው ሲገባ ለወመዘክር (Ethiopian national Archive) ተሰጠ። አሁን ወመዘክር እየተጠቀመበት እንደሚገኝ አጫውተውናል።

ሌላው አቶ አያሌው ለአገራቸው ያበረከቱት ነገር የእጅ ስልክ(ሞባይል ) ገንዘብ መሞያ ካርድ የሚፋቀውን ወደ ወረቀት የሚቀየርበትን መንገድ የፈጠሩበት ነው። ምክንያታቸው ደግሞ ሁለት ነገር ሲሆን የመጀመሪያው ካርዱ ሲፍቁት የተለያዩ በሽታዎችን ማምጣት መቻሉን በማረጋገጣቸው ፤ ሌላው ደግሞ ከህትመት ጋር ተያይዞ አገሪቱ እያወጣች ያለውን የውጪ ምንዛሪ ወጪ ለመቀነስ አስበው ነው። ስለዚህም ጨረታ ወጥቶ ተወዳድረው አሸነፉ። ሆኖም ጥቅማቸው በተለያየ መልኩ የቀረባቸው ሰዎች ሊያስቀምጧቸው አልቻሉም። በሕይወታቸው ላይ አደጋ ለማድረስ ሁሉ ፈለጉ። በዚህም የከፈቱትን ተቋም ይዘጋልኝ ብለው አመልክተው ሳይዘጋላቸው ትተው ከአገር ወጡ።

እንደ እርሳቸው እምነት ሀሳቡ እያሸነፈ ሲመጣ የሚበላው ገንዘብ ይቀራል። ትርፉ አገር እንጂ ሌቦች አይሆኑም። እናም ብልጫውን ላለማመን የጨረታውን ሰነድና የመጡ መሳሪያዎችን ደበቁት። ይባስ ብሎም በየስድስት ወሩ የሚወጣው 500 ሺህ ካርድ ለሶስት ዓመት እንዲሆን ተደርጎ ጨረታው ተሰረዘ። አምስት መቶ ሺህ ብራቸውን ይዘው ጠብቁ ይከፈታል እያሉ ያጓጓቸው ገቡ። በዚህም ሳይበቃቸው ያሳድዷቸው ጀመር። ስለዚህም «ከመሞት መሰንበት» ብለው የሚወዷትን አገራቸውን ትተው ዳግመኛ ወደውጪ ሄዱ። ቴክኖሎጂውን ስላዩትና መረጃዎቻቸውን በእነርሱ እጅ ስለሆነ እርሳቸው ከወጡ በኋላ ወደ ተግባር ገቡበት። ይህንን ሲመለከቱም «ከብሩ በላይ አገሬ ተጠቅማለችና ደስ ብሎኛል» ይላሉ።

አገራቸውን ትተው ቢሄዱም ያልተዋቸው ነገሮች ነሩር። ይህም የከፈቱትን ካምፓኒ ስላልዘጉት የስራ ግብር ተብሎ ከነቅጣቱ 700 ሺህ ብር እዲከፈሉ ተወሰነ። ይህንን ያህል ገንዘብ ከፈል መባል ትክክል አይደለም ቢሉም ማንም ሊሰማቸው አልቻለም። ሳይሰሩና ጁፒተር ከተባለ ድርጅት ያመጡትን ሪጅስተር ማሺኑን በደብዳቤ መልሰው ባሉበትም ነበር ክፈል የተባሉት። ስለዚህ አገራቸውንን ትተው ወጡ። በድጋሚ ሰባት ዓመት ቆይተው መስራት ፈልገው ጠቅላይ ሚኒስቴር ዶክተር ዐብይ አህመድ አገራችሁን በእውቀትና በጉልበት እንዲሁም በገንዘባችሁ አገልግሉ ሲሉ እሺ ብለው ቢመጡም ይህ ጉዳይ አላፈናፍን ስላላቸው ተመለሱ። ዳግመኛ ወደአገራቸው የሚመልሳቸው ጉዳይ አገኙ። ከመሄዳቸው በፊት በወቅቱ አመልክተው ስለነበር 700 ሺህ ብር እዳ በኮቪድ ምክንያት ከፍተኛ የግብር እዳ ያለባቸው ሰዎች ተለይተው ሲሰረዝላቸው እርሳቸው አንዱ ሆኑ። በደረሳቸው ደብዳቤ መሰረት ነጻ መሆናቸውን አረጋገጡ። ይህ ደግሞ ለአገራቸው ለመስራት እንዲንደረደሩ አደረጋቸው።

ለአገራቸው አዲስ መሰረት ለመጣልም ይፈልጋሉ። አንደኛው ከሸንኩርት ኬሚካል መስራት ሲሆን፤ ይህንን በውጪ አገር በሚኖሩበት ወቅት አድርገውታል። ሌላው ደግሞ ከቡና ወደ አራት አይነት ምርት መስራት ችለዋልና አገራቸው ላይ መከወን ይሻሉ። በተጨማሪም መንግስት አቅዶት ያለውን የውጪ ባንኮችን ወደ አገር ውስጥ ማስገባት ጉዳይ ላይ መሳተፍ ይፈልጋሉ። ለዚህ ደግሞ የተመቻቸ ሁኔታ እንዳላቸው ይናገራሉ።

ለሁለተኛ ድግሪያቸው የያዙት ፕሮጀክት በphysical fiat currency (PFC) and Digital fiat Currency ( DFC) እንዲሁም ከዲጅታል ባንኪንግ ጋር የሚያያዝ መሆኑ አንዱ በቴክኖሎጂ የታገዘ ሥራ ለማቅረብ የሚያስችላቸው ነው። እናም ይህንን ፕሮጀክታቸውን ለመስራት አንድ ሚሊዬን ዶላር ጠይቀዋልና ሲጨርሱት ባንክ ስርዓቱ ላይ ትልቅ አቅም እንደሚፈጥር ያምናሉ አገራቸውንም እንደሚጠቅሙበት አጫውተውናል።

## መልዕክት

ከሙስና ጋር በተያዘ የመጀመሪያ መልዕክታቸውን ያስተላልፋሉ። ሙስና ሲስተም እንጂ ሌላ አይደለም። ማንም ባለስልጣንም ሆነ አመራር ያለ ህግ ክፍተት አይሰራም። ሕጉን ተጠቅሞ ክፍተቱን አይቶ በአሰራር ውስጥ አልፎ አገርን ሊሰርቅ ይችላል። እናም ይህንን ማጥፋት የሚቻለው ሰዎችን በመያዝና በማሰር ብቻ ሳይሆን መንገዱን (ሲስተሙን) በማስተካከል ነው። ለሙስና መፍትሄው ሲስተሙ እንዳያሰርቅ ማድረግ ሲቻል ብቻ ነው። ከዚያም በሻገር የተዘረፈውን ገንዘብ ለሕዝብ ጥቅም መዋል ሲቻል በራሱ ጊዜ ሌባው ሥራውን ያቆማል።

መንግስት ለአገር ጥቅም ሲባል የማያደርገው ነገር የለም። ጥቅሙ ግን በጥልቀት መመርመርና ሕዝብን የያዘ መሆን አለበት። ምክንያቱም አንዳንድ ጊዜ በምሁራን ብቻ ነገሮች ሲመረመሩ ህዝብ የማይረዳበት አጋጣሚ ይፈጠራል። እናም ሕዝብ አውቆት ጸሐይሞቆት ፤ ጠቃሚነቱ ተረጋግጦ ነገሮች መከወን ይኖርባቸዋል። ሕጎች መከበርም አለባቸው። በተለይም ከውጪ የሚገቡ ነገሮች ላይ መለሳለስ ማሳየት አይገባም። ለአገር ጥቅም ሲባል ጥብቅና ጥልቅ ምርመራ ማድረግ ያስፈልጋል ሌላው ምክረሀሳባቸው ነው። እኛም ምክሩ መልካም ነውና እንመልከተው በማለት ለዛሬ የያዝነውን ሀሳብ ቋጨን።

# ባህልና ቱሪዝም

# ለቱሪዝም ኢንዱስትሪው ውጤታማነት- የስልጠና ኢንስቲትዩቱ ድርሻ

**ዳግም ከበደ**



ኢትዮጵያ የታሪክ፣ ተፈጥሮ፣ ቅርስና የብዝሃ ባህል ባለቤት ነች። ከእነዚህ የቱሪዝም መስህብ ሀብቶቿ የምታገኘው ኢኮኖሚያዊ ጥቅም ግን አነስተኛ መሆኑን መረጃዎች ያሳያሉ። ከጎረቤት አገር ኬኒያ ጋር ሲነጻጸርም ኢትዮጵያ ከዘርፉ የምታገኘው ገቢ ዝቅተኛ ነው:: ለአብነትም በኢትዮጵያ ከፍተኛ ነው ተብሎ በቀዳሚነት ከተመዘገበው ከ920 ሺህ በላይ ቱሪስት ፍሰትና የ3ነጥብ 5 ቢሊዮን ዶላር ገቢ ጋር ሲነፃፀር የኢትዮጵያ አፈጻጸም የኬኒያን የሩብ ዓመት አፈፃፀም እንደሚያህል መረጃዎች ያመለክታሉ። የቱሪስት ፍሰቱ በእጅጉ አነስተኛ ከመሆኑ በተጨማሪ ለጉብኝት የሚመጣውን ቱሪስት ቆይታ ለማራዘም የሚደረገው ጥረት ደካማ መሆኑ ይገለጻል።

ቱሪስቶች በኢትዮጵያ ያላቸውን ቆይታ እንዳያራዝሙ፤ ይዘው የመጡትን ገንዘብ መልሰው ወደ አገራቸው እንዲሄዱ ከሚያስገድዱ ምክንያቶች አንዱ በዘርፉ የተሰማሩት ባለሙያዎችና የአገልግሎት ጥራት ጉድለት መሆናቸው ይጠቀሳል። የሆቴል ሙያተኞች፣ የአስጎብኚዎችና ሌሎች ተያያዥ ሙያዎች ላይ የተሰማሩ አገልግሎት ሰጪዎች ብቃት(ፕሮፌሽናል) እና የአገልጋይነት ስሜት(ሆስፒታሊቲ) በሚፈለገው ደረጃ አለመሆን በችግርነት ይጠቀሳሉ።

የቱሪስት መዳረሻ ሥፍራዎችንና መስህቦችን ጠንቅቆ አለማወቅና በመረጃ በተደገፈና ቱሪስቱን በሚስብ መልኩ ማስጎብኘት አለመቻል ቱሪስቱ የቆይታ ጊዜውን እንዳያራዝም ከሚያደርጉት ምክንያቶች መካከል ይጠቀሳል:: የዓለም የኢኮኖሚ ፎረም ጥናትም ይህንኑ ነው ያረጋገጠው:: የቱሪዝም ኢንዱስትሪው በሚፈልገው ልክ ባለመሰራቱ ኢትዮጵያ ውስጥ የቱሪስቶች ቆይታ አጭር እንደሆነና ገንዘባቸውንም ይዘው እንደሚመለሱ ጥናቱ አመላክቷል::

ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ደግሞ በዘርፉ ላይ ለውጦች መታየት ጀምረዋል:: ዘርፉን በማነቃቃት ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ጥቅም ለማሳደግ መንግስት ሰፋፊ ፕሮጀክቶችን ቀርፆ እየሰራ ይገኛል።እየተከናወኑ ካሉ ተግባራትም አንዱ የሙያ ማሰልጠኛ ተቋማትን ማጠናከር እና የጥራት ደረጃቸውን ከፍ ማድረግ ነው። መንግሥታዊና መንግሥታዊ ካልሆኑ ማሰልጠኛ ተቋማት ተመርቀው የሚወጡ ባለሙያዎች በንድፈ ሃሳብ የሚያገኙት እውቀትም ሆነ በተግባር የሚላበሱት ክህሎት የተሟሉ እንዲሆኑ የሚያስችል ነው።

የቱሪዝም ዘርፍ ባለሙያዎችን ለበርካታ አስርት ዓመታት በማፍራት የሚታወቀው የቱሪዝም ማሰልጠኛ ኢንስቲትዩት ከላይ ካነሳናቸው ሀሳቦች ጋር የሚሄድ የምክክር መድረክ በቅርቡ አዘጋጅቶ ነበር። የምክክር መድረኩ በዋናነት ቱሪዝም እንዲነቃቃ፣ ጎብኚዎች ወደ አገሪቱ እንዲመጡና ከዚያም ባለፈ ቆይታቸውን ማራዘም እንዲችሉ ባለሙያውን በብቃትና በጥራት ማፍራት በሚያስችሉ ጉዳዮች ላይም የመፍትሄ አቅጣጫ አመላክቷል። ኢንስቲትዩቱም የማሰልጠኛ ኢንስቲትዩቱን የስልጠና ጥራት ለማስጠበቅ አዲስ በተዘጋጁ የሥነምግባርና የአሰራር ሥርዓት ማኑዋሎች ላይ ትኩረቱን አድርጎ ከባለድርሻ አካላት ጋር በመወያየት ግብአት የሚሆኑ መረጃዎችን መሰብሰብ ችሏል::

በምክክር መድረኩ ላይ የተገኙት የቱሪዝም ማሰልጠኛ ኢንስቲትዩት ዋና ዳይሬክተር አቶ ጌታቸው ነጋሽ እንዳሉት፤ መንግሥት ለቱሪዝም ዘርፉ ልዩ ትኩረት ሰጥቷል፤ አዳዲስ የቱሪስት መዳረሻዎችን ከማስፋፋት ጎን ለጎን ዜጎች በዘርፉ በተመረጡ ሙያዎች ብቃት ያለውና የተሟላ የክህሎት ስልጠና አግኝተው፣ የኢኮኖሚው እንቅስቃሴ የሚፈጥረውን የስራ ዕድል በመጠቀም የሥራ ገበያውን እንዲቀላቀሉ ለማስቻል ከፍተኛ ጥረት በማደረግ ላይም ይገኛል:: የቱሪዝምና ሆስፒታሊቲ ኢንዱስትሪው እንዲዘምን እና አገልግሎቱም እንዲሻሻል፣የዜጎች ዋንኛው የገቢ ምንጭ እንዲሆን፣ለወጣቶች ሰፊ የስራ እድል እንዲፈጥርላቸው፣ ከሁሉም በላይ ደግሞ እንዱስትሪው የሰለጠነ፣ በቂና ብቁ የሰው ሀይል እንዲያገኝ በማድረግ ረገድ የሁሉም ባለድርሻ አካላት ተሳትፎና የስራ ትብብር ይጠይቃል::

“አንስቲትዩቱ፣ በመንግስት የተሰጠውን ተልዕኮ በብቃት ለመወጣት፣ የሚያስችለውን ተቋማዊ የአደረጃጀትና የአሰራር ማሻሻያዎች በማድረግ በእንቅስቃሴ ላይ ይገኛል” ያሉት ዋና ዳይሬክተሩ፣ ላለፉት በርካታ ዓመታት በሆቴልና ቱሪዝም ዘርፍ በርካታ ባለሙያዎችን ማፍራቱን ይጠቅሳሉ:: በምርምርና ማማከር መስኩም እንደዚሁ የበኩሉን አስተዋጽኦ በማበርከት አንጋፋና ስመጥር ተቋም መሆኑን ገልጸዋል::

እሳቸው እንዳሉት፤ በሆቴልና ቱሪዝም ዘርፉ፣ ሙያን ማዕከል ያደረጉ የክህሎት ስልጠናዎችን የሚሰጡ የስልጠና ተቋማት ቁጥር ከጊዜ ወደ ጊዜ እያደገ የመጣ ቢሆንም፣ ከሀገሪቱ የሆቴል ኢንዱስትሪ መስፋፋት ጋር ተያይዞ አሁንም በገበያ ላይ ሰፊ የሆነ የሰለጠነ የሰው ሀይል እጥረት ጎልቶ ይስተዋላል::የስልጠና ተቋማት በርካታ ባለሙያዎችን በማሰልጠን በየጊዜው ሙያተኞችን ቢያፈሩም ኢንዱስትሪው የሚፈልገውን የሰው ኃይል ማሟላት አልተቻለም::

“አሁን በዘርፉ የሚታየው የሰው ኃይል አቅርቦትና ፍላጎት ያለመጣጣም ችግሩን በዘላቂነት ለመፍታት ሲባል የቱሪዝም ማሰልጠኛ ኢንስቲትዩት በሀገራችን የዘርፉ የልህቀት ማዕከል ሆኖ ለማገልገል በስፋት አቅዶ እየሰራ ይገኛል” ያሉት አቶ ጌታቸው፣ ኢንስቲትዩቱ የልህቀት ማዕከል ይሆናል ሲባል የላቀ ስልጠና፣ የላቀ የምርምር ሥራ እና የላቀ የማማከር አገልግሎት ይሰጣል ማለታቸው እንደሆነም ይገልፃሉ::

እንደ እሳቸው ገለጻ፤ ኢንስቲትዩቱ ከባለድርሻ አካላት ተሳትፎና ትብብር ውጭ፣ የቱንም ያህል ቢሮጥ በዕቅድ ይዞ የተነሳውን ትልቅ ሀገራዊ ግብና ዓላማ ብቻውን ማሳካት አይችልም። ስለሆነም የሆቴልና ቱሪዝም ኢንዱስትሪው፣ በሙያ ደረጃ ዝግጅት፣ በስርዓተ ስልጠና ቀረጻ፣ በትብብር ስልጠና፣ በብቃት ምዘና ሂደት፤ በጥናትና ምርምር፣ በባለሙያ ልውውጥ እና በመሳሰሉት ጉዳዩች ዙሪያ የላቀ ተሳትፎ እንዲኖረው ይፈለጋል::

የምክክር መድረኩ ያስፈለገበትን ዋናው አላማን አስመልክተው አቶ ጌታቸው እንደገለጹት፤ ተቋሙ ቀደም ሲል የጀመረውን ከኢንዱስትሪው ጋር ተቀራርቦ የመስራት ባህሉን የበለጠ በማጎልበት ወደፊት ጠንካራና ዘላቂ የስራ ቅንጅት ተፈጥሮ ውጤትን ታሳቢ ያደረጉ ስራዎችን ለመስራት፣ ብቁና በተግባር የተፈተነ የቱሪዝም ባለሙያ ለማፍራት የሚያስችል ምቹ ሁኔታን መፍጠር ነው። በመሆኑም በዘርፉ የሰው ሀይል ልማት ዙሪያ በትብብርና በመደጋገፍ ስሜት የሚከናወኑ ተግባራትን በመለየት በቀጣይ ዕቅድን መሠረት ያደረጉ ስራዎችን መስራት ይጠበቃል።

አቶ አሸናፊ ሙሉጌታ በቦሌ የአምባሳደር ሆቴል ማኔጂንግ ዳይሬክተር ሆኖ እየሰራ ይገኛል:: ትምህርቱን በሆቴልና ቱሪዝም ማሰልጠኛ ኢንስቲትዩት ነው የተከታተለው። በዚሁ ሰልጥኖ በተመረቀበት ኢንስቲትዩት በተዘጋጀው መድረክ ላይ ተካፍሏል:: እኛም በስልጠና ጥራትና የትብብር ስልጠና ዙሪያ ሀሳቡን እንዲያካፍለን ጠይቀነው፤ ኢኒስቲትዩቱ በዘርፉ ልምድ ካላቸው ባለድርሻ አካላት ጋር ውይይት ማድረጉና ግብአት መሰብሰቡ ለስልጠና ጥራትና ብቁ ባለሙያዎች ለማፍራት ያግዛል ብሏል::

“በቱሪዝም ዘርፍ ሥርአተ ትምህርት የሚቀርፁ ባለሙያዎች እያንዳንዱን የዘርፉን ኦፕሬሽን የሚያውቁና በውስጡ ያለፉ መሆን ይኖርባቸዋል ብዬ አምናለሁ” የሚለው አቶ አሸናፊ፤ ስርዓተ ትምህርቱ በዘርፉ ልክ ከተቀረጸና ተማሪዎች የተግባርም ሆነ የፅንሰ ሃሳብ ስልጠና ከወሰዱ ገበያው ላይ ተፈላጊነታቸው እንዲጨምር ይረዳል ሲል አስተያየቱን ሰጥቷል። የንድፈ ሀሳብና የተግባር ትምህርትን ያጣጣመ የአሰራር ስርዓት መዘርጋት አስፈላጊ መሆኑ በመጥቀስም ከኢንዱስትሪው አንቀሳቃሾች ሆቴሎች፣ ቱር ኦፕሬተሮችና መሰል ተቋማት ጋር በቅንጅት መስራት እንደሚያስፈልግም ጠቁሟል።

ኢንስቲትዩቱ የስልጠናና የቅበላ አቅሙን ለማሳደግ ሪፎርም እያካሄደ መሆኑ የሚያበረታታ ነው የሚለው አቶ አሸናፊ፣ ስኬታማ ሪፎርም ለማካሄድም የኢንስቲትዩቱን ምሩቃን ቀጣሪ ከሆኑ የሆቴል ፣ የቱር ኦፕሬተርና ሌሎች ባለ ድርሻ አካላት ጋር ምክክር ማካሄዱን አድንቋል። ከኢንስቲትዩቱ ተመርቀው ወደ ስራ የሚሰማሩ ሰልጣኞች ያሉባቸው ክፍተቶች፣ መጨመር ያለባቸውና ተገቢ አይደሉም ያሏቸውን ኮርሶች እንዲሁም ለተግባራዊ ትምህርት እና በቋንቋ ብቃት ዙሪያ ሰፋ ያሉ ሃሳቦችን አንስቷል።

ከመድረኩ የተነሱ ሀሳቦችንም በመውሰድ ወደ ተግባር እንደሚለውጡ ተስፋ እንደሚያደርግ የተናገረው ማኔጂንግ ዳይሬክተሩ፣ አዲስ በሃላፊነት የተሾሙትን የኢንስቲትዩቱ የስራ ኃላፊዎች የትምህርት ተቋሙን ለመለወጥ እያከናወኑ ያሉት ተግባራት የሚያበረታታ መሆኑንም ጠቁሟል።

ኢንስቲትዩቱ እንዲህ ዓይነት መድረኮችን በማዘጋጀት ግብዐት መውሰዱ ለቱሪዝም ኢንዱስትሪው ዕድገት ጉልህ ሚና እንዳለው አንዳንድ የመድረኩ ተሳታፊዎችም ገልፀዋል:: በምክክር መድረኩ የተሳተፉ አብዛኞቹ ተሳታፊዎች ከኢንስቲትዩቱ የተመረቁና በተለያዩ ተቋማት ውስጥ ኃላፊ ሆነው እየሰሩ ያሉ መሆናቸውንም ሀሳባቸውን ከሰጡት ለመረዳት ችለናል:: ይህም ኢንስቲትዩቱ ባለሙያዎችን በማፍራት በዘርፉ ያለው ሚና የላቀ መሆኑን ያስገነዝባል::

መረጃዎች እንደሚያመለክቱት፤ የቱሪዝም ማሰልጠኛ ኢንስቲትዩት ይህንን የምክክር መድረክ ከማዘጋጀቱና ከኢንዱስትሪው አንቀሳቃሾች ጋር ምክክር ከማድረጉ አስቀድሞ የስልጠና ጥራትን ለማስጠበቅ የሚያስችሉ የተዘጋጁ አዳዲስ የአሰልጣኞችና የሰልጣኞች የሥነምግባር ማኑዋል እና የሬጅስትራር አሰራር ስርዓት ላይ ከአሰልጣኞች ጋር ውይይት አካሂዷል::

የአሰራር ማንዋሎቹ ተቋሙ በዘርፉ የመሪነት ሚናውን በመወጣት ምሳሌ እንዲሆን የሚያስችሉ መሆናቸውን የኢንስቲትዩቱ ምክትል ዋና ዳይሬክተር አቶ ገዛኸኝ አባተ ይገልጻሉ:: በተለይም አሰልጣኞች ውጫዊና ውስጣዊ ሥነ ምግባርን በመላበስ በተቋሙ ውስጥ ለተማሪዎቻቸው ጥሩ ምሳሌ በመሆን፣ በሀገር ደረጃ ብቃት ያላቸው የቱሪዝም እና የሆቴል ባለሙያዎችን ለማፍራት እንደሚያግዝ አስረድተዋል:: አዲስ የሬጅስትራር አሰራር ሥርዓት መዘጋጀቱ ትክክለኛ የሰልጣኖች መረጃ እንዲኖር ለማድረግ፣ ቀልጣፋ አገልግሎት ለመስጠት ኢንዲሁም ለሚከሰቱ ችግሮች ተጠያቂነትን ለማስፈን ያስችላልም ሲሉ አብራርተዋል::

ቱሪዝም በግሉም ሆነ በመንግስት አካላት ውስጥ በሚገኙ በርካታ ባለድርሻ አካላት ካልተደገፈ ውጤታማ እንደማይሆን የተለያዩ ተሞክሮዎች ያሳያሉ:: በዋናነት ቅንጅት፣ ተግባቦትና ምክክርን የሚሻ ልዩ ልዩ ተቋማትን የሚያሳትፍም መሆን ይጠበቅበታል። በተለይ ዝቅተኛ ገቢ ካላቸው የህብረተሰብ ክፍሎች ጀምሮ በመስኩ የተሰማሩ ልዩ ልዩ አካላትን በማካተት ሁሉን አቀፍ የቱሪዝም እድገት ለማምጣት ምሁራኑ ፖሊሲ፣ ስትራቴጂና ልዩ ልዩ ሳይንሳዊ ምርምሮች ላይ የድርሻቸውን ማበርከት ይጠበቅባቸዋል።

የሆቴል፣ የቱርስት ኦፕሬተርና መሰል ኢንዱስትሪውን የሚያንቀሳቅሱ ተቋማት የተማሩና ለቱሪዝሙ እድገት እርሾ የሆኑ ሙያዎች ላይ እውቀት ያላቸውን ከማሳተፍ ይልቅ በዘመድ አሊያም በሌሎች ጥቅማጥቅሞች ማሳተፍን ምርጫቸው ያደርጋሉ። በእርግጥ ይህ አሰራር በግሉም ሆነ በመንግስት የቱሪዝም መስሪያ ቤቶች ውስጥ የሚታይ መሆኑን የሚያሳዩ በርካታ መረጃዎችን መጥቀስ ይቻላል።

የቱሪዝምን ፅንሰ ሃሳብ የሚያስጨብጡ እንዲሁም የኢትዮጵያን ሃብቶች ለማልማትና ከዚያ ተጠቃሚ ለመሆን የሚያስችል እውቀት የሚያደረጁ የትምህርት ተቋማት እየበዙና በየደረጃው እየተከፈቱ ሲመጡ ከፍተኛ በዘርፉ የተማረ የሰው ሃብት ፍሰት እንደሚመጣ ይጠበቃል። ይህን ተከትሎ ከባለድርሻ አካላት ውይይት በተካሄደ ቁጥር የሚነሳው “የሙያና ፕሮሚካፌሽናሊዝም” ችግር እየተቀረፈ እንደሚመጣ መገመት አያዳግትም።

# ሳምንቱን በታሪክ

## የደርግ የህብረተሰባዊት ኢትዮጵያ አዋጅ

**ዋስልኝ አየለ**

ለሺህ ዘመናት የኖረውን ንጉሣዊ ሥርዓት የገረሰሰው ደርግ ለዘመናት የኖረውን «የፊውዳል» ሥርዓት በሶሻሊዝም (ህብረተሰባዊነት) ሥርዓት ቀየረው። ይህን ያደረገው ደግሞ ንጉሳዊ ሥርዓቱን በገረሰበት በ100ኛው ቀን በዚህ ሳምንት ታኅሳስ 11 ቀን 1967 ዓ.ም ነው።

በዛሬው ሳምንቱን በታሪክ ዓምዳችን 48 ዓመታትን ወደ ኋላ መለስ ብለን በዚህ ሳምንት ታኅሳስ 11 እና 12 ቀን 1967 ዓ.ም የተከናወኑ የደርግ የሕብረተሰባዊት ኢትዮጵያ አዋጅ፣ የዕድገት በሕብረት የዕውቀትና የሥራ ዘመቻ እና ሌሎች የደርግ እንቅስቃሴዎችን እንቃኛለን።

የታሪክ ተመራማሪው ፕሮፌሰር ባህሩ ዘውዴ በዚህ በታኅሳስ ወር አጋማሽ አካባቢ የነበሩ የሕብረተሰባዊት ኢትዮጵያ አዋጅና አጠቃላይ እንቅስቃሴዎች በተመለከተ የሚከተለውን ታሪክ ጽፈዋል።

በ1966 ዓ.ም አጋማሽ ላይ አራተኛ ክፍለ ጦር መሽገው፤ የሀገሪቱ የወደፊት ዕጣ ፈንታ ምን ይሁን ብለው ሲመክሩ፣ ሳይንሳዊ ሶሻሊዝምን በኢትዮጵያ ውስጥ ሰርጎ የማስገባቱ ጉዳይ ከአብዛኛዎቹ ኅሊና እጅግ የራቀ ነበር።

መመሪያቸው ያደረጉት «ኢትዮጵያ ትቅደም» የሚለው መፈክር ግፋ ቢል አገር ወዳድነትን የሚጠቁም ነበር። በታኅሣሥ ወር በአብዛኛው የእድገት በኅብረት ዘማቾችን ለማስደሰት ሲባል ወደ «ኅብረተሰብዓዊነት» ሲኃለምስም ዓላማው ኢትዮጵያዊ ሶሻሊዝምን እንጂ ሳይንሳዊ ሶሻሊዝምን ለማስረፅ አልነበረም። ይሁንና ደርግ ፈራ ተባ ሲል የያዘው የሶሻሊስት ፈር ወደፊት የሚከተለውን የርዕዮተ ዓለም አቅጣጫ አመልካች ነበር።

ያንን ፈር መልቀቁ እያደር አስቸጋሪ ብቻ ሳይሆን የማይታሰብ እየሆነ መጣ። የዚህንም ዋነኛ ምክንያት ለመረዳት ተማሪዎች በኢትዮጵያ አብዮት አመጣጥና ሂደት ላይ የነበራቸውን ወሳኝ ሚና ማጤን ያስፈልጋል። እንደ እውነቱ ከሆነ መለዮ ለባሹ በየካቲት 1966 ያለው በአመዛኙ ከሙያው ጋር የተያያዙ ብሶቶችን ይዞ ነው። የደመወዝ ጭማሪ፣ የኑሮ ሁኔታ መሻሻል፣... ወዘተ ማለት ነው።

ጥቅማቸውን አስከብረው ወደ ካምፓቸው ለመመለስ ሲያስቡ «ወቴ ደሞዟን አስጨምራ ወደ ካምፕ ተመለሰች» የሚለው የተማሪዎችና የሌሎች ሲቪል ወገኖች ጉንተላ፣ ሹፈትና ወቀሳ ነው መለዮ ለባሹን ወደ ፖለቲካው መድረክ የገፋፋው። እያደርም ደርግ ሥልጣን ለመያዝ ብቻ ሳይሆን በሥልጣን ላይ ለመቆየት ከፈለገ እየገነነ ከመጣው ማርክሳዊ ርዕዮት ውጭ አማራጭ ሕዝባዊ አመፅ እንደሌለው እየተገነዘበ መጣ።

ከ1966 እስከ 1968 ድረስ ባሉት ሁለት ዓመታት ደርግ ከዚህ ርዕዮት ጋር ለመተዋወቅ ብቻ ሳይሆን ከማንም ያላነሰ ክህሎት አለኝ ለማለት ያላሰለሰ ጥረት ማድረግ ነበረበት። ሁልጊዜ አንድ እርምጃ ወደፊት ቀድሞ ከሚገኘው የግራ ክንፍ ኃይል ጋር ለመስተካከልና ብሎም ለማለፍ የነበረው ትግልና ጥረት ቀላል አልነበረም፤ ጥረቱም ተሳክቶ በሚያዝያ 1968 ዓ.ም ደርግ የመጨረሻውን ርዕዮተ ዓለማዊ እመርታ በማድረግ፣ የብሔራዊ ዴሞክራሲያዊ አብዮትን በመመሪያነት አወጀ። በዚህ ድርጊቱም እየቀደመ ሲያስቸግረው ከነበረው የግራ ክንፍ የፖለቲካ ቡድን ጋር ተስተካከለ ማለት ይቻላል። ከዚያ የሚቀጥለው እርምጃ ራሱን የሠፊውንና የጭቁኑን ሕዝብ ትግል በግንባር ቀደምነት ለመምራት በታሪክ የታጨ ብቸኛ የፖለቲካ ኃይል አድርጎ ማየቱ ነው።

ይህን አስደናቂ የደርግ የርዕዮተ ዓለም ጉዞ ካሰመረለት አንዱ፤ የግራ ክንፉ ተከፋፍሎ ወደ አብዮቱ መድረክ መውጣት ነው። በተለይም ከሀገር ውጭ የሚገኘው የተማሪው ንቅናቄ አካል አብዮቱ ሲፈነዳ በሁለት አክራሪ ጎራዎች ተሰልፎ ነበር። ኋላ ገሀድ እንደ ወጣው እነዚህ ሁለት ጎራዎች የኢሕአፓና የመኢሶን ድርጅቶች ተከታዮች ነበሩ። እነዚህ ሁለት አንጋፋ የግራ ክንፍ ኅቡዕ ድርጅቶች በተማሪ ድርጅቶች ሽፋን ደጋፊዎቻቸውን ማብዛትና ማጠናከር ተያይዘው ነበር። በአብዮቱ ዋዜማ ሁለቱ ጎራዎች በዓለም አቀፉ የተማሪዎች ድርጅት አወቃቀር ላይ ሳንጃ ቀረሽ ክርክር እያደረጉ ነበር። የኢሕአፓ ወገኖች በአዲስ መልክ የተዋቀረውን ዓለም አቀፍ የኢትዮጵያ ተማሪዎች ፌዴሬሽን ሲደግፉ፣ የመኢሶን ተከታዮች ደግሞ በቁጥጥራቸው ስር የነበረው ዓለም አቀፍ የኢትዮጵያ ተማሪዎች ማኅበር እንዲቀጥል ይሟገቱ ነበር።

በዚህ ሁሉ ውጥንቅጥ ውስጥ ያለው ደርግ «ሕብረተሰባዊት ኢትዮጵያ» ዘመቻውን በተለያዩ ዘርፎች ማጧጧፍ ቀጥሏል።

**«ኢትዮጵያ ትቅደም» ማለት ሕብረተሰባዊነት ማለት ነው። ሕብረተሰባዊነት ማለት ደግሞ የራስን ዕጣ ፋንታ መወሰን መቻል፣ የመሥራት እና ሀብት የማግኘት መብት ማለት ነው።**

ታኅሳስ 11 ቀን 1967 ዓ.ም በደርግ ወታደራዊ ምክር ቤት የሕብረተሰባዊት ኢትዮጵያ አዋጅ ሲታወጅ፤ በነጋታው ታኅሳስ 12 ቀን 1967 ዓ.ም ደግሞ የዕድገት በሕብረት የዕውቀትና የሥራ ዘመቻ አዋጅ፤ በአዋጅ ቁጥር 11/1967 ለህዝብ ይፋ ሆነ።

የዕድገት በሕብረት ዘመቻ ኮሎኔል መንግሥቱ ኃይለማርያም በተገኙበት በጃንሜዳ በይፋ በተጀመረበት ዕለት (ታኅሳስ 12) የነበረውን ሁነት ገስጥ ተጫኔ «ነበር» በተሰኘው መጽሐፉ እንዲህ ያስታውሰዋል።

«ታህሳስ 12 ቀን 1967 የእድገት በኅብረት የዕውቀትና የሥራ ዘመቻ የክተት በዓል በመላ ሀገሪቱ ተከበረ። ለዘመቻው የተዘጋጁ 60 ሺህ ተማሪዎችን የወከሉ የአዲስ አበባ ዘማቾች በአሉን ለማክበር በጃንሜዳ ተሰለፉ። ሰልፉን ለመጎብኘት እና በአሉን በጋራ ለማክበር ብርጋዴል ጀነራል ተፈሪ በንቲና ሻለቃ መንግስቱ ኃይለማርያም በስፍራው ተገኝተው ነበር። ሰልፈኛው በየተመደበበት የዘመቻ ቀጠና በረድፍ እንደቆመ ጃንሜዳን ከምእራባዊ ጫፍ እስከ ምስራቃዊ ጫፍ ሞልቶት ነበር።»

ፍቅረሥላሴ ወግደረስ ደግሞ «እኛና አብዮቱ» በሚለው መጽሐፋቸው ሁነቱን ሲገልጹ፤ «መለዮአቸውን በማውለብለብ በሆታና በጭፈራ «ቪቫ መንግሥቱ! «ቪቫ መንግሥቱ!» እያሉ ሲቃ እየተናነቃቸው በመጮህ አለፉ፤ አንዳንዶቹ የመንግሥቱን እጅ ለመጨበጥ ወደ ትሪቡን የሚመጡ ነበሩ!»

**በዚሁ ዕለት ዘማቹ፡-**
**ፋኖ ተሰማራ**
**ፋኖ ተሰማራ**
**እንደ ሆቺ ሚኒ እንደ ቼ ጉቬራ!**
**በደስታ በዕልልታ እንደሸኘናችሁ**
**በሳቅ በፈገግታ እንቀበላችሁ**
**በህይወት ግቡ በህይወት**
**ዘመቻ የምትሄዱ ስዕድገት በህብረት!**

እየተባለ እስከ መስቀል አደባባይ ድረስ ሰልፍ ተደርጓል። ይህ የደርግ የዕውቀትና የሥራ ዘመቻ ሲካሄድ፤ ኢህአፓንና የትጥቅ ትግል የሚያደርጉ ኃይሎችን የሚደግፉ ወጣቶች «ደርግ እኛን ገጠር ልኮ እሱ በከተማ ሊጠናከር ነው» በማለት ዘመቻውን ተቃወሙ። ሌሎች ደግሞ ከሕዝባችን መሐል ገብተን ፊደል ማስቆጠር አለብን በማለት ዘመቻውን ደገፉ።

ፍቅረሥላሴ ወግደረስ እንደሚሉት፤ 60 ሺህ (ቁጥሩ ላይ ልዩነቶች አሉ) የሁለተኛ ደረጃና የዩንቨርሲቲ ተማሪዎች ከመምህሮቻቸው ጋር በመሆን በመላ አገሪቱ በሚገኙ ስድስት ቀጠና ማስተባበሪያ ማዕከላት፣ 57 የክፍለ አገር ማስተባበሪያዎች፣ 517 ምድብ ጣቢያዎችና እያንዳንዳቸው 30 ተማሪዎች ወዳቀፉ ጣቢያዎች ለመላክ ታቅዶ ነበር።

ከአንድ ዓመት በኋላ መንግሥት ያወጣው ሪፖረት ግን ዘማቾች በ51 ማዕከላትና 397 ጣቢያዎች መዝመታቸውን፤ ቁጥራቸውም 48 ሺ ብቻ መሆኑን ይፋ አድርጓል።

የዕድገት በሕብረት የዕውቀትና የሥራ ዘመቻ ዘማቾች በመላ አገሪቱ የገጠር ክፍሎች ተሰማርተው ሥራቸውን ጀመሩ። ገበሬውን በእርሻ ሥራና በዕለት ተዕለት ኑሮው እያገዙት ማንበብና መጻፍን አስተማሩት። ፖለቲካዊ ንቃት እንዲኖረው ለማድረግና መብቱን እንዲጠይቅ አሰለጠኑት። በሂደቱ የራሳቸውን ትግል ጀምረው የፖለቲካ እንቅስቃሴ በማድረጋቸው በርካቶች ታስረዋል።

ቀስ በቀስ ደግሞ በየጣቢያው ነገሮች ከቁጥጥር ውጭ መሆን ጀመሩ። በዚህም በርካቶች ጣቢያቸውን ጥለው ወደ ቤተሰቦቻቸው ተመለሱ። በዚህ ጊዜ ደርግ «ወደ ዘመቻው ተመለሱ» ሲል ጥሪ አቀረበ። ጥሪውን ተከትሎም ጥቂቶች ወደ ዘመቻ ተመለሱ። በቁጥር ላቅ የሚሉት ግን ሳይመለሱ ቀሩ።

የዕድገት በሕብረት የዕውቀትና የሥራ ዘመቻ በመላ አገሪቱ ለሁለት ዓመታት ያህል የዘለቀ ነበር። የመጀመሪያው ዙር ዘመቻ በወጉና በሥርዓቱ እንዳይፈፀምና ሌላ ዙር ዘመቻ እንዳይቀጥል ኢህአፓ ተፅዕኖ ሲያደርግ እንደነበር የተለያዩ ጸሐፍት እና በወቅቱ የታተሙ የፓርቲው (ኢህአፓ) ልሳን ጋዜጣ ጽሑፎች ያሳያሉ።

በኢህአፓ፣ በሕወሓት እና በሌሎች በደርግ ላይ ባመፁ የውስጥ ትግሎች፤ እንዲሁም ፕሮፌሰር ባህሩ ዘውዴ እንደሚሉት ደርግ ከሶሻሊዝም ሳይንስ ይልቅ ሶሻሊዝምን ለማስረፅ በአገር ወዳድነት ስሜት ብቻ በመጓዙ ሊሆን ይችላል የደርግ ሥርዓት መቀጠል ሳይችል ቀረ።

ታኅሳስ 11 ቀን 1967 ዓ.ም የታተመው «ዘ ኒው ዮርክ ታይምስ» የተሰኘው የአሜሪካ ዕለታዊ ጋዜጣ ይህን የደርግ የህብረተሰባዊነት (ሶሻሊዝም) አዋጅ አስመልክቶ ሰፊ ሐተታ አውጥቷል። ሙሉ መረጃው እንዴት እንደደረሰውና በዕለቱ እንዴት መታተም እንደቻለ ባይታወቅም በዚያ ኢትዮጵያ ውስጥ የኢንተርኔት አገልግሎት በሌለበት ዘመን ጋዜጣው «ዛሬ» እያለ ነበር የሚያትት።

ዘ ኒው ዮርክ ታይምስ በወቅቱ እንደዘገባው፤ ደርግ የሕብረተሰባዊነት (ሶሻሊስት) አዋጅ ያወጀው በአንድ ፓርቲ (አሃዳዊ) ሥርዓት ብቻ ነበር። ሥርዓቱ የማህበር የግብርና ሥራዎችን መሰረት ያደረገ ቢሆንም የአገሪቱ ሀብቶች ግን በመንግሥት ቁጥጥር ሥር ነበሩ።

እንደ ጋዜጣው ማብራሪያ «ኢትዮጵያ ትቅደም» ማለት ሕብረተሰባዊነት ማለት ነው። ሕብረተሰባዊነት ማለት ደግሞ የራስን ዕጣ ፋንታ መወሰን መቻል፣ የመሥራት እና ሀብት የማግኘት መብት ማለት ነው። ይህም «ፊውዳል» ይባል የነበረውን የባላባትና የከበርቴ ሥርዓት በመናድ ሁሉንም እኩል የማድረግ ሥርዓት ማለት ነው።

በዚሁ ጋዜጣ ዘገባ፤ የደርግ ምክር ቤት የውጭ ባለሀብቶች (ኢንቨስተሮች) የአገሪቱን የኢኮኖሚ እንቅስቃሴ ስለሚያሳድጉ እንዲገቡ ፈቅዷል። ወደ ሀገር ውስጥ የሚገቡ ምርቶች ለአገር አደገኛ ከሆኑ ግን በጥብቅ የተከለከሉ መሆናቸውንም አሳውቋል። የውጭ ግንኙነትን በተመለከተ ከጎረቤት አገራት በተለይም ኬንያ፣ ሶማሊያ እና ሱዳን በጋራ እና በትብብር እንደሚሰራ ቃል ገብቷል።

ወታደራዊ ምክር ቤቱ ሥርዓቱ ብዙ ፓርቲዎች እንዲኖሩት አልፈቀደም ነበር፤ ምክንያት ያደረገውም ከሕዝብ ጥቅም ይልቅ ለግል ጥቅማቸው ይሰራሉ የሚለውን ነው። ብቸኛ የፖለቲካ ድርጅት የነበረው ደርግ «ተራማጅ ኃይል» የሚለውን ስብስብ የያዘው ምክር ቤት ብቻ ነው።

ዘ ኒው ዮርክ ታይምስ እንደሚለው፤ የደርግ ምክር ቤት አባላት ከፍተኛ የትምህርት ደረጃ ያላቸው ቢሆኑም በመንግሥታዊ ጉዳዮች ላይ ግን ልምድ የሌላቸው እና የፖለቲካ ግንዛቤያቸው አነስተኛ የሆኑ ናቸው። በዚህም ምክንያት መጨረሻው ጦርነት ሆኗል።

ሁሌም እንደምንለው፤ ታሪክን ስናስታውስ ለመገረሚያነት ወይም ለመዝናኛነት ወይም ለመናደድ ሳይሆን ከጥንካሬውም ሆነ ከድክመቱ ለመማር ይሁን!




የሕብረተሰባዊት ኢትዮጵያ ጊዜያዊ ወታደራዊ መንግሥት



# የዝነኞች ገጽ

# የኳሱ አርቲስት-መንግሥቱ ወርቁ

**ቦጋለ አበበ**

በኢትዮጵያ እግር ኳስ ታሪክ በአንድ ወቅት ብቅ ብለው የስፖርት ቤተሰቡን ጮቤ ካስረገጡ ታላላቅ የእግር ኳስ ባለሙያዎች መካከል አንዱ ነው። ከአንጋፋው ቅዱስ ጊዮርጊስ ክለብ ተጫዋችነት እስከ ኢትዮጵያ ብሔራዊ ቡድን አሰልጣኝነት ድረስ ስኬታማ ታሪኮችን ያስመዘገበው ዝነኛው የእግር ኳስ ጥበበኛ መንግሥቱ ወርቁ ከ12 ዓመታት በፊት ታኅሳሥ 6 ቀን 2003 ዓ.ም ነበር ከዚህ አለም በሞት የተለየው። የአለም ሕዝብ በኳታሩ አለም ዋንጫ አስደናቂ ክስተቶች ተስቦ እግር ኳስ ከትንሽ እስከ ትልቁ መነጋገሪያ ሆኖ በገነነበት በዚህ ወቅት እኛም ከተለያዩ ምንጮች ባገኘነው መረጃ ኢትዮጵያዊውን የእግር ኳስ አርቲስት በዝነኞች ገጽ ልናስታውሰው ወደድን።

መንግሥቱ የተወለደው በ1932 ዓ.ም በቀድሞው በጌ ምድር ጠቅላይ ግዛት፣ ቋራ ተብሎ በሚታወቀው አካባቢ ነው። ቤተሰቦቹ ያወጡለት ስም «አሻግራቸው» ነበር። አባቱ ፊታውራሪ ወርቁ ስንቄ ፀረ-ፋሺስት አርበኛ ስለነበሩና ለፋሺስት ኢጣሊያ ባለስልጣናት በማስቸገራቸው አባቱን ለመያዝ በማሰብ ሕፃኑ አሻግራቸው ወርቁ ከእናቱ ከወይዘሮ እማዋይሽ አብተው ጋር ታሠረ። «አሻግራቸው» የሚለው ስሙ ወደ «መንግሥቱ» የተለወጠው ከእናቱ ጋር ታስሮ በነበረበት ወቅት በፋሺስቶች ቢሆንም እንዴት እንደተለወጠ የሚገልፁት መረጃዎች ግን ሁለት ዓይነት ናቸው።

አንደኛው የአባቱ የፊታውራሪ ወርቁ ወንድም ፊታውራሪ ዓለሙ በፋሺስቶች ከተያዙ በኋላ ፋሺስቶች ፊታውራሪ ወርቁ ወንድማቸውን በጣም ይወዱ እንደነበር ስለሰሙ "ወንድምህን እንድንለቀው ከፈለግህ መጥተህ እጅህን ስጥ። አለበለዚያ በወንድምህ ላይ አደጋ ይደርሳል» የሚል መልዕክት ላኩባቸው። ፊታውራሪ ወርቁም እጃቸውን ሰጥተው ወንድማቸውን ካስፈቱ በኋላ ከእስር ቤት አምልጠው ስለጠፉ ፋሺስቶች «መንግሥቱን (ንጉሰ ነገሥቱ በስደት እየኖሩና አገሪቱ በጠላት ኃይል እየተገዛች ስለነበር) ሊፈልግ ነው ያመለጠው» ብለው ሕፃን አሻግራቸውን «መንግሥቱ» አሉት የሚል ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ «በልጅነቱ ከእናቱ ጋር በእሥር ላይ የነበረው አሻግራቸው ጣሊያኖች ሁኔታውን ዐይተው ‹አንተ መንግሥት ለመሆን ነው የምትፈልገው› በሚል ‹መንግሥቱ› ብለው ስም እንደሰጡት የሚገልፅ ነው። የሆነው ሆኖ «አሻግራቸው» የሚለው ስሙ እየተረሳ በ«መንግሥቱ» እየታወቀ ሄደ። መንግሥቱም «እንዴት ፋሺስት ባወጣልህ ስም ትጠራለህ?» ተብሎ ሲጠየቅ «ስሜ የኢትዮጵያዊ እንጂ የፋሺስት ስም አይደለም፤ እንዲያውም ስሜ የአባቴን ሙያ ያስገነዝበኛል» ብሏል።

### የትምህርት ቤት ቆይታው

የፋሺስት ኢጣሊያ ወራሪ ኃይል ድል ሆኖ ከኢትዮጵያ ከተባረረ በኋላ መንግሥቱ የቅኔ ትምህርት ቤት ገብቶ ዳዊት ደግሟል። ፊታውራሪ ወርቁ ስንቄ ከጠላት ጋር ሲፋለሙ መሞታቸውን በማሰብ ንጉሰ ነገሥት ቀዳማዊ አፄ ኃይለሥላሴ ሕፃኑ መንግሥቱ ወደ አዲስ አበባ ሄዶ በቤተ-መንግስት እንዲቀመጥ አደረጉ። በ1940 ዓ.ም መድሐኔዓለም ትምህርት ቤት ገብቶ ዘመናዊ ትምህርት መማር ጀመረ። በዚሁ ትምህርት ቤትም ከአንደኛ እስከ 12ኛ ክፍል ድረስ ተማረ።

መንግሥቱ በአንድ ወቅት ስለ ትምህርት ቤት ቆይታው ሲናገር «በ … ተማሪ ቤት እያለሁ ተማሪ ሁሉ ዘመዱ ሲጠይቀው እኔ ግን የዘመድ ጠያቂ ባለማግኘቴ እብሰለሰል ነበር። ግርማዊነታቸው ትምህርት ቤቱን ለመጎብኘት ሲመጡ የ«ወርቁ ልጅ የት አለ» ብለው አስፈልገው አነጋግረው አስፈላጊውን ሁሉ ፈፅመውልኝ ‹በርታ› ይሉኝ ስለነበር በጣም ደስ ብሎኝ እፅናና ነበር … » ብሏል።

በቀለም ትምህርት ጎበዝ ከሚባሉ ተማሪዎች መካከል አንዱ የነበረው መንግሥቱ፣ በትምህርት ቤቱ በሚከናወኑ የስፖርት ውድድሮች (በመረብ ኳስ፣ በቅርጫት ኳስ፣ በሩጫ፣ በእግር ኳስ … በመሳተፍ ሁለገብ ስፖርተኛ መሆኑን አሳይቷል። በኢትዮጵያ ተማሪዎች መካከል በተደረገ የሩጫ ውድድርም በአንድ መቶ ሜትር ተወዳድሮ አሸናፊ ሆኗል። መንግሥቱ በሁሉም የስፖርት ዓይነቶች ተሰጥዖ የነበረው ቢሆንም ትኩረት ማድረግ የፈለገው በእግር ኳስ ላይ ነበር።

በአንድ ወቅት ከሌሎች የስፖርት ጨዋታዎች ሁሉ ለእግር ኳስ የተለየ ፍቅር እንዴት እንዳደረበት ተጠይቆም « … ከጓደኞቼ ጋር እየሆንን ጢቢ ጢቢ እንጫወት ነበር። ያለማቋረጥ ብዙ እመታለሁ፤ በኋላ ገንዘብ አዋጥተን ትንሽ ሸራ ኳስ ገዛንና ራስ ኃይሉ ሜዳ እየሄድን ቅዳሜና እሁድ ስንፋተግ እንውላለን። እንዲህ እዲህ እየተጫወትን ባለንበት ወቅት ሚስተር ሒውዝ የተባሉ የስፖርት መምህራችን «A»/«B»/«C» የተሰኙ ቡድኖች አቋቋሙ። እኔ በሲ ቡድን ውስጥ ተመደብኩ። በኋላም ከአዲስ አበባ ትምህርት ቤቶች ጋር ውድድር ተመሰረተና በሁለት ቁጥር ቦታ እየተጫወትኩ ድሉ የትምህርት ቤታችን ሆነ … በ«C» ቡድን ጥሩ እጫወት ስለነበር በቀጥታ በቁመትም ሆነ በእድሜ አቻዬ ካልሆኑት ከ«A» ቡድን አባላት ጋር በአምስት ቁጥር ቦታ ተሰልፌ እንድጫወት ተመደብኩ። በ«A» ቡድን ተጨዋች በነበርኩበት ዘመን አከታትለን ቻምፒዮን ሆነናል …» በማለት የኳስ አጀማመሩንና የመድሐኔ ዓለም ትምህርት ቤት ትዝታውን ገልፆ ነበር።

### መንግሥቱ እና ቅዱስ ጊዮርጊስ

መንግሥቱ የመድሐኔዓለም ትምህርት ቤት ተማሪ ሳለ በአካባቢው ለነበረው የጉለሌ ቡድን ለመጫወት ልምምድ ጀመረ። በወቅቱ ጉለሌ በኢትዮጳያ እግር ኳስ ያልተመዘገበ የሰፈር ክለብ ነበር። ታዋቂው የቅዱስ ጊዮርጊስ እግር ኳስ ቡድን ደጋፊ የነበሩት አቶ ቱፋ ሻይና ተጨዋቹ ነፀረ ወልደ ሥላሴ መንግሥቱን ሲጫወት አይተውት ስለነበር ወደ ቅዱስ ጊዮርጊስ ቡድን እንዲገባ አግባቡት። በተለይ አቶ ቱፋ ደጋግመው ስለጠየቁት ጥያቄያቸውን ተቀብሎ በ1949 ዓ.ም፣ ክረምት ወቅት የቅዱስ ጊዮርጊስን ቡድን ተቀላቀለ።

በወቅቱ የቅዱስ ጊዮርጊስ ቡድን ወደ ድሬዳዋ ሄዶ ይለማመድ ስለነበር መንግስቱ ከቡድኑ ጋር አብሮ ተጓዘ። ቡድኑ ከጥጥ ማህበር ቡድን ጋር ሲጫወት መንግስቱ ተጠባባቂ ወንበር ላይ ለመቀመጥ ተገደደ። ያምሆኖ በጨዋታው መንግስቱ ራሱን የሚያሳይበት አጋጣሚ አገኘ። ጥጥ ማኅበር ሦስት ለ አንድ በሆነ ልዩነት እየመራ ቅዱስ ጊዮርጊስም በይድነቃቸው ተሰማ ብቸኛ ግብ እየተመራ በሚገኝበት ሰአት የፈረሰኞቹ አንድ ተጨዋች ተጎዳና መንግሥቱ ተቀይሮ ወደ ሜዳ ገባ። ሁለት ግቦችን በማስቆጠርም ቡድኑን ከሽንፈት ታደገው።

በቀጣዩ ጨዋታ ደግሞ መንግስቱ በስምንት ቁጥር መለያ ተሰለፈ። ቅዱስ ጊዮርጊሥ ስድስት ለ ሁለት በሆነ ሰፊ ውጤት አሸነፈ። ቅዱስ ጊዮርጊሥና መንግሥቱም ውል አሰሩ። የቅዱስ ጊዮርጊሥ ስምንት ቁጥር መለያ የመንግሥቱ ሆነ። በዚህ የተጀመረው የመንግሥቱና የቅዱስ ጊዮርጊስ ቡድን ትስስር እየጠነከረ ሄዶ በቡድኑ ታሪክ እስካሁን ድረስ በግንባር ቀደምትነት የሚጠቀስ ባለታሪክ ለመሆን በቃ። ቅዱስ ጊዮርጊስ ማለት መንግሥቱ፤ መንግሥቱ ማለት ቅዱስ ጊዮርጊስ ሆኑ!

መንግሥቱ ከ1951 ዓ.ም እስከ 1966 ዓ.ም ድረስ ለቅዱስ ጊዮርጊስ ቡድን ተጫውቷል። በተጨዋችነት ዘመኑ የሌላ ክለብ መለያ አልለበሰም። ከ1958 ዓ.ም እስከ 1963 ዓ.ም የኢትዮጵያ እግር ኳስ ሻምፒዮና ዋንጫን፤ በ1965 እና 1966 ዓ.ም ደግሞ የኢትዮጵያ ጭሎ ማለፍ ዋንጫን ከቅዱስ ጊዮርጊስ ቡድን ጋር አሸንፏል።

የቴክኒክና ሙያ ምሩቅ የነበረው መንግሥቱ ከተመረቀ በኋላ ለመጀመሪያ ጊዜ ሥራ የተቀጠረው መብራት ኃይል መስሪያ ቤት ውስጥ ነው። በወቅቱ መብራት ኃይል የእግር ኳስ ቡድን ነበረው። መንግሥቱ ግን የሚጫወተው ለቅዱስ ጊዮርጊስ ነበር። በ1955 ዓ.ም. ቅዱስ ጊዮርጊስ እና መብራት ኃይል በኢትዮጵያ ጥሎ ማለፍ ዋንጫ ተገናኙ። ቅዱስ ጊዮርጊስ መብራት ኃይልን አራት ለ አንድ አሸንፎ ዋንጫውን ሲያነሳ ሦስቱን የቅዱስ ጊዮርጊሥ ግቦች መብራት ኃይል ላይ ያስቆጠረው የመብራት ኃይሉ ሰራተኛ መንግሥቱ ነበር። የመብራት ኃይል ሰራተኞች «እኛ ዘንድ እየሠራና ደመወዝ እየበላ እንዴት መጫወቻ ያደርገናል?» ብለው ተቆጡ። የሰራተኞቹ ተቃውሞ እያየለ ሄዶ የድርጅቱ ኃላፊዎች «ለእኛ ካልተጫወትክ አቋምህን አሳውቅ» አሉት። እርሱም «ለጊዮርጊሥ መጫወት አላቆምም … ጊዮርጊስንም አልለቅም …» ብሎ ከመብራት ኃይል መስሪያ ቤት ሥራውን ጥሎ ወጣ።

መንግሥቱ ወርቁ ለሌሎች የእግር ኳስ ክለቦች እንዲጫወት ተጠይቆ ነበር። ነገር ግን ስምንት ቁጥርንና የ «V» ምልክት ያለበትን የቅዱስ ጊዮርጊስ መለያን ጥሎ መውጣትን እንደክህደት ስለቆጠረው የእግር ኳስ ዘመኑን በቅዱስ ጊዮርጊስ ቤት ብቻ በታማኝነት አገልግሏል። ሌላው አስገራሚ ነገር ደግሞ መንግሥቱ ቅዱስ ጊዮርጊሥን በታማኝነትና በትጋት እያገለገለ ምንም ዓይነት ክፍያ ጠይቆ አለማወቁ ነው። ስለዚህ ጉዳይ መንግሥቱ በአንድ ወቅት እንዲህ በማለት ተናግሮ ነበር …

« … የሚያጫውትህ የሕዝብ ፍቅር ነው። ከማልያው ጋር ተዋህጄ ስለነበር ትቼ መሄድ አልፈለግሁም … ደምተህና ተፈንክተህ ቡድኑን እዚህ ካደረስክ በኋላ እንዴት ጥለህ ትሄዳለህ? ስለዚህ ‹ጊዮርጊስ አልከፈለኝም› ብዬ አንድም ቀን እንኳን ገንዘብ ጠይቄ ሰንፌም አላውቅም … » … መንግሥቱ ለቅዱስ ጊዮርጊሥ የነበረው ፍቅርና ታማኝነት እንዲህ ያለ ነው።

ከኢትዮጵያ የስፖርት አባት ከይድነቃቸው ተሰማ (ለ23 ዓመታት) ቀጥሎ ለቅዱስ ጊዮርጊስ ረዥም ጊዜያት በመሰለፍ ሁለተኛ ሰው መንግሥቱ ወርቁ ሲሆን ለ16 ዓመታትም ክለቡን አገልግሏል። መንግሥቱ በተጨዋችነት ዘመኑ በእግር ኳስ ችሎታውና አብዶ በመስራት በሚያሳየው ጥበብ ተማርከው የቅዱስ ጊዮርጊስ ደጋፊ እንደሆኑ የሚናገሩ ብዙዎች ናቸው። እንዲያውም «ቅዱስ ጊዮርጊስ ኃያልና የብዙ ደጋፊ ባለቤት መሆን የቻለው በመንግሥቱ ምክንያት ነው» ብለው የሚናገሩ ወገኖች በርካታ ናቸው።

### የብሔራዊ ቡድን አገልግሎቱ

መንግሥቱ ከክለብ በተጨማሪ ለኢትዮጵያ ብሔራዊ ቡድን ተሰልፎ በመጫዋት እስከዛሬም ድረስ በማንኛውም የኢትዮጵያ ብሔራዊ ቡድን ተጨዋች ያልተደፈሩ ክብረ ወሰኖች ባለቤት ለመሆን በቅቷል። ለኢትዮጵያ ብሔራዊ ቡድን መሰለፍ የጀመረው በ1951 ዓ.ም በተካሄደው ሁለተኛው የአፍሪካ ዋንጫ ነው። በ1954 ዓ.ም ኢትዮጵያ ባስተናገደችው ሦስተኛው የአፍሪካ ዋንጫ ሦስት ግቦችን በማስቆጠር የውድድሩን ኮከብ ግብ አግቢነት ክብርን ከግብፁ መሐመድ በደዊ አብደል ፋታህ ጋር በጋራ ተቀዳጅቷል። የውድደሩ ኮከብ ተጨዋችም እርሱ ነበር። ኢትዮጵያ እስካሁን ድረስ አንድ ለእናቱ የሆነውን የአፍሪካ ዋንጫዋን (1954) እንድታሸንፍ ከፍተኛውን አስተዋፅዖ ያበረከተው መንግሥቱ ነበር።

እስከ ሰባተኛው የአፍሪካ ዋንጫ ድረስ የብሔራዊ ቡድኑን መለያ ለብሶ አገሩን አገልግሏል። በአጠቃላይ ከ1951 እስከ 1964 ዓ.ም ድረስ 102 ጊዜ ለብሔራዊ ቡድኑ ተሰልፎ ተጫውቷል፤ 62 ግቦችን ለብሔራዊ ቡድኑ በማስቆጠር የክብረወሰን ባለቤትም ነበር።

በሀገር ውስጥ ውድድሮች ላይም በርካታ ጊዜያት ኮከብ ግብ አስቆጣሪ መሆን ችሏል። መንግሥቱ በአፍሪካ ዋንጫ ታሪክ እስካሁን ድረስ ብዙ ግብ ካስቆጠሩ አፍሪካውያን ተጨዋቾች መካከል አንዱ በመሆን ከአፍሪካ ኮኮብ ግብ አግቢዎች ተርታ መሰለፍ የቻለበትን ደማቅ ታሪክም መፃፍ ችሏል። ኢትዮጵያ እስካሁን ድረስ በተሳተፈችባቸው የአፍሪካ ዋንጫዎች ላይ ከመንግሥቱ በስተቀር ኮከብ ግብ አግቢ ሆኖ ያጠናቀቀና የተሸለመ ተጨዋች የለም።

መንግሥቱ አገሩ ኢትዮጵያ የአፍሪካ ዋንጫ አሸናፊ እንድትሆን ቢያደርግም እርካታ አላገኘም። የአፍሪካ ዋንጫን አንድ ጊዜ ብቻ ሳይሆን ደጋግሞ ለኢትዮጵያ ማስገኘትን አልሞ የነበረው መንግሥቱ፣ ኳስ መጫወት ለማቆም በወሰነበት ወቅት «ላሳደገኝና ለወደደኝ ሕዝብ ውለታውን ሳልመልስ ከኳስ ተጨዋችነት መገለሌ እየፀፀተኝ ነው። ነገር ግን አገራችን ጥሩ ተጨዋቾች እንዲኖሯት በአሰልጣኝነትና በአማካሪነት ለማገልገል ከመጣር አልቦዝንም» ብሎ ተናግሮ ነበር።

### የአሰልጣኝነት ሕይወት

መንግሥቱ ከተጨዋችነቱ ባሻገር በአሰልጣኝነት ስራውም ውጤታማ መሆን ችሏል። በአሰልጣኝነቱ ያስመዘገባቸው ስኬቶች ጎበዝ ተጨዋቾች በመሆኑ የተገኙ ብቻ ሳይሆኑ ብዙ የስልጠና ኮርሶችን ወስዶ በአንደኛነት በማጠናቀቁም ጭምር የተገኙ ናቸው። የእግር ኳስ ችሎታና ልምድ ብቻውን ጥሩ አሰልጣኝ እንደማያደርግ የተረዳው መንግሥቱ፣ በዓለም አቀፉ የእግር ኳስ ማኅበር ፊፋና በሌሎች ተቋማት የተዘጋጁ የአሰልጣኝነት ስልጠናዎችን ተከታትሎ አንደኛ በመውጣት ሰርተፊኬት፣ ዋንጫና ሜዳልያዎችን አግኝቷል።

ካሰለጠናቸው ክለቦች መካከል ቅዱስ ጊዮርጊሥ፣ መብራት ኃይል፣ ኢትዮጵያ መድን፣ አየር መንገድ፣ ባንኮች እና ወንጂ ስኳር ይገኙበታል። ከአዲስ አበባ ከተማ 190 ኪሎ ሜትር እየተመላለሰ «ሕጻናት አምባ» ውስጥ የነበሩ ታዳጊዎችንም አሰልጥኗል። በ«ምርጥ» ደረጃ ደግሞ «የአዲስ አበባ ምርጥ»፣ «የሸዋ ምርጥ» እና «የኢትዮጵያ ተስፋ» ቡድኖችን አሰልጥኗል።



መንግሥቱ የእግር ኳስ ክህሎት ያላቸውን ልጆች የማወቅ ልዩ ተሰጥዖ እንደነበረው የሚያውቁት ሁሉ ይመሰክሩለታል። ክለብ ለማሰልጠን ከመስማማቱ በፊት ከክለቡ ጋር ከፍተኛ ድርድር የሚያደርገው በደመወዝ ጉዳይ ላይ ሳይሆን በሜዳ ላይ ነው። ቡድኑ የተስተካከለ መለማመጃ ሜዳ እንዲኖረው ግፊት ያደርጋል። መብራት ኃይልና መድኅን ሜዳ እንዲኖራቸው ያደረገው መንግሥቱ ነው።

የኢትዮጵያ ብሔራዊ ቡድን አሰልጣኝ በመሆንም ሀገሩን አገልግሏል። በአሰልጣኝነት ስራ ብሔራዊ ቡድኑን የተቀላቀለው በ1968 ዓ.ም በረዳት አሰልጣኝነት ነው። ቀጥሎም ዋና አሰልጣኝነቱን በመረከብና በወጣቶች የተገነባ ቡድን በመስራት ኢትዮጵያ ለ13ኛው የአፍሪካ ዋንጫ እንድታልፍ አድርጓል። በአፍሪካ ዋንጫ በተጨዋችነት ዋንጫና የወርቅ ሜዳሊያ አግኝቶ በአሰልጣኝነት ቡድኑን ለአፍሪካ ዋንጫ ያሳለፈ ብቸኛው ሰው መንግሥቱ ወርቁ ነበር። ከአሰልጣኝነቱ በተጓዳኝም የእግር ኳስ ፌዴሬሽኑ የቴክኒክ ኃላፊ ሆኖ ለአሰልጣኞች ስልጠናዎችን ሰጥቷል፤የቴክኒክ ኮሚቴን አዋቅሯል። የክለቦችን ሥልጠና በንቃት ተከታትሏል።

መንግሥቱ በኢትዮጵያ የመጀመሪያው ኢንስትራክተር (የአሰልጣኞች አሰልጣኝ) ነው። የአፍሪካ የእግር ኳስ አሰልጣኞች አሰልጣኝ በመሆን በናይጄሪያ፣ በታንዛኒያ፣ በኡጋንዳ እንዲሁም በስዋዚላንድ በመዘዋወር ለአሰልጣኞች ስልጠናዎችን ሰጥቷል። በርካታ ተተኪ አሰልጣኞችንም አፍርቷል። መንግሥቱ በኤርትራና በሱዳንም ከፍ ያለ ዝናና ተወዳጅነት ነበረው።

### መንግሥቱና 'ስምንት' ቁጥር

መንግሥቱና 'ስምንት' ቁጥር የተዛመዱ ናቸው። «መንግሥቱ ወርቁ» የሚለውም ስም ስምንት ፊደሎች አሉት። ክለቡ «ቅዱስ ጊዮርጊስ»ም ባለስምንት ፊደል ነው። የሚቆርጠው ሎተሪና የሚነዳው መኪና የመጨረሻ ቁጥራቸው እንዲሁም ለክለብም ሆነ ለብሔራዊ ቡድን ሲጫወት የሚለብሰው የመለያ ቁጥር ስምንት ነበር። በባህርይው ኮስተር ያለ (ቁጡ) እንደነበር የሚነገርለት መንግሥቱ፣ «በባህሪዬ ቁጡ ነኝ፤ አኩራፊም ነኝ። አሁን እድሜዬ በመግፋቱ ሁሉንም ትቻለሁ። ግን ኳስ ተጨዋች ለመሆን በትንሹ ቁጡ መሆን ያስፈልጋል» ብሏል።

ኢትዮጵያ እስካሁን ድረስ ካፈራቻቸውና ካየቻቸው ታላላቅ የእግር ኳስ ባለሙያዎች መካከል አንዱ የሆነው፤ ለቅዱስ ጊዮርጊስና ለሌሎች ክለቦች እንዲሁም ለኢትዮጵያ ብሔራዊ ቡድን ባከናወናቸው ዘመን አይሽሬ ወርቃማ ተግባራት አሁንም ድረስ በበርካታ አድናቂዎቹና የእግር ኳስ ቤተሰቦች ዘንድ ልብ ውስጥ ላቅ ያለ ቦታ ያለው ወርቃማው የእግር ኳስ አርቲስት መንግሥቱ ወርቁ፣ የጤና እክል አጋጥሞት በአገር ውስጥና በውጭ አገራት በሕክምና ሲረዳ ቆይቶ፣ ታኅሣሥ 06/ 2003 ዓ.ም ነበር ከዚህ ዓለም በሞት የተለየው።

# ዓለም አቀፍ

## በቻይና የኮቪድ 19 ወረርሽኝ አሳሳቢ ደረጃ ላይ መድረሱ ተገለጸ



በቻይና በአንድ ቀን ብቻ 37 ሚሊዮን ሰዎች በኮቪድ 19 ሳይያዙ እንዳልቀረም ብሉምበርግ የሀገሪቱን ጤና ተቋማት አሃዞች ጠቅሶ ዘግቧል፡፡በታህሳስ ወር 20 ቀናት ውስጥ 248 ሚሊዮን ቻይናውያን በቫይረሱ ተጠቂ መሆናቸው ቢገምትም ቤጂንግ የምትጠቅሰው ቁጥር ከዚህ በብዙው ያነሰ ነው፡፡ከሁለት አመት በፊት የኮሮና ቫይረስ ለመጀመሪያ ጊዜ የተገኘባት የቻይናው ዉሃን ከተማ ወረርሽኙ ዳግም አገርሽቶባታል።

ወረርሽኙ በታህሳስ ወር መላው ቻይናን እያዳረሰ መሆኑንም ከቤጂንግ እየወጡ ያሉ መረጃዎች ያሳያሉ።ብሉምበርግ የሀገሪቱን ጤና ተቋማት አሃዞች ጠቅሶ ባወጣው ዘገባ በአንድ ቀን ብቻ 37 ሚሊየን ሰዎች በኮቪድ 19 ሳይያዙ እንዳልቀረ ጠቁሟል።በታህሳስ ወር 20 ቀናት ውስጥ 248 ሚሊየን ቻይናውያን በቫይረሱ ተጠቂ ስለመሆናቸውም ዘገባው ያክላል።

የቻይና ባለስልጣናት ግን አለም አቀፍ ጫናውን ለመቀነስ ከተጠቀሰው አሃዝ እጅግ ዝቅ ያለውን ሪፖርት እያደረጉ ነው ተብሏል።ለሶስት ተከታታይ ቀናት የኮቪድ ሞቶችን የመዘገበችው ቤጂንግ በታህሳስ 22 ብቻ 4 ሺ አዳዲስ የቫይረሱ ተጠቂዎች መኖራቸውን ይፋ አድርጋለች።ይሁን እንጂ በማህበራዊ ሚዲያዎች እየወጡ ያሉ ተንቀሳቃሽ ምስሎች ሆስፒታሎች በህመምተኞች መጨናነቃቸውን የሚያሳዩ ናቸው።

የሀገሪቱ የተላላፊ በሽታዎች ተቆጣጣሪ ድርጅት ዋና ዳይሬክተር ዣንግ ዌንሆንግ ከሻንጋዩ ዘ ፔፐር ጋዜጣ ጋር ባደረጉት ቆይታ፥ "በቻይና የወረርሽኙ ስርጭት በአንድ ሳምንት ውስጥ ለቁጥጥር አዳጋች የሚሆንበት ደረጃ ይደርሳል" ብለዋል።በዚህም ለከባድ ህመምና ህልፈት የሚዳረጉ ዜጎች ቁጥር ሊያሻቅብ እንደሚችል ጠቅሰው የሀገሪቱ የጤና ተቋማትም ከፍ ያለ ዝግጅት እንዲያደርጉ አሳስበዋል።

የአለም ጤና ድርጅትም የኮቪድ 19 ወረርሽኝ አሁንም የምድራችን ፈተና መሆኑን እየገለጸ ነው።ወረርሽኙ የጠፉ የመሰላቸው በርካቶች ይሁኑ እንጂ በየሳምንቱ 10 ሺህ ሰዎች በዚሁ ቫይረስ እየሞቱ መሆኑንም ነው የሚጠቅሰው።ቻይና በፈረንጆቹ ታህሳስ 19 2019 በሁቤይ ግዛት መዲናዋ ዉሃን የኮቪድ 19 ወረርሽኝ ከተከሰተባት ወዲህ ከአለም ጤና ድርጅትም ሆነ ከምዕራባውያን መገናኛ ብዙሃን የሚወጡት መረጃዎች የተጋነኑ ናቸው በሚል ትሞግታለች።

ከመካሰሱ ይልቅ ቀለም ወይም ሃይማኖት የማይመርጠውን ወረርሽኝ በጋራ እንከላከለው የሚል ጥሪንም ደጋግማ ስታቀርብ ተደምጣለች።ሃያላኑ ሀገራት በዚሁ ቫይረስ መነሻና ተያያዥ ጉዳዮች ሲነታረኩ በመላው አለም 657 ሚሊየን ሰዎችን ያጠቃው ኮሮና ከ6 ነጥብ 6 ሚሊየን በላይ ሰዎችን ህይወት ቀጥፏል።

በታህሳስ ወር ዳግም በውሃን የተቀሰቀሰው ወረርሽኝም ሀገራትን ከመዘናጋት ሊያነቃቸውና የጋራ መፍትሄን ለመፈለግ እንዲሰሩ ሊያተጋቸው ይገባል መባሉን አል ዐይን ዘግቧል።

## ዩክሬን ከአፍሪካ ጋር ያላትን ዲፕሎማሲያዊ ግንኙነት ለማጠናከር እንደምትሰራ ፕሬዝዳንት ዘሌንስኪ ገለጹ

የዩክሬኑ ፕሬዝዳንት ቮሎዲሚር ዘሌንስኪ ኪቭ በአፍሪካ፣ በላቲን አሜሪካ እና በእስያ ያለውን "ትልቅ የኢኮኖሚ አቅም" እና ሌሎች ዓለም አቀፍ ጥቅሞችን ለመጠቀም ዲፕሎማሲያዊ ጥረቶችን አጠናክራ እንደምትቀጥል ተናግረዋል።

ዘሌንስኪ የኪቭ የዲፕሎማሲ ትኩረት ብዙም ተጽእኖ የለኝም ብላ ወደ ምታስበው የደቡብ የዓለም ክፍል አቅጣጫ መሆን እንዳለበት ከትናንት ወዲያ በምሽት ለዲፕለማቶቻቸው ባስተላለፉት የቪዲዮ መልእክት ተናግረዋል፡፡በአፍሪካ "ትልቅ የኢኮኖሚ አቅም እና ትልቅ ዲፕሎማሲያዊ መንገዶች አሉ"ም ብለዋል ፕሬዝዳንቱ፡፡

በተጨማሪም ዩክሬን ከባህላዊ አጋሮቿ ጋር ግንኙነት ለመፍጠር እንደምትፈልግ መግለጻቸው ሮይተርስ ዘግቧል፡፡ፕሬዝዳንት ዘሌንስኪ ቀደም ሲል ለዲፕሎማቶች በሰጡት አስተያየት፤ ከአፍሪካ ጋር ያለውን ግንኙነት ለማስፋት የተደረጉ ሙከራዎችን ለይቷል።

በዚህም ዩክሬን በተጋላጭ ሀገራት ውስጥ ያለውን ረሃብ ለመቅረፍ የሰብዓዊ እህል ርዳታን በመላክ የአፍሪካ ሀገራትን ከዓላማዋ ጎን ለማሰለፍ ስትሞክር ቆይታለች።ሩሲያ፤ ዩክሬን በጥቁር ባህር በኩል ወደ ውጭ የምትልካቸው የግብርና ምርቶች ማገዷን ተከትሎ በዚህ አመት ዓለም አቀፍ የእህል እና የማዳበሪያ እጥረት አስከትሎ እንደነበር የሚታወስ ነው፡፡

በዚህም በተባበሩት መንግስታት አደራዳሪነት በሐምሌ ወር ስምምነት ላይ ተደርሶ በከፊል መለቀቅ እስከጀመረበት ድረስ በሚሊዮኖች የሚቆጠሩ ሰዎችን አደጋ እንዲወድቁ ምክንያት ሆነ ነበር፡፡በተፈጠረው ነገር እጅጉን ማዘናቸው የገለጹት ፕሬዝዳንት ዘሌንሰኪ አሁን ላይ "በደርዘን ከሚቆጠሩ የአፍሪካ ሀገራት ጋር ያለውን ግንኙነት እያስተካከልን ነው" እናም በሚቀጥለው ዓመት ይህንን ማጠናከር አለብን ሲሉም ለዲፕሎማቶቻቸው ተናግረዋል።

ግንኙነቱን ይበልጥ ለማጎልበት ዩክሬን በአህጉሪቱ ውስጥ ባሉ በርካታ ማዕከሎች ውስጥ የንግድ ተወካይ ጽህፈት ቤቶችን ማቋቋም እንደምትፈልግም ጭምር አስታውቀዋል፡፡እነዚያ አዳዲስ ኤምባሲዎች ወይም የንግድ ቢሮዎች የት እንደሚገኙ ግልጽ ያላደረጉት



ዘሌንሰኪ፤ ዩክሬን በአህጉሪቱ 30 ሀገራት እንድትወከል እናደርጋለን ማለታቸውን አል ዐይን ዘገባ ያመለክታል፡፡

የኢትዮጵያ አእምሯዊ ንብረት ባለስልጣን
Ethiopian Intellectual Property Authority

ከኢትዮጵያ አእምሯዊ ንብረት ባለስልጣን ጋር
በመተባበር በየአስራ አምስት ቀኑ የሚታተም

## የአእምሯዊ ንብረትና የባሕላዊ ሕክምና እውቀት የባለቤትነት አወቃቀር

**በታደሰ ወርቁ**

የአእምሯዊ ንብረት ባለቤትነት ማለት የአንድ ፈጠራ ባለቤት ፈጠራውን በሚመለከት ሌሎች ሶስተኛ ወገኖች እንዲጠቀሙበት የመፍቀድ ወይም የመከልከል መብት በሕግ ማግኘት ነው። ነገር ግን ይህ የንብረት ባለቤትነት ሥርዓትና አተገባበር አብዛኛውን ጊዜ ታሳቢ የሚያደርገው በግል ጥረት መንጭቶና ለምቶ በራሱ በግለሰቡ ባለቤትነት የሚያዝን ሀብት /ፈጠራን እና እውቀትን/ በመሆኑ እንደ ማሕበረሰቦች እውቀትና ተያያዥ ሀብቶችን ለማስጠበቅ ባለው ምቹነትና አዋጭነት ላይ በርካታ የድጋፍና ተቃውሞ አመለካከቶች ይንጸባረቃሉ።

መደበኛዎቹ የአእምሯዊ ንብረት ሕጎች ማለትም የፓተንት፣ የንግድ ምልክት፣ የኮፒራይት አሠራሮች ሀገር በቀል የማህበረሰብ እውቀትን ለማስጠበቅ ያሉባቸው ውሱንነቶች እና ጥንካሬዎች እንዳሉ ሆነው በባህላዊ መንገድ በተፈጠሩ እውቀቶችና ክህሎቶች ላይ የእውቀቱ ባለቤቶች የአእምሯዊ ንብረት መብት የሚያገኙባቸውን ሕጎች ለመዘርጋት በተለያዩ ሀገራት ጥረቶች እየተደረጉ ነው። በዓለም አቀፍ ደረጃም የዓለም አእምሯዊ ንብረት ድርጅት የሚመራው የበይነ መንግስታት ኮሚቴ (Inter Governmental Committee) እያረቀቀ ያለው የስምምነት ሰነድ ሊጸድቅ እንደሚችል ከፍተኛ እምነት የተጣለበት ጉዳይ ነው፡፡

ማንኛውም የንብረት ባለቤትነት መብት በግለሰብ ብቸኛ ባለቤትነት ከሚያዙት ንብረቶች ማለትም ቤት፣ መኪና፣ የፈጠራ ሥራ ወ.ዘ.ተ ጀምሮ የሰው ልጅ ሁሉ በጋራ እስከሚጠቀምባቸው ሀብቶች ማለትም ንጹህ አየር፣ ውሀ፣ ወ.ዘ.ተ ባሉት ምድቦች ውስጥ ሊካተት ይችላል። ይህንን ጉዳይ በሚመለከት ማክስ ፕላንክ የተባለው ተቋም (Max Planck institute) ባሳተመው የምርምር ጽሁፍ መሠረት ሦስት ዋና ዋና የንብረት ባለቤትነት መዋቅሮች መኖራቸውን ይገልጻል።



እነዚህም በግለሰብ የሚያዝ (Individual ownership)፣ በውስን ባለቤቶች የተያዘ (Multiple ownership) እና በወል ወይም በጋራ ባለቤትነት የተያዘ (Collective ownership) በማለት በዝርዝር ያብራራቸዋል።

በሌላ መልኩ የአለም አቀፉ የአእምሯዊ ንብረት ድርጅት የማህበረሰቦች እውቀትን (Traditional Knowledge) በሚመለከት የባለቤትነት አወቃቀር በሦስት እንደሚከፈል ያስረዳል። እነዚህም 'በተወሰኑ መንግሥታት ብቻ የሚያዝ፣' 'በአካባቢ ማህበረሰቦች በጋራ የተያዘና' 'በግለሰቦች ብቻ የሚታወቅ' በማለት ይከፋፍላቸዋል። እነዚህ ከላይ የተጠቀሱት የባለቤትነት አወቃቀር ሥርዓቶችም ይሁኑ ሌሎች የባለቤትነት ሥርዓቶች በእውቀቱ ተጠቃሚዎችና በእውቀቱ ባለቤቶች መካከል ለሚኖሩ ኢኮኖሚያዊ መስተጋብሮች እንዲሁም የተሳለጠ የእውቀት ሽግግርና ልማት የየራሳቸውን አስተዋጽኦ ያበረክታሉ።

በንድፈ ሃሳብ ደረጃም ቢሆን ሙሉ በሙሉ በግለሰብ ወይም በተወሰኑ ተለይተው በታወቁ ቤተሰቦች ብቻ በተያዙ እውቀቶችና መረጃዎች ላይ ሌሎች ሦስተኛ ወገኖችን ወይም አልሚዎችን እና የእውቀቱን ባለቤቶች በቀላሉ ማደራደርና የመረጃ ሽግግር ማድረግ እንዲሁም ወደ ልማት ለማስገባትም ይሁን ሌሎች ተያያዥ ጉዳዮችን ለመወሰን ይቻላል። በሌላ መልኩ ብዙ ባለመብቶች የሚጋሩትን እውቀት ወይም ትክክለኛ የእውቀቱ አመንጪው የማይታወቅ እውቀትንና መረጃን አስመልክቶ እውቀቱን ለማስተላለፍም ይሁን የእሽታ ፍቃድ ከማግኘት ጀምሮ እስከ ልማትና ጥቅም ክፍፍል አወሳሰን ድረስ ባለው ሂደት ውስጥ ውስብስብ የአፈጻጸም መሰናክሎች ሊያጋጥሙ እንደሚችሉ መገመት ይቻላል።

ከዚህ አኳያ በሀገራችን ያለውን የባሕላዊ ሕክምና እውቀት የአእምሯዊ ንብረት ባለቤትነት ጉዳይን ለመወሰን ሲሞከር አስቀድመው የሚነሱ መሠረታዊ ጥያቄዎች አሉ። ከእነዚህ ጥያቄዎች መካከል በኢትዮጵያ ውስጥ የሚገኙት ባህላዊ መድሃኒቶች በእርግጥ በኢትዮጵያ ውስጥ ብቻ የሚገኙ ናቸውን? በተለያዩ ሙዚየሞችና በቅርስ ጥበቃ ማዕከላት የሚገኙ ጥንታዊ የመድሃኒት መግለጫ ሰነዶች (Pharmacopias) ውስጥ የተገለጠ እውቀት ባለቤቱ ማነው? የግል ባለቤትነት የሚጠየቅባቸው እውቀቶችስ ከእነዚህ ጥንታዊ ሰነዶች ያለመቀዳታቸውን እንዴት ማረጋገጥ ይቻላል? አንድ የመድሃኒት እውቀት በጋራ ተይዟል የሚባለው ምን ያህል አባላት ሲጋሩት ነው? በጋራ ባለቤትነት የተያዘ መሆኑንስ እንዴት ማረጋገጥ ይቻላል? የሚሉት ይገኙበታል።

ስለዚህ ባህላዊ የሕክምና መድሃኒት በአሁኑ ወቅት አገልግሎት እየሰጠ በሚገኝበት ደረጃ ያለው ፈዋሽነትም ይሁን የአስገዳጅነት ጥራት ሙሉ በሙሉ አስተማማኝ ባለመሆኑ ባህላዊ መድሃኒቱ ባሉት ይዘቶች ላይ ተጨማሪ ምርምርና ጥናት ማድረጉ የመድሃኒቱን ኢኮኖሚያዊ ፋይዳም ይሁን የፈዋሽነት አቅሙን ለማሳደግ ያስችላል። ተጨማሪ ምርምርና ጥናት ለማድረግ የመጀመሪያው ሥራ የሚሆነው እውቀቱንና መረጃውን ይዘው የሚገኙትን ወገኖች ታሳቢ ያደረገ የባለቤትነትና የእውቀት ሽግግር ሥርዓት መዘርጋት ነው። በሌላ መልኩ የባሕላዊ ሕክምና እውቀትም ይሁን ሌሎች የማህበረሰቦች እውቀት ልማትና እሴት የማበልጸግ ሥራ በተግባር የሚጀመረው ጤናማ የመረጃ ፍሰት ሲረጋገጥና በእወቀቱ ዙሪያ የሚታየው የሚስጥራዊነት አሠራር ሲቀንስ ነው፡፡ ለዚህ ደግሞ የአእምሯዊ ንብረት ባለቤትነት ሥርዓቱ (መደበኛው የአእምሯዊ ንብረት መብት ማስጠበቂያዎች ወይም ሌሎች ራሳቸውን የቻሉ የጥበቃ ዘዴዎችና አሠራሮች ሊሆኑ ይችላሉ) ሊጫወት የሚችለው ሚና በቀላሉ ሊታይ አይገባም፡፡

# ስፖርት



# የአንበሶቹ አንበሳ-ዋሊድ ራግራጉዊ

**ብርሃን ፈይሳ**

ከሳምንት በፊት የተጠናቀቀው የኳታር ዓለም ዋንጫ በርካታ አስደናቂ ጉዳዮች የታዩበት ነው። የሞሮኮ ብሄራዊ ቡድንም የአለም ዋንጫው አስደናቂ ክስተት እንደነበር አለም በሙሉ ድምጽ የሚመሰክረው ነው። በአለም ዋንጫው የእግር ኳስ ኃያል ሃገራትን ጭምር ሳይጠበቅ በማሸነፍ አራተኛ በመሆን ያጠናቀቁት የአትላስ አንበሶች፣ በአፍሪካ እግር ኳስ የመጀመሪያው የግማሽ ፍጻሜ ተፋላሚ አገር በመሆን አዲስ ታሪክ ማስመዝገብ ችለዋል።

በኳታሩ አለም ዋንጫ አፍሪካዊ መሰረት ያላቸው ተጫዋቾችና አሰልጣኞች ትኩረት ስበውም ነበር። አህጉራቸውን የወከሉት የአፍሪካ ቡድኖችን ጨምሮ ጥቁር ተጫዋቾች በአውሮፓ ቡድኖች ውስጥ በብዛት በታዩበት በዚህ አለም ዋንጫ፣ አፍሪካዊያኑ አምስት ቡድኖች ለመጀመሪያ ጊዜ በአፍሪካውያን አሰልጣኞች መመራታቸው ይታወቃል።

ከእነዚህ አሰልጣኞች መካከል ባስመዘገበው ስኬት መሰረት በቀዳሚነት የሚቀመጠው የአትላስ አንበሶቹ አለቃ ዋሊድ ሬግራጉዊ ነው። የቀድሞው እግር ኳስ ተጫዋች የአሰልጣኝነት ህይወቱን አሃዱ ካለ 10 ዓመታትን ብቻ ያስቆጠረ ቢሆንም በዚህ ዓለም ዋንጫ ቡድኑን የማሰልጠን ዕድሉን ማግኘቱ ሃገሩን በክብር ስፍራ ከማስቀመጥ አልፎ በአህጉር አቀፍ ደረጃም የደማቅ ታሪክ ባለቤት ለመሆን ችሏል። ውልደቱን በፈረንሳይ ያደረገው ጎልማሳው አሰልጣኝ «ሃገር ማለት ልብህ ያለባት ስፍራ ናት» በሚለው ታዋቂ አባባል መሰረት አውሮፓዊቱን ሃገር ሳይሆን የዘር ሃረጉ የሚሳብባትን ሞሮኮን መምረጡ ለስኬት አብቅቶታል።

የአትላስ አንበሶቹ አንበሳ ተብሎ የተወደሰው የዋሊድ ሬግራጉዊ ውልደት እአአ በ1975 በፓሪስ ደቡብዊ ክፍል ኮርቢል-ኢሶኔስ ከተባለ ስፍራ ነው። እግር ኳስን በተወለደበት አካባቢ በሚገኝ ቡድን ውስጥ መጫወት የጀመረ ሲሆን፤ የ23 ዓመት ወጣት ሳለም መቀመጫውን በፓሪስ ያደረገውን ሬሲንግ ፓሪስ የተባለ ቡድን ተቀላቀለ። እአአ እስከ 2009 ባሉት ዓመታትም በስድስት የፈረንሳይ ክለቦች ውስጥ በተጫዋችነት አሳልፏል። ከ2009-2012 ባሉት ዓመታት ግን ከአውሮፓ ወደ ሞሮኮ በመምጣት መግሪብ አትሌቲኮ ቴቱዋን የተባለውን ክለብ ተቀላቅሎ በተጫዋችነት አሳልፏል። የእግር ኳስ ተጫዋችነት ዘመኑ እስኪጠናቀቅ ድረስም የሞሮኮ ብሄራዊ ቡድንን ሲያገለግል የቆየ ሲሆን፤ እአአ በ2004ቱ የአፍሪካ ዋንጫ ላይ ሃገሩ የዋንጫ ተፋላሚ በነበረችበት ወቅትም ከቡድኑ ጋር ነበር።

አሰልጣኙ በተጫዋችነት ወደ ሞሮኮ መምጣቱን ተከትሎ የአሰልጣኝነት ህይወቱም በዚያው የቀጠለ ሲሆን፤ እአአ በ2012 የብሄራዊ ቡድኑ ምክትል አሰልጣኝ ሆኖ አገልግሏል። ከሁለት ዓመት በኋላም ፋዝ ዩኒየን ስፖርት የተባለውን ክለብ ለአንድ ዓመት የማሰልጠን ዕድል በማግኘት እአአ እስከ 2019 ድረስ ቆይታ አድርጓል። ቀጣዩን አንድ ዓመት በኳታሩ ክለብ አል ዱሃይል ካሳለፈ በኋላ፤ ወደ ሃገሩ በመመለስ የካዛብላንካውን ታዋቂ ክለብ አልዋይዳድን በማሰልጠን የሊግዋንጫን እንዲሁም የካፍ ቻምፒዮንስ ሊግ ዋንጫን ተቀናቃኙን ክለብ አል ሃሊን በመርታት ለሶስተኛ ጊዜ እንዲያነሳ አድርጓል። ይኸውም በሞሮኮ እግር ኳስ ታሪክ ዋንጫውን ያሳካ ሁለተኛው አፍሪካዊ አሰልጣኝ አድርጎታል።

ከአራት ወራት በፊትም የሞሮኮ ብሄራዊ ቡድን አሰልጣኝ በመሆን ተመረጠ፤ ስራውንም የጀመረው ከማዳጋስካር ጋር በነበራቸው የወዳጅነት ጨዋታ ነበር። የ47 ዓመቱ አሰልጣኝ ቡድኑን በተረከበበት ወቅት በበርካታ የስፖርት ቤተሰቡ ዘንድ ተቃውሞን ያስተናገደ ሲሆን፤ ከዚያም አልፎ «አቮካዶ ራስ» የሚል ቅጽል ስምም ተሰጥቶት ነበር። ይሁንና አሰልጣኙ ዓላማውን ለማሳካት ጆሮ ዳባ ልበስ ብሎ ራሱን አግልሎ የቆየውን አሸራፍ ሀኪሚን ወደ ቡድኑ በመመለስ፣ በተጫዋቾች መካከል ጠንካራ ቁርኝት በመፍጠር እንዲሁም በማነሳሳት ከስኬት መድረስ ችሏል።



**የሞሮኮ እግር ኳስ ብሄራዊ ቡድን አሰልጣኝ ዋሊድ ሬግራጉዊ በአለም ዋንጫ ታሪክ የማይደረሳ ታሪክ መስራት ችሏል፣**

አሰልጣኙ በዓለም ዋንጫው ቀላል የሚመስለውን ነገር ግን በርካታ ቡድኖች መተግበር ያልቻሉትን በጠንካራ መከላከልና በመልሶ ማጥቃት እንቅስቃሴ ጠንካራ ቡድን ከመፍጠር አልፎ፤ ራሱን ከመጠላት ወደ ብሄራዊ ጀግናነት ቀይሯል። ቡድኑንም በዓለም ዋንጫው ምድብ ስድስት ቀዳሚ በመሆን 16ቱን ሲቀላቀል በስፔን እና ፖርቹጋል ላይ ፍጹም የበላይነትን ወስዶ ነበር። በግማሽ ፍጻሜው ፍልሚያም የ2018 የአለም ቻምፒዮኗ ፈረንሳይን በማስጨነቅ ለደረጃ ተፎካካሪነት በማብቃት ደማቅ ታሪክ ማስመዝገብ ችሏል። ከሃገሩ አልፎ ለአፍሪካዊያን አሰልጣኞችም አርዓያ መሆን የቻለው ይህ አሰልጣኝ በብዙዎች ዘንድ አድናቆት እየጎረፈለትም ይገኛል።

‹ባልተጠበቀ ሁኔታ ቤልጂየም፣ ስፔን እና ፖርቹጋልን በማሸነፋችን፤ ብዙዎች ተዓምር ነው እንደሚሉ እርግጠኛ ነኝ። ነገር ግን ይሄ ጠንክሮ የመስራት ውጤት ነው›»። የሚለው ዋሊድ ሬግራጉዊ ከዓለም ዋንጫው በፊት ቡድኑን በ3 ጨዋታዎች ላይ ብቻ ነበር መምራት የቻለው።የአፍሪካ ብሄራዊ ቡድኖች ከዚህ ቀደም በርካታ የአውሮፓ አሰልጣኞችን ከፍተኛ ወጪ በማውጣት ቀጥረው እንዲያሰለጥኑ አድርገዋል። ነገር ግን ዋሊድ ሬግራጉዊ የሰራውን ገድል ፈፅመው አፍሪካን እግር ኳስ አንድ እርምጃ ማራመድ አልቻሉም።

ይህ ስኬት የተመዘገበው በምዕራባዊ አሰልጣኝ ቢሆን ኖሮስ ብለን ብናስብ ደግሞ ስኬቱ የሃገሪቱ መሆኑ ይቀርና የአሰልጣኙ ማንነት ይበልጥ ትኩረት ያገኝ እንደነበር ምንም ጥርጥር የለውም። የሞሮኮ ስኬት የአፍሪካን እግር ኳስ ስነ ልቦና ከፍ ከማድረግ አኳያ ከፍተኛ ሚና ስለሚኖረው ውጤቱ ከዚህ በኋላ ለሚኖረው ተሳትፎ መጠቀም ከተቻለ ትልቅ ግብአት በመሆኑ አሰልጣኙ ለብዙዎች ምሳሌ ሆኗል።




# በጎነትን ናፋቂዋ ልጅ

**በስጦሻቸው ልዑልሰገድ**

ሰላም ልጆች እንዴት ናችሁ! ሳምንቱ እንዴት አለፈ? ሳምንቱ ያለፈው በትምህርት ነበር እንዳላችሁ እርግጠኛ ነኝ። ምክንያቱም ጎበዝ ተማሪ ሳምንቱን የሚያሳልፈው በትምህርት ነው። እናንተ ደግሞ ጎበዝ ተማሪ እንደሆናችሁ አምናለሁ፡፡ ጎበዝ ተማሪ ትምህርቱን በአግባቡ ያጠናል፣ የቤት ስራውን ይሰራል እና የቤተሰብ ምክር ይሰማል። እናንተም እነዚህን ትግባራት ስለምታከናውኑ ጎበዝ ናችሁ።

ልጆች በልጅነታችሁ መሆን የምትፈልጉት ነገር ወደፊት ካደጋቹ በኋላ ለምትሆኑት ነገር ትልቅ መሰረት እንደሆነ ታውቃላችው? ብዙ ልጆች እኔ ሳድግ ፓይለት፣ ሣይንቲስት ፣ ፖሊስ፣ አስተማሪ፣ ወታደር እና የሌሎች ሙያዎች ባለቤት እሆናለሁ ሲሉ ትሰማላችሁ። እናንተም ስታደጉ መሆን የምትፈልጉት እና መስራት የምትፈልጉት ሙያ እንዳላችሁ እርግጠኛ ነኝ። መሆን የምትፈልጉትን ማወቃችሁ ለምን እንደሚጠቅማችሁ ልንገራችሁ፤ መሆን የሚፈልገውን የሚያውቅ ልጅ ወደፊት ሲያድግ መሆን የፈለገውን እንዲሆን ዛሬ ጠንክሮ ይማራል፤ ከሚፈልገው ነገር ጋር የሚያያዙ መፃህፍትን ያነባል እናንተም መሆን የምትፈልጉትን ስታውቁ የምትፈልጉት ነገር ጋር የሚያያዙ መፃህፍት ታነባላቹ በትምህርታቹም ጎበዝ ትሆናላችሁ።

ልጆች የምትመኙትና መሆን የምትፈልጉት ነገር ከሙያ ወይም ከስራ አንፃር ብቻ መሆን የለበትም። ጥሩ ስራ የሚሰሩና ለብዙ ሰው አርአያ የሚሆኑ ሰዎችን ስታዩ እናንተም ስታድጉ እንደዛ ሰው ለመሆን መመኘትና ጥሩ ስራ መስራት ካሁኑ መለማመድ አለባችሁ። ልጆችዬ ዛሬ በልጆች አምድ ይዤላችሁ የቀረብኩት ስታድግ ምን መሆን እንደምትፈልግ የምታውቀዋንና ካሁኑ እየተለማመደች



**በፀሎት ተከተል**



ያለችውን ህፃን በፀሎት ተከተልን ነው። በፀሎት የስድስት አመት ህፃን እና «የአርአያ ለትውልድ» አፀደ ህፃናት ትምህርት ቤት የመዋለ ህፃናት ተመራቂ ተማሪ ናት።

ልጆች በፀሎት ምን መሆን እንደምትፈልግ ታውቃላችው? አድጋ ትልቅ ስትሆን ሰው ስለሚረዳና በጎ ስራ ስለሚሰራ እንደ ዶክተር ቢንያም በለጠ መሆን ነው የምትፈልገው። ቢኒያም በለጠ ማን እንደሆነ ታውቃላችሁ? ያወቃችሁ ጎበዞች ናችሁ። ላላወቃችሁት ደግሞ በፀሎት ትነግራቹሃለች። በፀሎት ቢኒያም ማን ነው ብላችሁ ብትጠይቋት መቄዶኒያ የአረጋዊያንና የአእምሮ ህሙማን መርጃ ማእከል ያቋቋመውና «ሰው ለመርዳት ሰው መሆን በቂ ነው» የሚለው ነው ብላ ትነግራቹሃለች።

በፀሎት የተቸገሩ ሰዎችን መርዳት ያስደስታታል። ትምህርት ቤትም ጓደኞቿ ሲወድቁ ደግፋ ታነሳቸዋለች፣ ሲያለቅሱ ታባብላቸዋለች። ወደፊት አድጋ ቢኒያም ያስጀመራቸውን ሰው የመርዳት ስራዎች ለማስቀጠል ትፈልጋለች። ለዛ እንዲረዳት ደግሞ ከአሁኑ በዙሪያዋ ያሉ ሰዎችን አንዱን ከአንዱ ሳትለይ በእኩል ዓይን በማየት ልትረዳቸው ትሞክራለች። ሁሉም ልጆችም ልክ እንደሷ ሁሉንም ሰው እኩል እንዲረዱ ልዩነት ሳያደርጉና ሳያዳሉ ለሁሉም እንዲደርሱ ትመክራለች።

በፀሎት ወደፊት ልክ እንደ ቢኒያም በለጠ የተቸገሩ አረጋዊያንን እና የአዕምሮ ህሙማንን እንዲሁም የተቸገሩ ህፃናትን መንከባከብ ፣መርዳትና የጎድላቸውን ማንኛውም ነገር በማሟላት ከጎናቸው መሆን ትልቁ ፍላጎቷ ነው። ቅርብ ጊዜም መቄዶኒያ ድረስ በመሄድ ከዶክተር ቢኒያም በለጠ ጋር በመሆን መቄዶኒያን ጎብኝታለች፤ መቄዶኒያ ዉስጥ ያየቻቸው አረጋውያንና የአዕምሮ ህሙማን "ያምራሉ ግን ያሳዝናሉ" ትላለች። የተሰማት የሀዘን ስሜት ፊቷ ይታያል። "ቢኒያምን በጣም ነው የምወደው። እሱ ብዙ በጎ ነገሮችን ይሰራል። እኔም እሱ የጀመርዉን አስቀጥላለሁ" ትላለች በህፃን ጣፋጭ አንደበቷ።

መቄዶንያን በጎበኘችበት ወቅት አረጋዊያንን እግራቸውን አጥባ ከአልጋ መነሳት የማይችሉትን ደግሞ እየዞረች አይዞዋችሁ ብላቸው መርቀዋታል። አያችሁ ልጆች ጥሩ ስራ መስራትና ሰውን መርዳት በትልልቅ ሰዎች እንድንመረቅ ያደርገናል። ምርቃት ደግሞ ያሳድጋል። ልጆች በፀሎት ገና የስድስት አመት ህፃን ናት ።ግን ህፃን መሆኗ ሰው ከመርዳት አላገዳትም፤ የምትሰጣቸው ብርም ሆነ የምታካፍላቸው ንብረት ባይኖራትም የተቸገሩ ሰዎችን ብቻችሁን አይደላችሁም አለሁላችሁ በማለት ነግራ ተስፋ በመስጠት ትረዳቸዋለች። እናንተም ሰው ለመርዳት ብር ወይም የምሰጣቸው ነገር ሊኖረኝ ይገባኛል ብላችሁ እንዳታስቡ፤ ሰው ብር ወይም ቁሳቁስ ብቻ አይደለም የሚቸግረው እናንተ ሲከፋችሁ እናትና አባታችሁ አብሮዋችሁ እንዲሆኑ ትፈልጉ የለ? እነሱም ሲከፋቸው አጠገባቸው የሚሆን ሰው ይፈልጋሉ። ስለዚህ አጠገባቸው በመሆን ብቻ ልትረዷቸው ትችላላችሁ እሺ።

በፀሎት ጥሩ ስነምግባርና ሰውን የመርዳት ፍላጎት እንዲኖራት ያገዛት የቤተሰቧን ምክር መስማቷ ነው። እናትዋ ሁል ጊዜ «ሰው የሚልሽን ስሚ ሰው የሚልሽን ከሰማሽ የምትፈልጊውን ታገኛለሽ» እያለች ትመክራታለች።በፀሎት የእናቷን ምክር ሰምታ ስለምትተገብር ሁሉም ሰው ይወዳታል። እናንተም በሰዎች ዘንድ እንድትወደዱና ጥሩ ስነምግባር እንዲኖራችሁ የቤተሰብ ምክር መስማትና መተግባር አለባችሁ እሺ።

ልጆች በጸሎት ትምህርቷን ጎበዝ ሆና ተምራ ዶክተር መሆንና መቄዶኒያ ውስጥ የሚኖሩ የታመሙ ሰዎችን ማከም ትፈልጋለች። ስለሆነም ሁሌ ትመህርቷን በአግባቡ ትማራለች ።የቤት ስራዋን ትሰራለች እናም ጎበዝ ተማሪ ናት። በሉ ልጆች ለዛሬ እዚህ ላይ ላብቃ ሳምንት በሌላ ጽሑፍ እስከንገናኝ መልካም የትምህርት ሳምንት ይሁንላችሁ።